# ፳

ለሦስት ሳምንታት ያህል ቸሩ የት እንደደረሰ ሳይታወቅ ቀረ ።

ተረሸነ ተብሎ ተወራ ። አልተረሸነም ፣ ወደ ደናኔ እስር ቤት ተወሰደ ተባለ ። የለም ! የለም ! ወደ ኢጣሊያ አገር ተወስዶ አዚናራ ከተባለ ወህኒ ቤት ታስሯል የሚል ወሬም ነፈሰ ። ነገር ግን ይህ ሁሉ መሠረተ ቢስ ወሬ ነበር ፣ ቸሩ በአዲስ አበባ ውስጥ በአንድ የእስረኞች ማጎርያ ሠፈር ነበር ። ቦታው ፣ ከውጭ በባለ ወስፌ ሽቦ የታጠረ ፣ ከውስጥ በግምብ አጥር የተከበበ ሰፊ ሜዳ ሆኖ በመሐከሉ አንድ ሰፊ አዳራሽ ነበረበት ። አንድ ቀን ቀትር ላይ ከእስር ቤቱ ዘበኞች አንዱ የእስረኞችን ስም ሲጠራ ቆየና ቍጥር ፫፻፩ ! ሲደርስ ፣ "ቸሩ በላይነህ !" ሲል ተጣራ ።

"አቤት !" አለው ቸሩ ።

"ና ወዲህ !" አለውና ወደ አዳራሹ እየነዳ ወሰደው ።

የገቡበት አዳራሽ ሰፊና ጨለምለም ያለ ነበር ። በውስጡ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩበት ። አንደኛው እንጨት ወንበር ላይ ተቀምጧል ። ጥቁር መነጽር አድርጓል ። ከፊቱ አንድ ጠረጴዛ አለ ። በጠረጴዛው ላይ መጻፊያ ወረቀትና ብዕር ይታያሉ ። የቸሩም ሽጉጥ በጠረጴዛው ላይ ተጋድሟል ። ሁለተኛው ሰውዬ ራቅ ብሎ ቆሟል ። ከዓይኖቹና ከአፉ በስተቀር መላ ፊቱ በጥቁር ጨርቅ ተሸፍኗል ። ማን እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ አይቻልም ። ሰውነቱም ከብረት እንጂ ከሥጋና ከደም የተሠራ አይመስልም ።



ወንበር ላይ የተቀመጠው ሰውዬ በዓይኑ ላይ ያደረገው የእውር መነጽር ፣ የቆመው ሰውዬ ፊት የተሸፈነበት ጥቁር ጨርቅ ፣ እና ፣ የአዳራሹ ጨለምላማነትና ባዶነት ቸሩን አስፈራው ። ቀፈፈው ! ዘገነነው ።

ብረት ለበስ የመሰለው ሰውዬ ራመድ ብሎ ወደ ቸሩ ሲጠጋ ቸሩ መሬት ላይ ተንደባለለ ። "መታኝ እንዴ ? ሊሆን አይችልም ! እጁን ሳያንቀሳቅስ ሊመታኝ እንዴት ተቻለው ? የለም ! ተሳስቻለሁ ። አልመታኝም ። ብቻ አፌን አመመኝ" ብሎ አሰበና እጁን እንሥቶ ከንፈሩን ሲደባብስ በአፉ የነበረው ደም ወደ ጣቶቹ ተጋባ ። "መትቶኛል !" አለ በሐሳቡ ። "መትቶኛል ፣ ይህ አረመኔ !"

ብረት ለበስ የመሰለው ሰውዬ ከቸሩ አጠገብ ቆሞ ዝቅዝቅ ሲመለከተው ነበር ። ተቀማጩም ሰውዬ በሩቅ ሆኖ ሲያስተውለው ቆየና ጥያቄ ያቀርብለት ጀመር ።

"መሣርያ መያዝ ክልክል መሆኑን እያወቅህ ይህን ሽጉጥ በወቅቱ ለባለሥልጣን ሳታቀርብ ለምን ቀረህ?"

"ፈታሾቹ ከመምጣታቸው በፊት ሳላስረክብ የቀረሁት ከባድ መሣርያ አይደለም በማለት ነበር ። ለማን ማስረከብ እንደሚገባኝም አላውቅም ነበር ። ፈታሾቹ ሲመጡ ግን ለነሱ አስረከብኳቸው ። በዚያ ላይ ሽጉጡ በገዛ ገንዘቤ የገዛሁት ፣ የገዛ ንብረቴ እንጂ ከሰው የዘረፍኩት አይደለም" አለው ቸሩ ዝግ ባለ አንደበት ።

"የፋሺስት ጠላት መሆንህን ታምናለህ ወይንስ አታምንም ?"

"የማምነውም ሆነ የማላምነው የለኝም ።"

"የፋሺስት መንግሥት አበሻን ለማሠልጠን በመምጣቱ የፋሺስትን ሥርዓት ወደህ ተቀብለሃል ? "

"ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል ምርጫው የኔ አይደለም ።"

"አልተቀበልህም ማለት ነው ? "

"ምርጫው የኔ አይደለም ብያለሁ ።"

"ተቀማጩ ፋሺስት ለብረት ለበሱ ምልክት ሰጠው። ብረት ለበሱም ቸሩን ተነሥቶ እንዲቆም አዘዘው ። ቸሩ እየተንገዳገደ ተነሥቶ ሲቆም ብረት ለበሱ አሁንም አዘንግቶ መታው ። ሰውን በማጥቃት የሠለጠነ በመሆኑ ፤ ከአሰነዛዘሩ ፍጥነት የተነሣ የእጁ እንቅስቃሴ አይታይም ነበር ። ቸሩም እንደ ገና መሬት ላይ ወርዶ ተፈጠፈጠ ።

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሆነና ተቀማጩ ፋሺስት ጥያቄውን ቀጠለ ። .

"ከእነማን ጋር ሆነህ ነው ፋሺስቶችን የሚቃወም ድርጊት የጀመርከው ? "

የቸሩ አፍ በድጋሚ ከተመታ በኋላ ሕመሙ አላናግር አለው ። መልስ አለመስጠቱን ሲያይ ተቀማጩ ፋሺስት ጥያቄውን ደገመለት ። ቸሩም ከከንፈሩ የሚፈስሰውን ደም በእጁ ለመጠራረግ እየሞከረ ፤ "ከማንም ጋር " አለው ።

"እውነቱን ብታወጣ ይሻልሃል ። አለዚያ እውነቱን እንድታወጣ እናስገድድሃለን " አለው ተቀማጩ።

እንደ ገና ዝምታ ሆነ ። ቸሩ ደም ተፋ ።



ተቀማጩ ፋሺስት ለብረት ለበሱ እንደ ገና ምልክት ሰጠው ። ብረት ለበሱ ቸሩ ተነሥቶ እንዲቆም እንደ ገና አዘዘው ። ቸሩ ለመነሣት ጣረ ። ነገር ግን አልተቻለውም ። ናላውም ዞረበት ። ይበልጥ እንዳይቀጣው በመፍራት ለመነሣት እንደ ገና ሞከረ ። በመጨረሻም ተነሥቶ ቆመ ። ቀጪው አድብቶ እንደሚመታው በመገንዘብ ከንዱን አንሥቶ ለፊቱ ከለላ አበጀለት ። ቀጪው ግን ፊቱን በመምታት ፈንታ በግራ ቡጢው ጆሮ ግንዱን አለው ። ቸሩ ለመውደቅ ዘንበል ሲል ብረት ለበሱ በቀኝ ቡጢው ተቀበለው ። ሁለቱም ጆሮ ግንዶቹ በየተራ ከተመቱ በኋላ ቸሩ ተዝለፍልፎ ወለሉ ላይ ወደቀ ። የፈሰሰውም ደም ኩሬ አከለ ።

ቀጪው ፋሺስት ከአዳራሹ ወጥቶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአንድ እጁ ባልዲ ውኃ ፤ በሌላ እጁ ቆመጥ ይዞ ገባ ። እንደ በረዶ የሚቀዘቅዘውን ውኃ በቸሩ ፊት ላይ ቸለሰው ። ቸሩ ነፍስ ዘርቶ ተንቀሳቀሰ ።

ቀጪው ፋሺስት በያዘው ቆመጥ ቸሩን ወጋጋው— ከእምብርቱ ዝቅ ብሎ ። ቸሩም ደንግጦ ብድግ ብሎ ተነሣ ። ነገር ግን በሕልም ዓለም ውስጥ እንጂ በውን ዓለም ያለ አልመሰለውም ።

ቸሩ ወደ ውጭ እንዲወጣ ብረት ለበሱ አዘዘው ። ሁለቱም ተከታትለው ወጡ ። ሜዳው ላይ የነበሩትም እስረኞች ፤ "ዛሬ ደሞ ምን ይታይ ይሆን ? " ብለው እያሰቡ የሚሆነውን ለማየት አሰፍስፈው ይጠብቁ ነበር ።

"ሩጥ ! " አለው ብረት ለበሱ ፤ "በቃህ እስክልህ ድረስ እንዳትቆም ። አለዚያ ወዮልህ ! " ሲል አስፈራራው ።

ቸሩ ፍዝዝ ብሎ ፋሺስቱን ይመለከተው ገባ ።

"ሩጥኮ ነው የምልህ ! የማንቡን ጥግ ጥግ ይዘህ ሩጥ ። በቃህ እስክልህ ድረስ እንዳትቆም ።"

ቸሩ እግሮቹን ማንቀሳቀስ ጀመረ ፡ ቀና ደፋ...ቀና ደፋ እያለ ። አሁንም በሕልም ዓለም እንጂ በወን ዓለም ያለ አልመሰለውም ። ጥቂት ርቀት እንደ ሮጠ እግሮቹ ተማትተው በአፍ ጢሙ ተደፋ ። ተፍጨርጭሮ ተነሥቶ እንደ ገና መሮጥ ጀመረ ።

"ብቅ ጥልቅኮ ነው !" አለ ከእስረኞቹ መሐከል አንድ ወጣት ልጅ ። ቸሩ የምኒልክን ሐውልት ይሥል በነበረበት ቀን በሐውልቱ አካባቢ ተኩልኩለው ይመለከቱ ከነበሩት የአራዳ ልጆች አንዱ ነበር ። በውል ባልታወቀ ምክንያት እሱም ታስሮ ነበር ። በዚያ ከታጐሩ እስረኞች መሐከል ሌሎችም ወጣቶች ፡ ጐልማሶች አዛውንቶችና አሮጊቶች ነበሩባቸው ። "እሱ ነው" አለ ልጁ መልሶ ፡ "አንድ እግሩ አጭር ስለ ሆነ ሊሮጥ አይችልም" አለ ኀዘኔታ በተመላበት ድምፅ ።

ልጁ እንዳለውም ቸሩ ጥቂት ቦታ ከሮጠ በኋላ እግሮቹ እንደ ገና ተሳስረው ምድር ላይ ወርዶ ክብልል አለ ። አለ መነሣቱን ሲያይ ፋሺስቱ ራመድ ብሎ ሄዶ በያዘው ቆመጥ ይቀጠቅጠው ገባ ። በዱላ ከመሞት እንደ ገና ብሞክር ይሻለኛል በማለት ቸሩ ከወደቀበት ለመነሣት ጥረቱን ቀጠለ ። ለአንድ አፍታ ተነሥቶ ቆመ ። ነገር ግን ወዲያውኑ መሬት ከዳቸው ። ሕሊናውንም ሳተ ።

ፋሺስቱ በጣም የሚያሥቅ ቲአትር እንደ ተመለከተ ሁሉ እስካካና ቸሩን ትቶት ወደ አዳራሹ አመራ ።



በዚህ ጊዜ ወጣቱ ልጅና ሌሎችም እስረኞች ወደ ቸሩ ሄደው ከወደቀበት አንሥተው ሣር ወዳለበት ወስደው ሸማቸውን አንጥፈው አስተኙት ። ነፋስም ያራግቡለት፡ ደሙንም ይጠራርጉለት ፡ በአጠቃላይም በተቻላቸው መጠን ይረዱት ጀመር...

፳

ብረት ለበሱ ቸሩን ያሠቃይ በነበረበት ሰዓት ሹምባሽ እስጢፋኖስ ወደ ቸሩ መኖሪያ ቤት ሄዶ ሙሉን ሲያባብል ነበር ። በሐምራዊ ወረቀት ተጠቅልሎ በአረንጓዴ ክር የታሰረ ስጦታ በእጁ ይዞ ፡ እጁንም ዘርግቶ ፡

"ከካፒታኖ ባርዚኒ የተላከልሽ ስጦታ !" አላት ።

"ምንድነው እሱ ?"

"ከፍተሽ አታዪውም !"

"ምንም ይሁን ምንም አልፈልግም ብለህ ንገረው"

"ገና ምን እንደሆነ ገልጠሽ ሳታዪው ?"

"አዎ ።"

"ካፒታኖ ባርዚኒን ለማስቀየም ነው ፍላጎትሽ ?"

"ኧረ እኔ በምን አቅሜ !" አለችና ፡ "ለመሆኑ ከኔ የሚፈልገው ምንድነው ?" ስትል ጠየቀችው ።

"አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ምን ሲፈልግ ነው ስጦታ የሚልክላት ?"

“እኔ ምን ዐውቄ ! ”

“ሴት ሆነሽ ይኸንን ሳታውቂ ቀርተሽ ! ” ብሎ እሱ ራሱ ክሩን ፈትቶ ፣ ወረቀቱን ገላልጦ ፣ በወረቀቱ ውስጥ የነበረውን አንድ ትንሽ የጌጥ ሳጥን ከፍቶ አሳያት ። ሳጥኑ ከላይ ጥቁር ሐር ከውስጥ ቀይ ከፋይ ሆኖ በከፋዩ ሥር በጣም የሚያምር የወርቅ ሐብል ነበረበት። ሙሉ ልብ ብላ ተመልክታው፣ “ያ በሐብሉ ጫፍ የተንጠለጠለው ምንድነው ? ” ስትል ጠየቀችው የማወቅ ጉጉት አድሮባት ።

“ይኸ ? እስከዛሬ ድረስ ይኸ ምን እንደሆነ አታውቂም ? ”

“ባውቅማ ባልጠየቅሁህ ። ”

“ፋስ ነው…የፋሺስት አርማ ። ”

“ለስጦታው እግዚአብሔር ይስጥልኝ…ነገር ግን እኔ የምፈልገው ባሌ እንዲፈታልኝ እንጂ የወርቅ ሐብል አይደለም ብለህ ንገረው ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። ”

“ስጦታውን አልቀበልም ካልሽ ካፒታኖ ባርዚኒ በጣም ይቆጣል” አላት ።

“ምንድነው ከኔ የሚፈልገው ? ”

“ወዳጅነትሽን ነዋ ! ካፒታኖ ባርዚኒ ባያፈቅርሽ ኖሮ ይህንን ስጦታ ባልላከልሽ ! ”

“እኔ ክርስቲያን ነኝ ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። በዚያ ላይ ባለ ትዳር … ”

“ካፒታኖ ባርዚኒም ክርስቲያን ነውኮ ! ”



“እንዲህ እርሳም ክርስቲያን የለ ! ለማንኛውም እኔና እርሱን የሚያገናኘን ነገር የለም ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። ”

“ስጦታውን ከናቅሽበትኮ ሊያሳስርሽ ይችላል ” አላት ።

“አስገድደህ ስጣት ካለህ እቅጩን ንገረኝ ” አለችው ።

“አይ ፣ ትዕዛዝ አይደለም ። ፍቅሩን ለመግለጽ ያህል ነው ይኸንን የላከልሽ ። ”

“እንግዲያውስ ስለ ስጦታው እግዚአብሔር ይስጥልኝ…እኔ ግን የምፈልገው ባሌን ፈትተህ እንድትሰጠኝ ነው ብለህ ንገረው ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። ”

“ባልሽ ምንም ጉዳት አይደርስበትም ። ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ በእስር ቤት ይቆያል እንጂ ከዚያ በኋላ ይለቀቃል ። ካፒታኖ ባርዚኒ ራሱ ነው ይኸንን የነገረኝ ። ”

“እንግዲያውስ ባሌ ከእስር ቤት እስኪለቀቅ ድረስ ምንም ዓይነት ስጦታ አልቀበልም ብላለች ብለህ ንገረው ። ”

“ይኸማ የባሰ ያስቆጣዋል ! ”

“ታዲያ ምን አድርጊ ነው የምትለኝ ? ”

“ስጦታውን ተቀበዪ… ደስ ይለዋል ። ”

ሙሉ ተከዝ ብላ ቆየችና ፣ “በል እሺ ይሁን… ስጦታውን እቀበላለሁ… ” ብላ በእጁ የነበረውን ሣጥን ሳትወርስ ፣ “ተስማማሽ ? ጉሽ ! ጉሽ ! እንዲያ ነው

እንጂ !” ሲል አቋረጣት ። ሙላ ፊቱም በደስታ እየተጥበረበረ ቀጠለ ፣ “ወዳጅ ከሆንሽ በኋላ የፈለግሽውን ሁሉ እንደሚያደርግልሽ እርግጠኛ ነኝ ። ከአሁን ወዲያ ከርማ የመጣ ልብስና ጫማ እንጂ እዚህ ማንም ገልጃጃ የሰፋውን አትለብሺም ። ልብስ...ጫማ...ሻሽ...ጌጣጌጥ... ”

“እኔኮ እሱን ላለማስቀየም ስጦታውን እቀበላለሁ አልኩ እንጂ ሌላ አልወጣኝም ” አለችው ሙሉ ፤ “ወዳጁ ለመሆን አልችልም ። በገዢና በተገዢ መሐከል ወዳጅነት ሊኖር አይችልም ። ”

“እሱ በዚህ ዓይን አይደለም የሚያይሽ ። ከልቡ ነው የሚያፈቅርሽ ። እና ፣ ወደ መኖርያ ቤቱ መቼ ይዤሽ ልሂድ ? ”

“ጉዴ ፈላ ! ወደ መኖርያ ቤቱ ? ምን ለመሆን ? ”

“ለምን እንደዚህ አስቸጋሪ ትሆኛለሽ ? ወዳጅነትሽን ነው የሚፈልግ አላልኩሽም ? ” ሲላት ላለ የሰው ኮቴ ሰሙ ። “አንድ ሰው ወደዚህ እየመጣ ነው” አለ ሹምባሽ አስጢፋኖስ ደንገጥ ብሎ ፤ “እኔ መሄድ አለብኝ ። ወደ ካፒታኖ ባርዚኒ መኖርያ ቤት ልወስድሽ ነገ ተመልሼ እመጣለሁ ” ብሎ ፣ ሙሉ የምትሰጠውን መልስ ለመስማት ባለ መፍቀድ ተቻኩሎ ሲወጣ በሬቱ ላይ ከአባተ ጋር ግንባር ለግንባር ተጋጩ ! ። “ይቅርታ ብሎ ፣ ዓይኑን አቅንቶ ሳይመለከት በመሥረቅ ላይ እያለ እጅ ከፍንጅ እንደ ተያዘ ቀጣፊ ሌባ አንገቱን ደፍቶ መንገዱን ቀጠለ ። አባተ ግምባሩን እያሻሸ ቆሞ ተመለከተው ። ከዚያም በኋላ በጥርጣሬ የተሞሉ ዓይኖቹን ወደ ሙሉ መልሶ ፣ “ማን ነው ? ” ሲል ጠየቃት ።



“ሙሉ በበኩሏ ወንጀል ሥርቶ የሕሊና ጸጸት እንዳደረባት ሁሉ እንባ ይተናነቃት ጀመር ።”

“ማነው ፣ ሰውዬው ? ” አላት አባተ መልሶ ።

“የካፒታኖ ባርዚኒ አቃጣሪ...ካፒታኖ ባርዚኒ ይህንን የወርቅ ሐብል ላከልኝ ..እንደ ስጦታ... ” ብላ ትንሰቀሰቅ ጀመር ።

አባተ ከንዴት የተነሣ መናገር አቅቶት ዝም አለ።

“ምን ላድርግ ጋሼ አባተ ? እባክህን ምከረኝ ፣ ጋሼ አባተ ። ይህንን ስጦታ የተቀበልኩት ወድጄ አይደለም፣ ካፒታኖ ባርዚኒን እንዳላስቆጣው ብዬ እንጂ... ”

“ግብዞች ! ” አለ አባተ ፣ ምርር ብሎ ። ነጭ ከጥቁር ይበልጣል ብለው የአረመኔነት ሥራ ሲፈጽሙ ይኖሩና የአበሻ ቤት ሲያዩ “ትልቅነታቸውን” ይረሱታል ! ግብዞች !... ማልቀስ ዋጋ የለውም ፣ ሙሉ ። ይህ ባንዳ በተላላኪነት ሳይሆን በገዛ ፈቃዱ ለመልከስከስ አስቦ የመጣ መስሎኝ ነበር ። የፈለገሽ ባርዚኒ ከሆነስ አትጨነቂ ። ያለ ፈቃድሽ አንዳችም ነገር እንደማያደርግ ዐውቃለሁ ። ስለ ውስጣዊ ደምባቸው አንድ ጓደኛዬ አጫውቶኛል ። ከዚህ ቀደም ግደይ...” አለና ፣ “ግደይን ታውቂው የለም ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ዐውቀዋለሁ እንጂ ! ”

“ወደ ጂቡቲ ሸሽቶ ከመሄዱ በፊት ስለ ውስጣዊ ደምባቸው አጫውቶኛል ። ደምቡ ኤርትራ ውስጥ ያሉትን ነጮች የሚመለከት ቢሆንም እዚህም አንድ ዓይነት ደምብ ሳይኖራቸው የሚቀር አይመስለኝም ። እና ፣ በደምባቸው መሠረት ማንኛውም ፋሺስት ከጥቁር ሴት

ጋር እንዳችም ዓይነት ግንኙነት እንዳይኖረው በጥብቅ የተከለከለ ነው ። ይኸውም የነጭ ደም ከጥቁር ደም ጋር ተቀላቅሎ 'ዘር' እንዳያበላሽ ነው ። ግብዞች !" አለ እንደ ገና ፣ "እና ፣ ባርዚኒ ያለፈቃድሽ ልወዳጅሽ ብሎ ካስቸገረሽ በአለቃህ እከስሃለሁ ብለሽ ንገሪው ። ከዚያ ወዲያ እንኳንስ ሊቀርብሽ ቀርቶ አንቺ ልትቀርቢው ብትሞክሪ ይሸሽሻል " አላት ።

"በችሩ ላይ የበቀል እርምጃ ቢወስድበትስ ፣ ጋሽ አባተ ? "

"እንዳችም የበቀል እርምጃ አይወስድበትም ። ምክንያቱም 'ስላልፈቀድኩት በባሌ ላይ የበቀል እርምጃ ወሰደ' ብለሽ በአለቃው ልትከስሺው ትችያለሽ ። በእነሱ ዓይን ከጥቁር ሴት ጋር ግንኙነት አድርጎ መያዝ በጣም የሚያሳፍርና የሚያዋርድ ድርጊት ነው። ቅጣቱም ቀላል አይምሰልሽ ። "

በተዋቡ ጉንጮቿ ኮለል ብሎ የሚወርደውን እንባ እየጠራረገች ፣ "እውነት እስከዚህ ቀላል ነገር ይመስልሃል ፣ ጋሽ አባተ ?" አለችው ፤ "የችሩ ነገር ነው ያሳሰበኝ ። "

"አስረው ያቆዩታል እንጂ ሌላ ምን ያረጉታል !"

"የሽጉጡስ መዘዝ ... ? "

"ሽጉጥ የለኝም ብሎ አልካደም ። በጠየቁት ጊዜ ሰጣቸው ። ይኸኮ ከባድ ወንጀል አይደለም ። አባባን የገደሏቸው መሣሪያ የለኝም ብለው ከካዱ በኋላ መሣሪያዎቹን ስላገኙባቸው ብቻ ነው ። ሞኙ ነው አባባን አሳልፎ የሰጣቸው ፣ ከሐዲ ! "



"ሞላ ? ምን አጠቀማለሁ ብሎ ? ቀኛዝማች ከሌሎች አሽከሮቻቸው አብልጠው የሚወዱት እሱን ነበር። በገዛ ጣታቸው እንዳላጐረሱት ሁሉ !"

"እሱ ነው አሳልፎ የሰጣቸው ። ከሐዲ"! አለ ፣ እንደ ገና ፤ "ፋሺስቶች በገንዘብ እየደለሉ ጌቶቻቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ይገፋፏቸዋል ። እነሱም ያጐረሳቸውን ጣት ከመንከስ አይመለሱም ። ፋሺስቶች ኢትዮጵያን ስለያዙ እነሱ ራሳቸው ከአሽከርነት ወጥተው ግራዝማችና ቀኛዝማች የሚሆኑ ይመስላቸዋል ። ደደብ ሁሉ!" አለ በንዴት ።

"ሁሉምኮ አይደሉም ፣ ጋሽ አባተ ። በአንድ በሁለት ሰው ምክንያት ሁሉንም መሳደብ ጥሩ አይደለም ።"

"እሱንማ መች አጣሁት ! ንዴቴም በእነሱ ላይ አይደለም ፣ በፋሺስቶች ላይ እንጂ...በላያችን ላይ ተቀምጠው እንዲጨፍሩብን ያመቻቸው ዘንድ እርስ በርሳችን እያባሉን ናቸው ። "

፳

የፋሺስት ሥርዓት በኢትዮጵያ ላይ ሰፈነ ። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለዘለቄታው ቅኝ ግዛት አድርገው ለመኖር ባላቸው ውጥን መሠረት የአጭር ጊዜና እስከ ኀምሳ ዓመት የሚቆይ የረጅም ጊዜ ዕቅድ በመንደፍ ሥራቸውን ጀመሩ ። ለእነሱ የገቡና ሥርዓቱንም የተቀ

በሉ ባንዳዎች ቢኖሩም ፣ በአርበኝነትና በውስጥ አርበኝነት የተሠማሩ ቆራጦች በብዛት ስለ ነበሩ ጣሊያኖች ባንድ በኩል የአቅኝነት ሥራቸውን ሲያካሂዱ በሌላ በኩል እነዚህን እየተከታተሉ ያስሯቸው ፣ ይገርፏቸው፣ ይጨፈጭፏቸውም ነበር ።

አባተ ሺፈራው የውስጥ አርበኛ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በሥጋት ይኖር ነበር ። በአንድ ፊት የቀኛዝማች ሺፈራው ልጅ በመሆኑና አባቸውም በመገደላቸው ፣ በሌላ ፊት የተማረ ሰው በመሆኑ ፣ ጣሊያኖች በዓይነ ቁራኛ ይጠባበቁት ነበር ። በመጀመሪያ ከቀድሞ ሥራው አባረሩት ፣ ቀጥሎም ከሚኖርበት ሆቴል አስወጡት ። በዚህም ምክንያት ወደ አባቱ ቤት ገብቶ የቤተሰቡን ንብረት ከማስተዳደርና በውስጥ አርበኝነት ሥራው ከመጠንከር በስተቀር ሌላ ሐሳብ አልነበረውም ። “ከእኛ ሥራ የናንተ የውስጥ አርበኞች ሥራ ይበልጥ አደገኛ ይሆናል” ሲል ባሻ ቅጣው የነገረው ቃል ዘወትር በውስጥ ጆሮው ያስተጋባ ነበር ።

ባሻ ቅጣው ደንቴንና ሕፃናት ልጆቹን ወደ ባላገር ሰድዶ እሱም ለውጭ አርበኝነት የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘገጃጅቶ ካጠናቀቀ በኋላ አንድ ቀን ሌሊት ከተደበቀበት ወጥቶ ወደ ቤቱ አመራ ። ትዳር የያዘበት ሕፃናት ልጆቹ የተወለዱበት ፣ እሱና ደንቴ ደስታና ኀዘን የተካፈሉበት ሣር ቤታቸው ባዶ...እና ነበር—ያን ቀን ሌሊት ። ከውጭ ተቆልፎም ነበር ። ባሻ ቅጣው በሩን ከፍቶ ገባ ። በውስጡ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ አንድ ታኒካ ቤንዚን ብቻ ነበረበት ። ነዳጁን በወለሉና በግድግዳው ላይ ረጭቶ ፣ ከቤቱም ወጥቶ የቀረውን ነዳጅ በጣሪያው ሣር ክዳን ላይ አርከፍክፎ ክብሪት ጭሮ ወረወረበት ። ቤቱ መቀጣጠል ሲጀምር ከበጋሻው ጋር



ወደ ተቃጠሩበት ሥፍራ ሮጦ ሄዶ እሳቱን በሩቅ ሆኖ ይመለከተው ገባ ። «ከአሁን ወዲያ ቤት ንብረት የለኝም ። ይህች ቅድስት አገር ነጻ እስክትወጣ ድረስ ጣሊያንን ባልዋጋ እግዚአብሔር ሥጋዬን በምድር ነፍሴን በሰማይ ያቃጥላት» ብሎ ለራሱ ቃል ኪዳን ገብቶ ከከተማው ወጥቶ ሄደ ።

ባሻ ቅጣው በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁለት መቶ የሚሆኑ ወጣት ተዋጊዎችን መልምሎ የአርበኝነት ሥራውን ጀመረ ። በጋሻው የሱ ምክትል አዛዥ ሆነ ። በየቀኑም ተጨማሪ ወጣቶች ለመመልመል እየመጡ ይመዘገቡ ነበር ። ወላጆቻቸው የተገደሉባቸው ፣ ሚስቶቻቸውና እህቶቻቸው የተደፈሩባቸው ኢትዮጵያውያን ሁኔታው እያስመረራቸው ወደ ጫካ ይጐርፉ ነበር ። ባሻ ቅጣው ከሁሉም ይልቅ ደስ ያለው ተመስገን በሕይወት ኖሮ ያለበትን ጠይቆና አጠያይቆ ያገኘው ዕለት ነበር ። ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጠጉሩ ድረስ አስተውሎ እየወና ፣ «ይህንን ልብስ ከየት አመጣኸው ?» ሲል ጠየቀው ፣ ባሻ ቅጣው ።

«አንድ ባንዳ ገድዬ ነዋ ፣ ባሻዬ !» ሲል መለሰለት ተመስገን ። «ገድዬው ልብሱን ገፈፍኩት ። ወደዚህ ስመጣም ባንዳ መስዬ ተዝናንቼ እንጂ ጭለማ ለብሼ አይደለም የመጣሁት ፣ ባሻዬ ።»

«እንዲያ ነው እንጂ !» አለው ባሻ ቅጣው ፣ እጅግ በጣም ደስ ብሎት ።

«ሌላም የማሳይዎት አለኝ ፣ ባሻዬ» አለው ተመስገን ቀጠል አድርጎ ፣ ተጣጥፎ የተሻጠ አንድ ነገር ከኪሱ እያወጣ ።

«ምንድነው እሱ ?»

«የመኰንን ቆብ ነው ፥ ባሻዬ... የጣሊያን መኰንን ። ይህንን ሰለባ ይዤ ባልመጣ ኖሮ ጣልያን ገደልሁ ብልዎት ያምኑኝ ኖሯል ?» አለው፥ በልቡ በጣም ከፍ ያለ ኩራት ተሰምቶት ።

«ከአሁን ጀምሮ የአሥር አልቅና ማዕርግ ሰጥቼሃለሁ ፥ ተመስገን ። በእውነት ይገባሃል... !» አለው ።

ባሻ ቅጣው አሮጌ ጠበንጃውንና በውስጡ የነበረውን አንድ ቃታ ጥይት ከሰጠው ቀን ጀምሮ ተመስገን ዳግመኛ እንደተወለደ ይቆጥረው ነበር ። የአንድ ወዳጁ የአረሩ ሞትም ጣልያኖችን ለመውጋት ተጨማሪ ኃይል ሰጥቶት ነበር ። እንደ ሌሎቹ ነጻ ኢትዮጵያውያን ነጻ ጦረኛ ሆኖ ሲዋጋ ፥ አንድ ጥቁር ወታደርና አንድ ነጭ ፥ ያውም የመቶ አልቅና ማዕርግ ያለው ነጭ ገድሎ ስለነበረ የመኰንኑን ቆብ ከአስከሬኑ አንሥቶና አጣጥፎ ኪሱ ውስጥ ከቶት ነበር...እንደ ተጨባጭ ማስረጃ ።

፯

የደፈጣው ውጊያ ተፋፋመ ። በሸዋ ፥ በጐጃም ፥ በወለጋ ፥ በከፋ በሲዳሞና በተቀሩትም አካባቢዎች የአርበኝነት እንቅስቃሴ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ሄደ ። የአርበኞች መሪዎች ስማቸው ይፋ እየወጣና እየገነነ ሄደ ።



አበበ አረጋይ...ገረሱ ዱኪ...ኃይለ ማርያም ማሞ... በላይ ዘለቀ...ዘውዴ አባኮራን...ታከለ ወልደ ሐዋርያት...ዘውዴ አባፈርዳ...በቀለ ወያ...ዝርዝሩ ማለቂያም የለው ። እነዚሁ ሁሉ በየፊናቸው የያዙትን ጦር ይዘው ይዋጉ ነበር ። አንዳንድ ጊዜም እርስ በርሳቸው እየተገናኙ አለዚያም እየተላላኩ ይመካከሩ፥እንቅስቃሴ አቸውን ያቀነባብሩ ነበር ።

ከጊዜ በኋላ በፋሺስት መንግሥት እንደራሴነት ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረው ማርሻል ባዶሊዮ ወደ አገሩ ተጠርቶ በምትኩ ጄኔራል ግራዚያኒ ተሾመ ። ግራዚያኒ በጭካኔው ከባዶሊዮ የከፋ እንጂ ያነሰ አልነበረም ። የአርበኞችም እንቅስቃሴ እጅግ አድርጎ አስቆጥቶት ነበር ። "እነዚህ ሽፍቶች መደምሰስ አለባቸው" አለ ግራዚያኒ፤ ሥልጣኑን ከተረከበ በኋላ ፤ "እኛ ወደ አበሻ አገር የመጣነው አበሻን ለማሠልጠን ሆኖ ሳለ ሽፍቶቹ ዛሬ የገነባነውን ነገ የሚያፈርሱብን ከሆነ አንድ በአንድ ተገቢ ቅጣታቸውን መቀበል አለባቸው" ሲል ወሰነ ።

በእርግጥም ጄኔራል ግራዚያኒ "ሽፍታ" ብሎ የሚጠራቸው የኢትዮጵያ አርበኞች "ለሮማውያኑ" ቅኝ ገዥዎች መቅሠፍት ሆነውባቸው ነበር ። በአልታሰበ ሰዓት፥ ከአልታሰበ ቦታ መጥተው አደጋ ይጥሉ ነበር ። አደጋ ጥለው ከሸሹ በኋላ እንደ ገና በአልታሰበ ሰዓት ፥ ከአልታሰበ ቦታ መጥተው በመሠራት ላይ የነበሩትን ፥ ወይም ሥራቸው የተጠናቀቀላቸውን ሕንፃዎች ድልድዮች ፥ መንገዶች ፥ የመገናኛ መሥመሮችና እነዚህን የመሳሰሉትን ሁሉ ያፈራርሱ ይንዱ ያቃጥሉም ነበር ።

አንድ ቀን ጣሊያኖች አርበኞችን ለመበቀል ይዘገጃጁ በነበሩበት ሰሞን አንድ ሰው ወደ አባቱ ቤት መጥቶ

በሩን አንኳኳ። አባተ በሩን ከፍቶ አስገባውና፣ "ምን አዲስ ነገር አለ፣ ማሞ?" ሲል ጠየቀው።

ማሞ እንግዳ ሰው አልነበረም። ግደይ ገብረግዚእ ወደ ጂቡቲ በሄደበት ቀን ዋዜማ በኢቴጌ ሆቴል ውስጥ መጠጥ ሲቀዳላቸውና ራሱም ተጋብዞ ሲጠጣ የነበረ አሳላፊ ነበር። ውስጣዊው ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ እሱም የውስጥ አርበኞች አባል ሆኖ ነበር።

"እነባሻ ቅጣው በአደጋ አፋፍ ላይ ይገኛሉ፣ ጋሽ አባተ" አለው ማሞ፣ ሁለቱም መንበር ስበው ከተቀመጡ በኋላ።

"እንዴት?" ሲል ጠየቀው አባተ።

"ጣሊያኖች እነባሻን አድነው ለማጥፋት በመዘጋጀት ላይ ናቸው።"

"ሊዘምቱባቸው?"

"አዎን።"

"መቼ?"

"ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ።"

"ማን ነው የነገረህ?"

"ጣሊያኖች ዘወትር እየለፈለፉ ናቸው፣ ጋሽ አባተ። አፋቸውን በያዙቸው በሌላው ባመለጣቸው!" ብሎ ሣቅ አለና፣ "ወሬውን ያገኘሁት ከእነሱ ከራሳቸው ነው። ከዚያም በኋላ ከተወዳጀሁት ከአንድ ባንዳ ዘንድ ሄጄ አረጋግጫለሁ።"

"ማነው ባንዳው?"

"ያውቁት ይሆን፣ ጋሽ አባተ...? ሹምባሽ እስጢፋኖስ ይባላል።"



"ሹምባሽ እስጢፋኖስ...? ዐውቀዋለሁ እንጂ! አቃጣሪውም አይደል?"

"ነው ጋሽ አባተ። አቃጣሪው ሹምባሽ እስጢፋኖስ ራሱ! ከባርዚኒ ሥር ነው የሚሠራው።"

"እሱ የነገረህ የሚያስተማምን ይመስልሃል ታዲያ?"

"እሱኮ በተጨማሪ አረጋገጠልኝ እንጂ በመጀመሪያ የሰማሁት ከራሳቸው አፍ ነው ጋሽ አባተ።"

"በጁ ምን ያህል ወታደር እንደሚዘምት ነገረህ?"

"ስምንት ካሚዮን ወታደር ሊዘምት ነው አለኝ።"

"ስምንት ካሚዮን?" ብሎ አሰበና፣ "አራት መቶ ያህል ወታደር መሆኑ ነው?"

"እንደሱ መሰለኝ። እና፣ ታንክ ሁሉ ይዘው ሊሄዱ ነው አለኝ።"

"ስንት ፈረንጅ ይሄድ ይሆን?"

"ከአምስት እስከ አሥር ቢሆኑ ነው እሱ እንደ ነገረኝ። የተቀረው ሁሉ ጥቁር ወታደር ነው። እና፣ ለወሬው አምስት መቶ ሊሬ ከፈልሁት።"

"ለገንዘቡ አትጨነቅ። እንካ" ብሎ ከኪሱ አንድ ሺህ ሊሬ አውጥቶ ሰጠውና፣ "ይበልጥ የሚጠቅመን ወሬ ለመሰብሰብ የተቻለህን ያህል አድርግ፣ ማሞ። ይህም መረጃ በጣም የሚጠቅመን ሳይሆን አይቀርም" አለው።

ይህንን ከተጨዋወቱ በኋላ ማሞ ወደ ሆቴሉ ለመመለስ ተነሥቶ ወጣ። አባተም የእጅ ባትሪውን ካለበት አንሥቶ በቀኝ እጁም የብረት ከዘራ ይዞ ከቤቱ ወጣ። ከዘራ የያዘው በድንገት የሌሊት ጅብ ያጋጠመኝ እንደ

ሆነ ብሎ በማሰብ እንጂ ለሌላ አልነበረም ። ጣሊያኖች አዲስ አበባን ከያዙ ወዲህ ማጅራት መቺም ሆነ ሌላ ተራ ወንበዴ በከተማው ክልል ውስጥ እጅግም አይታይም ነበር ። ካራቢኒዬሪ የተባሉ የጣሊያን ፖሊሶች ጸጥታ ያስከብሩ ነበርና ።

አባተ በባትሪው ብርሃን እየተመራ ሲሄድ ሲሄድ ቆየና ከአሰበው ቦታ ሲደርስ ሦስት ጊዜ አከታትሎ አፏጨ። አላና ምልክቱ ገብቶአቸው ሊጎርሱት የነበረውን መልሰው መሶቡ ላይ አስቀምጠው ተነሥተው የጓሮአቸውን በር ከፈቱለት ። አላናና ወርቂቱ እራት በመብላት ላይ ነበሩ ። ያሳደጉት ልጃቸው ግን ቀደም ብሎ በልቶ ተኝቶ ነበር ።

አባተ እምድጃው ውስጥ ሲንቀለቀል ወደ ነበረው እሳት ተጠግቶ በርጩማ ላይ ዐረፍ አለና ፣ "በዚህ ሰዓት መጥቼ ከማዕድ ላይ ስላስነሣሁዎት ይቅርታ አርጉልኝ" አለ ።

"እስቲ ጠጋ በል...የናንተ ነገር ! " አሉ አላና ፈገግ ብለው ።

"እውነት በጣም አዝናለሁ ፣ አብዬ አላና ። አስቸኳይ ነገር ባያጋጥመኝ ኖሮ በዚህ ሰዓት ባልመጣሁም ነበር ።"

"በልኮ ጠጋ በልና ያዝ !"

"እራቴን ገና ዱሮ ነው የበላሁት ፣ አብዬ አላና ።"

"እራትህን ብትበላም ለአንድ ወይ ለሁለት ጉርሻ ቦታ አታጣለትም !"

"እውነት ! እውነት ! ለአንድም ጉርሻ ቦታ የለኝም።"



"በል እሺ ተወው...ምግቡ እስከዚህም ስላልሆነ እናስቸግርህም" ብለው ፊታቸውን ወደ ባለቤታቸው መልሰው ፣ "ባይሆን ጠላ አምጪለት ፣ ወርቄ" አሏቸው።

ወርቂቱ ጠላ ለማምጣት ሲሄዱ ፣ "የመጣህበትን ንገረኝ ፣ ልጅ አባተ" አሉት ፣ አላና ።

"በልታችሁ ስትጨርሱ ቢሆን አይሻልም ?"

"ምነው ? ልታረዳን ይሆን የመጣኸው ?"

"አይ ! መርዶስ አይደለም...ያውም በዚህ ሰዓት !"

"ታዲያ ንገረኝ እንጂ...የሥራ ጉዳይ ከሆነ ንገረኝ" አሉት ።

አላናም የውስጥ አርበኞች አባል ነበሩ ።

"ባሻ ቅጣው በአደጋ አፋፍ ላይ ነው እሉ ።"

"ያዙት ?" አሉ ፣ ደንገጥ ብለው ።

"አልያዙትም ፣ አብዬ አላና ። ነገር ግን ጣሊያኖች ባሻንና ሰዎቹን ጨርሶ ለማጥፋት በዝግጅት ላይ ናቸው የሚል ወሬ ደርሶኛል ።"

"እና ፣ የኔ ግዳጅ ምንድነው ? "

"ጣሊያኖች ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊያድኑት እንደሚመጡ ሄደው ይንገሩት ። በሠፈር ካላገኙትና በሁለት ቀናት ውስጥ ወደ ሠፈር የማይመለስ ከሆነ ወዳለበት ቦታ ድረስ ሄደው ይንገሩት ። የት እንደሚገኝና መቼ እንደሚመለስ ድንቄ ትነግርዎታለች ። "

"አሁኑኑ መነሣት ሊኖርብኝ ነዋ ! "

"ነገ ጥዋት ማልደው ቢነሡ ይሻላል ። "

"ነገሩ እስከዚህ አጣዳፊ ከሆነ ሌሊቱን ስንጓዝ ባደር ይሻል ይመስለኛል ።"

"የሌሊት ጉዞ አያስተማምንም አብዬ አባና ። በሌሊት ሲጓዙ አንዳች እክል አግኝቶዎት መልእክቱን ሳያደርሱለት ቢቀሩ በባሻና በሰዎቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል ። ስለዚህ ነገ ጥዋት ማልደው ቢነሡ ይሻላል ።"

"ጥሩ" አሉ አባና ፤ "እሱ ይሻላል ካልህ ነገ ጥዋት ጎህ ሲቀድ ተነሥቼ እገሰግሳለሁ" ብለውት ሐሳባቸውን ወደ እራታቸው መለሱ ። ወርቂቱም ማንቆርቆሪያና ብርጭቆ አምጥተው ለአባተ ጠላ ቀዱለትና ከባለቤታቸው ጉን ቁጭ አሉ ።

ጠላው ጉሽንቱ ያለቀለት የበሰለ ጠላ ነበር—ቀይ እንደ እንጆሪ...አባተ ሲጨዋወት ቆይቶ ማዕድ ከተነሣ በኋላ ተሰናብቶአቸው ወጣ ።

፳

"ባርዚኗን እዚሁ ቁጭ ብለን እንጠብቀውም ቀውሴ" አለ ባሻ ትጋው የከመቻው ወሬ ከደረሳቸው በኋላ ።

"እህሳ ?"

"እንዳይደክመው ትንሽ ቀረብ እንልለታለና !"

"እዚሁ እንጥፈን ብንጠብቀው አይሻልም ፣ ባሻ !"



"የለም ! ትንሽ ቀረብ እንልለታለን...እንዳይደክመው !"

"እስከ የት ድረስ ?"

"እስከ ቢተው መኖሪያ ሠፈር ነዋ !" ብሎ ማቀ ።

ቢተው ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ከመያዛቸው በፊት ሸፍቶ የነበረ ባላባት ነበር ። በመሸፈቱ ምክንያት ታድኖ ተይዞ የአምስት ዓመት እስራት ተፈርዶበት ነበር ። ፍርዱም ጸንቶበት እስር ቤት እንዳለ ጣሊያኖች ገቡ ። ባላባት በመሆኑ ሕዝቡን ይሰብክልናል ብለው በማመዛዘን ጣሊያኖች ከወህኒ ቤት ፈትተው ፣ የግራዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው በተወለደበት አገር ሾሙት ።

ቢተው ከወህኒ ቤት ተለቆ ሹመት በማግኘቱ በጣም ደስ ብሎት ለጣሊያኖች ውለታ ለመመለስ ያህል በተቻለው መጠን ይሯሯጥላቸውና ሕዝቡንም ይሰብክላቸው ነበር ።

"ጣሊያኖች አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያልሠሩት ተአምር ምን አለ !" አለ አንድ ቀን ሕዝቡን ሰብስቦ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ፣ "የመኪና መንገድ...ድልድይ...የድንጋይ ቤት...የራዲዮ ጣቢያ... የኮሬንቲ መብራት...ምን ተቆጥሮ ያልቃል ! ጣሊያኖች አዲስ አበባን ከየጠቅላይ ግዛቱ በአውራ ጎዳና በማገናኘት ላይ ናቸው ። አዲስ አበባ ራሷ እየተስፋፋች ነች። ከአራዳ በስተምዕራብ የነበረው ልቅ አገር ዛሬ ሜርካቶ ተብሎ በውስጡ የማይገኝ ነገር የለም ። የመገበያያ በረንዳዎች... ሱቆች... መኖሪያ ቤቶች... ቢሮዎች:... ምን ተቆጥሮ ይዘለቃል !" ብሎ ጭራውን አየር ላይ መታ መታ አደረገና ቀጠለ ፤—

"አዲስ አበባ ብቻ አይደለችም በሚያስደንቅ ሁኔታ የእተስፋፋች የምትሄደው ። ጅማ…ድሬዳዋ…ጐንደር… የተቀሩትም የየጠቅላይ ግዛቱና የየአውራጃው ከተሞች በመለወጥና በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ ።

"ጣሊያኖች በየቦታው የውኃ ጉድጓድ እያስቆፈሩ የቧምቧ ውኃም እያስገቡ ፥ የስልክ መሥመር እየዘረጉ ናቸው ። ከዚህ ሁሉ የላቀውን ተአምር ደሞ ልንገራችሁ" ብሎ ፥ ጭራውን እንደ ገና አየር ላይ መታ መታ አድርጎ ፥ በአዲስ አበባ ከተማ ሲኒማ ቤት ስለ መኳቋሙ ሲነግራቸው ሲዘገጃጅ ባለ ከአድማጮቹ መሐከል አንዱ ሰው ፥ "ይህን ሁሉ ያደረጉት ለራሳቸው እንጂ ለእኛ አስበው ያደረጉት አይመስለኝም ፥ ግራዝማች" ሲል በድፍረት አቋረጠው ። ቢተውም ቆጣ ብሎ ፥ "ምን አልክ ! ?" አለው ።

"ይህን ሁሉ ያደረጉት ለራሳቸው እንጂ ለእኛ አስበው ያደረጉት አይመስለኝም ፥ ግራዝማች" ሲል ደገመለት ተናጋሪው ።

"እንዴት አንተ ?" አለው ቢተው የባሰውን ተቆጥቶ ፥ "ሐኪም ቤቶች የተሠሩት ለማን ሆነና ! ሆድህን ሲቆርጥህ ፥ ወባ ይዞ ሲያንዘፈዝፍህ ፥ ዓይንህ ሲጨናበስብህ ወደ ሐኪም ቤት ሄደህ ገንዘብህን ከፍለህ እንዳትታከም የከለከለህ ሰው አለ ? አውራ ጐዳናዎች የተሠሩትስ ለማን ሆነና ! ከዚህ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ስትፈልግ እንደ ዱሮ በእግርህ ነው የምትንዘጠዘጠው? ከመኪና መሣፈርያ ሄደህ ገንዘብህን ከፍለህ ፥ ካርኔ አስቆርጠህ ፥ በትሬንታ ኳትሮ እንዳትጓዝ የከለከለህ አለ ? ትሬንታ ኳትሮው ጠር—ጠር እያለ በስተኋላው ጢስ እየተፋ ፥ አቧራ እያነሣ ሲበርር አሱ በአንድ ቦታ የቆመ

መስሎ ማር ቅጠሉ፣ ዛፍና ምድሩ እየሸሸ ወደ ኋላ የሚ ሄድ እንደሚመስል አይተህ አታውቅም አንተ ሙጢ አፍ?" ብሎ መልስ ሳይጠብቅ ዓይኖቹን ከአቋረጠው ሰውዬ ላይ አንሥቶ በአድማጮቹ ላይ ጣለ። "ይህ ሙጢ አፍ አቋረጠኝ እንጂ ልነግራችሁ የፈለግሁት ጣሊያኖች ስላቋቋሙት ሌላው ተአምር ነበር" አለ፤ "ሲኒማ ቤት ይባላል። እንደዚህ ሙጢ አፍ ያሉ ደንቆሮዎች 'ሰይጣን ቤት' ብለው ይጠሩታል። ቤቱ ግን ሲኒማ ቤት እንጂ ሰይጣን ቤት አይደለም" ሲል ያው ሰውዬ፣ "እስክዚህም ደንቆሮ አይደለሁም፣ ግራ ዝማች" አለው፤ አሁንም በድፍረት፣ "በዚያ ላይ ሲኒማ የሚባለው ነገር ከጣሊያኖች በፊት የነበረ እንጂ እነሱ ያመጡት አዲስ ነገር አይደለም።"

"እረ አንድ በሉልኝ ይህንን ሙጢ አፍ! ጣሊያኖች ከመግባታቸው በፊት የሚንቀሳቀስ፣ የሚናገር ሰው የሚያደርገውን ሁሉ የሚያደርግ ሲኒማ ነበር ነው የምትለው! ደደብ! ሁለተኛ ታቋርጠኝና ዋ!" ብሎ አስፈራርቶት ንግግሩን ቀጠለ። "ስለ አዲሱ ሲኒማ ነበር የምነግራችሁ" አለ፣ "በጭለማ ቤት ውስጥ ተቀመጠው ከፊት ለፊት ባለው ግድግዳ ላይ የሚታየው ትንግርት ተአምር ይባል እንደ ሆነ እንጂ ሌላ ቃል ሊገኝለት አይችልም! የሮማ ሰዎች ፈረስ ላይ ተቀምጠው፣ ጋሻ መክተው፣ ጦር ወርውረው ከጠላቶቻቸው ጋር ተዋግተው ድል ሲያደርጓቸው...ቆነጃጅት የፈረንጅ ልጃገረዶች የአበባ እቅፍ ይዘው ሲቀበሏቸው... ሲስሟቸው...ይህና የመሳሰለው ሁሉ የሚታየው በተንቀሳቃሽ ሥዕል አማካይነት እንጂ በውን አይደለም። ትርዒቱ በሚታይበት ጊዜ መብራት ቢበራ ከነጭ ግድግዳ በስተቀር ሌላ ነገር የለም። መብራት ሲጠፋ ግን

ያ ሁሉ ነገር እንደ ተና ሕይወት አግኝቶ ውርውር ሲል ይታያል ፡፡ ሙዚቃም ንግግርም ይሰማል ፡ ታዲያ ይህን ዓይነቱን ትርዒት ያመጡት ጣሊያኖች እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር ሥራ ካልተባለ ምን ተአምር ሥራ ለማለት ይቻላል !” ብሎ ንግግሩን ሲያበቃ ጭብጨባው አስተጋባ ፡፡

“በል እሺ አሁን ተናገር አንተ ሙጢ አፍ !” አለ ቢተው ጭብጨባው ጋብ ሲል ፤ “በል እስቲ ተና ገር...ጣሊያኖች የሚሠሩት ተአምር ራሳቸውን ብቻ ለመጥቀም እንጂ እኛን ለማሠልጠን አይደለም ነው የምትለው ?”

ሰውዬው መልስ መስጠት ባይችግረውም ያን ያህል ከተዘለፈ በኋላ ለመናገር አልደፈረም ፡፡ መልስ ያጣ መስሎ አንገቱን ደፍቶ ቀረ ፡፡ የተሰበሰበውም ሕዝብ በአንድ ፊት በሰውዬው ላይ ሲሥቅና ሲሣለቅ በሌላ ፊት ለቢተው መልስ ያጨበጭብለት ገባ ፡፡

ቢተው ጣሊያኖች የሾሙት ባለሥልጣን ስለ ነበር በወረዳው ሕዝብ ዘንድ ተሰሚነት እንደ ነበረው ባሻ ቅጣው ያውቅ ነበር ፡፡ ከጠላት ጋር አትተባበር ሲል ከአንድ ሁለቴም ማስጠንቀቂያ ልኮለት ነበር ፡፡ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች ወደ ሮማ ልከው ታላቅነታቸውን በዓ ይኑ እንዲያይ እንደሚያደርጉና መተባበሩን ከቀጠለም የበለጠ ሹመትና ሽልማት እንደሚሰጡት ቃል ገብተ ውለት ስለ ነበረ የባሻ ቅጣውን ማስጠንቀቂያ ከቁም ነገር ሊቈጥረው ሳይችል ቀረ ፡፡

ባሻ ቅጣው የቢተውን ማንነት ስለሚያውቅ ጣሊ ያኖች አርበኞችን ለማደን በሚመጡበት ጊዜ ቢተው ዘንድ እንደሚያርፉ ፤ ቢተውንም መንገድ መሪ እንደሚ



ያደርጉት ገና ዱሮ ጠርጥሮ ነበር ፡፡ እንደ ጠረጠረውም ሳይሆን አልቀረ ፤ ጣሊያኖች ዘመቻ በተነሡበት ቀን ምሽት እሱ ዘንድ ዐርፈው ነበርና ፡፡

የቢተው መኖርያ ቦታ በእሾህ አጥር የታጠረ፣ ነፋስ እንኳን የማያስገባ በውስጡ በርካታ ቤቶች ያሉ በት ፤ ምድረ ግቢውም ለድንኳን መትከያ በጣም ያመቸ ነበር ፡፡

ቢተው ባርዚኒን የሚያካክሉ ታላላቅ የጣሊያን ባለ ሥልጣኖች ለማስተናገድ ዕድልና ክብር በማግኘቱ ታላቅ ደስታ ተሰማው ፡፡ በወረዳው አሉ የሚባሉትን ምርጥ ምርጥ ሰንጋዎች አስመጥቶ አሳረደላቸው ፡፡ ባንዳዎቹ ወታደሮች እንደ አገር ባህል ጮማ ሲቆርጡ አመሹ ፡፡ ፈረንጆቹ የወጥ ቤት ሠራተኛ ይዘው መጥተው ስለ ነበር የተለምዶ ምግባቸውን የእስፓጌቲ ቁልል አዘጋ ጁላቸው ፡፡ ከእስፓጌቲው በኋላ ተበልቶ የማይጠገብ የጭቅና አርስቶ አቀረበላቸው ፡፡ ከዋናው ምግብ በኋላ ፍራፍሬ ቀርቦላቸው በሉና ፤ የሚወዱት ወፍራም ቡና ቀረበላቸው ፡፡ ጣሊያኖች በተለይ የኢትዮጵያን ቡና ጠጥ ተው አይጠግቡም ነበር ፡፡

ይህ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ የመጠጥ ግብዣ ቀጠለ፡፡ ጣሊያኖች የሚጓጓዙት በካሚዮን ስለሆነ የሚያስፈል ጋቸውን ስንቅም ሆነ መጠጥ በገፍ ይዘው ይሄዱ ነበር ፡፡ ያን ቀን ሌሊት ከራት በኋላ የተከፈተው የወይን ጠጅ ጠርሙስ አምስት መቶ ይጠጋ ነበር ፡፡ ጣሊያኖቹ ውድ የሆነውን ኪያንቲ ሲያጣጥሙ ባንዳዎቹ ወታደሮች ረከስ ያለውን ፤ ነገር ግን እንደ ኪያንቲው ለብዙ ዓመ ታት ከርሥ ምድር ውስጥ ተቀምጦ የበሰለ የጣሊያን አገር ወይን ጠጅ ሲለጉ አምሽተው ሰዓቱ ወደ እኩለ ሌሊት ሲጠጋ ሁሉም ወደየተመደበላቸው ሥፍራ ተበታትነው ማደሪያቸውን ያንጣጥፉ ጀመር ፡፡

## ፱

ሌሊቱ ጸጥ ያለ ነበር ። አልፎ አልፎ በሩቅ ከሚሰማ የቀንድ ከብቶች እምቧታ በስተቀር ሌላ ድምፅ አልነበረም ። ጨረቃ አካባቢውን በብርሃንዋ አጥለቅልቃው ነበር ። ከዋክብትም በሩቅ ሆነው ይብለጨለጩ ነበር።

የባርዚኒ ወታደሮች ጠግበው በልተው ጠግበው ጠጥተው ስለነበረ በየወደቁበት ሥፍራ ያንኮራፉ ይገላበጡና ይቃዡ ነበር ። የምድረ ግቢውን አራት በሮች ይጠብቁ የነበሩ ስምንት ዘበኞች እንቅልፍ ባይወስዳቸውም ሰነፍነፍ ብለው ነበር ። በግብግቡ ሰዓት እንደ ሌሎቹ ወታደሮች ጮማ ሲቆርጡ ቢያመሹም የጥበቃ ተረኞች በመሆናቸው መጠጥ አልተሰጣቸውም ነበር ። ሌሊቱ እየገፋ ፣ ብርዱም እየከፋ ስለ ሄደ በገዛ ፈቃዳቸው ከአንድ ካሚዮን ስምንት ጠርሙስ ወይን ጠጅ አውርደው ብርዱ ከሆዳቸው እስኪወጣ ድረስ ጠጥተው ነበር...

የባሻ ቅጣው ሰዎች ከመሸጉበት ሥፍራ ተነሥተው ሌሊቱን ሲገሰግሱ አድረው ሊነጋጋ አቅራቢያ ከቢተው መኖሪያ ቦታ ደርሰው የአጥር ውጭውን ከበቡት ። ቀጥለውም በጭፍራ በጭፍራ ሆነው ድምፅ ሳያሰሙ በዘዴ አራቱን በሮች ከፍተው ጠንብዘው የተኙትን ዘበኞች በስለት መሣሪያ ጭጭ አሰኝተው ከዚያም ዘልቀው ገብተው ሠላሳ ያህል ወታደር ገድለው ፣ ከዚህ ያላነሰ አቍስለው የቻሉትን ያህል መሣሪያ ዘርፈው፣ ጎጆዎቹንና የሾህ አጥሩን በእሳት እያይዘው ፣ በመጡበት ተመልሰው ወጥተው ሸሽት ጀመሩ ።

ግርግርታው ፣ የእሳቱ ወላፈንና የቁስለኞች ጩኸት ያነቃቸው ጣሊያኖችና ባንዳዎቻቸው የሆነውን ባዩ ጊዜ



በሕልም ዓለም ውስጥ ያሉ መሰላቸው እንጂ በውን ዓለም ያሉ አልመሰል አላቸው ። ባርዚኒም ከእንቅልፉ ነቅቶ ፣ ልብሱን በጥድፊያ ለባብሶ የሆነውን ከተመለከተ በኋላ ጸጉሩን ይነጭ ጀመር ።

"ዘበኞቹ የት አሉ ? ወዴት ደረሱ ?" ሲል ጮኸ ።

"ዘበኞቹ ተገድለዋል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ" አለው ሹምባሽ እስጢፋኖስ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ። "ሽፍቶቹ ገድለዋቸው ሸሽተዋል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ።"

"ተገድለዋል ? ይገባቸዋል !" አለ ባርዚኒ በቁጣ ፤ "ወንበዴዎቹ ባይገድሏቸው ኖሮ እኔ ራሴ አስረሽናቸው ነበር ። የማይረቡ ዘበኞች !"

"በሬሳቸው አካባቢ ባዶ ጠርሙሶች ስለ ተገኙ ወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረው የነበረ ይመስላል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ።"

"ግዳጅ ላይ ሆነው መጠጥ እንዲጠጡ ማን ፈቀደላቸው ?"

"ማንም አልፈቀደላቸውም ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ። እኛ ከተኛን በኋላ በገዛ ፈቃዳቸው ወይን ጠጅ ወስደው የጠጡ ይመስላል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ። ሌሊቱ ይበርድ ስለ ነበረ ምናልባት ያሞቀናል ብለው የሠሩት ሳይሆን አይቀርም ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ።"

"ዲስፕሊን ! ዲስፕሊን ! ዲስፕሊን !" እያለ ጩኸቱን ቀጠለ ፣ ባርዚኒ ፤ ጸጉሩን እየነጨ እጁንም እያወራጨ፤ "ዲስፕሊን መኖር አለበት ! እለዚያ ውጤቱ ይኸ ነው" አለ ፤ "ሽፍቶቹ እዚህ መስፈራችንን እንዴት ዐወቁ ለመሆኑ ? ዘመቻው የታቀደው በምሥጢር ነበር።

ሽፍቶቹ ግን መምጣታችንን በቅድሚያ ቢያውቁ ነው ቀድመው አደጋ የጣሉብን ። ከመሐከላችን ከሐዲዎች አሉ ማለት ነው” አለና፣ “ከሐዲዎቹ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ፣ ሹምባሽ አስጢፋኖስ?” ሲል ጠየቀው ።

“እኔ ምን ዐውቄ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ! ከሐዲዎች ግን በእርግጥ መኖር አለባቸው” አለው ሹምባሽ አስጢፋኖስ፣ ዓይኑን እያቁለጨለጨ ።

“በል እሺ ተወው ። ይህ ጉዳይ በጥብቅ እንዲመረመር አደርጋለሁ” አለውና አርበኞቹን ለማደን ጉዞ እንዲጀመር ትዕዛዝ ሰጠ ። የጉዞው መሪም ቢተው ሆነ ።

I

የባርዚኒ ጦር በቢተው እየተመራ ረጅም መንገድ ተጉዞ ቀትር ላይ ከባሻ ቅጣው ዘመዶች ሠፈር ደረሰ ። “መላው ሠፈር መቀጣት ይገባዋል፣ ካፒታኖ ባርዚኒ” አለ ቢተው፣ በሹምባሽ አስጢፋኖስ አስተርጓሚነት ፤ “የዚህ ሠፈር ነዋሪዎች ሽፍቶቹን ባያስጠጓቸውና መጠለያ ባይሰጧቸው ኖሮ ትናንት ሌሊት የደረሰብን አደጋ ባልደረሰብን… !”

“ያቀረብከው ሐሳብ ከቶ አይደልም” አለው ባርዚኒ፣ እሱም በሹምባሽ አስጢፋኖስ አስተርጓሚነት ፤ “ለድል አድራጊው ለዱቼ መንግሥት ስለ መቆምህም ይህ ብቻውን በቂ ማስረጃ ነው ። ነገር ግን” አለ ቀጠል



አድርጎ ፤ “ነገር ግን ከሠፈረተኞቹ መሐከል የፋሺስትን አስተዳደር የተቀበሉና በሥልጣኔ ጎዳና ለመራመድ ፈቃደኛ የሆኑ ስለማይጠፉ የድል አድራጊው የዱቼ መንግሥትም በፍትሕ ስለሚያምን መላ ሠፈሩን ከመቅጣት ይልቅ ጥፋተኞቹን ለይቶ ማውጣትና ለእነሱ ብቻ ተገቢ ቅጣት መስጠት የተሻለ ይሆናል ።”

“ሽፍቶቹ በጢስ ከእያንዳንዱ ቤት መዋጮ ስለሚሰበስቡና በዚህም ወረዳ መንግሥት ማለት ሽፍቶች ያቋቋሙት እንጂ ሌላ መንግሥት የለም ስለሚሉ፣ የሠፈሩም ነዋሪዎች ይህንን አንሰማም ብለው ሽፍቶቹን በማጥፋት ፈንታ ከሽፍቶች ጋር ስለሚተባበሩ፣ የገንዘብ መዋጮም ስለሚሰጡ፣ ሁሉንም አንድ ላይ መቅጣት ይገባል፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ። አለዚያ በዚህ አካባቢ ሰላምና ጸጥታ ይኖራል ማለት ዘበት ነው ።”

ጉዳዩ ከባድና አከራካሪ ሆኖ ስለተገኘ በሁለቱ መሀከል ሊያልቅ አልቻለም ። ስለዚህ፣ ሌሎች ጣሊያኖች በተገኙበት ውይይት እንዲደረግበት ተወሰነ ። ወዲያው ጉባዔ ተጠርቶ ሁላቸውም ከተከራከሩበት በኋላ የባርዚኒን ሐሳብ የሚደግፉት ስለአየሉ አጥፊዎቹ ብቻ ተለይተው እንዲቀጡ ተወሰነ ።

ከሰዓት በኋላ ሠፈርተኞች ለስብሰባ ተጠርተው መጡ ። ቢተው እንደተለመደው የስብከት ንግግር አደረገ ። ጣሊያኖች ከመጡ ወዲህ ሥራ ፈላጊ የሆነ ሁሉ ሥራ ማግኘቱን፣ ብዙ መንገድ ሕንፃና መኖሪያ ቤት መሠራቱን፣ ንግድና እርሻ መስፋፋቱን፣ ልዩ ልዩ እንዱስትሪ በመቋቋም ላይ መሆኑን፣ በአገሩ ውስጥ ሰላምና ጸጥታ መስፈኑን፣ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች በ“ሽፍቶች” ምክንያት ሰላምና ጸጥታ መደፍረሱን በዝርዝር ገልጾ፣

ሠፈርተኞቹ ውይይት አድርገው በዚህ ሠፈር ከ "ሽፍቶች" ጋር የሚተባበሩትን ለይተው እንዲያወጡ ፥ ይህንን ሳያደርጉ ቢቀሩ ግን ሁላቸውም አንድ በአንድ እንደሚቀጡ ነገራቸው ።

ቢተው ይህንን ተናግሮ ሲጨርስ ፥ ከተሰበሰቡት ሠፈርተኞች መሐከል አንድ አዛውንት ተነሥተው ጋቢያቸውን በቅጡ አጣፍተው ለብሰው 'ሽፍቶቹ' ለሠፈርተኞቹም ጭምር አደገኛ መሆናቸውን የሠፈርተኛውንም ከብት በየጊዜው መዝረፋቸውን ፥ ገንዘብ ያዋጣ ሰው ቢኖር 'በሽፍቶቹ' ተገዶ እንጂ ወዶ ያደረገው አለመሆኑን ፥ እና ፥ ከሠፈርተኞቹ መሐከል ማናቸውም ሰው ከ "ሽፍቶቹ" ጋር አለመተባበሩን ገልጸው ቁጭ አሉ ።

የቢተው ፊት ኮሶ መሰለ ። የአዛውንቱ ንግግር ፈጽሞ አልጣመውም ። "የሚተባበር ማንም የለም ብለህ ከመለፍለፍ ይልቅ እውነቱን ብታወጣ አይሻልም ኖሯል ? "አላቸው አዛውንቱን ፥ በዓይኑ እየገረፋቸው ፤ "የሚተባበሩ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን ። ለሽፍቶቹ ስንቅ የሚያቀብሉ ፥ በየጊዜው መዋጮ የሚሰጡና ሽፍቶቹን ከቤታቸው ውስጥ የሚያሳድሩ እንዳሉ ደርሰንበታል ። የዚህ ስብሰባ ዓላማም እነዚህን ከመሐከላችሁ ለቅማችሁ እንድታወጡና ለመንግሥት እንድታስረክቡ እንጂ ጉዳዩን አድበስብሳችሁ እንድታልፉት አይደለም ።"

"አዛውንቱ የተናገሩት እውነት ነው "አለ አንድ ጎልማሳ ብድግ ብሎ ። "ሽፍቶቹ አስቸግረውናል ። ከብቶቻችንን ይነዱብናል ። 'የገንዘብ መዋጮ ካላደረጋችሁ እንዘርፋችኋለን ፥ ጎጆአችሁንም እናቃጥልባችኋለን' እያሉ ፥ በየጊዜው ይዝቱብናል ። ማንነታቸውን ለይተን እንኳን እንዳናውቅ ምናምን ተከናንበው፥ ጨለማ ለብሰው ፥ ሌሊት ሌሊት ነው የሚመጡብን ።



የኃያሉ የዱቼ መንግሥት እነዚህን ሽፍቶች ይዞ ይቀጣልን እንጂ እኛ እነሱን ለመቋቋም ምን አቅም አለን፥ ጌታዬ ?"

"ከሽፍቶቹ ጋር የሚተባበሩትን ከመሐከላችሁ አውጥታችሁ ካልሰጣችሁ በስተቀር ከዚህች ቦታ ንቅንቅ ማለት የለም" አለ ቢተው ፥ የባሰውን ተቆጥቶ ፤ "ንቅንቅ ! ሰዎቹን አውጥታችሁ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳትሆኑ ብትቀሩ ሁላችሁም አይቀጡ ቅጣት እንደምትቀጡ እወቁት" ብሎ ትቷቸው ሄደ ።

እነባርዚኒ ዘመቻው እንዳሰቡት ባለመሳካቱ በስጨት ጨት ብለው ስለነበረ ፥ ብስጭታቸውን ለመርሳት ደህል ኪያንቲያቸውን ከፍተው ሲጠጡ ነበሩ—ቢተው ወደ ነሱ በተመለሰ ጊዜ ። ለሱም ተቀዳለትና ሲጠጡ ፥ ሲያወጉ ዋሉ ። ወታደሮቹ በበኩላቸው ድንኳን ሲተክሉ ፥ ምሽጋቸውን ሲያዘገጃጁ ዋሉ ። ሠራተኞቹም ሊደርስባቸው የሚችለውን ሥቃይና መከራ በመገንዘብ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲመካከሩ ፥ ሐሳብ ለሐሳብ ሲለዋወጡ ዋሉ ።

አርበኞች ባሉበት አካባቢ የሚኖሩ ገጠሬዎች ምንም እንኳ ልባቸው ከታጋይ አርበኞች ጋር ቢሆንም ተዝናንተው አይኖሩም ነበር ። አርበኞቹን በሚረዱበት ጊዜ የፋሺስት ጥቃት ይደርስባቸው ነበር ። አርበኞችን ከመርዳት ቆጠብ በሚሉበት ጊዜ የአርበኞቹ ጫና ይሰማቸው ነበር ።

የሆነ ሆኖ በዚህ ሠፈር የነበሩት ገጠሬዎች እነ ባሻ ቅጣውን ሙሉ በሙሉ የሚደግፉ ስለ ነበሩ ማንንም ለማሳጣት ፈቃደኛ አልነበሩም ። ስለዚህም ወደ ማታ ጊዜ ቢተው ተመልሶ መጥቶ ተባባሪዎቹን አጋልጠው እንዲ

ሆነ ቢጠይቃቸው አዛውንቱ ተነሥተው ቆመው ፣ “ከሽፍቶች ጋር የሚተባበር አንድም ሰው የለም” የሚል መልስ ሰጡ ። እሱም ተመልሶ ሄዶ ለባርዚኒ ይኸንኑ አስታወቀ ። ባርዚኒም በዚህ ጊዜ ቢተው የመሰለውን ቅጣት በሠፈርተኞቹ ላይ እንዲፈጽም ሥልጣን ሰጠው ።

የቢተው ቅጣት ቀላል አልሆነም ። በሠፈርተኞቹ ስም የተናገሩት አዛውንትና የአዛውንቱን ቃል የደገፈው ጉልማሳ እያንዳንዳቸው አርባ አርባ ጅራፍ እንዲገረፉ አዘዘ ። ሁለቱ ምስኪኖች ከሱሪያቸው በስተቀር ሌላ ልብሳቸውን አውልቀው መሬት ላይ በሆዳቸው እንዲተኙ ተደርጎ ፣ የጀርባቸው ቆዳ ተገሸልጦ እስኪነግ ድረስ ተገረፉ ። አዛውንቱ ደካማ ሰው ስለነበሩ ከሞት አፋፍ ደረሱ ። ጉልማሳው ግን ጠንካራ ሰው ስለነበረ ከገርፋቱ በኋላ ያለአንዳች እርዳታ ተነሥቶ ለመቆም ቻለ ።

ከዚህም በስተቀር በርከት ያሉ ሠፈርተኞች በሠንሠለት ታስረው በጠላት ምሽግ ውስጥ እንዲቆዩ ተደረገ ። ተጨማሪ መቀጫ እንዲሆንም ከሠፈሩ ጎጆዎች አንዳንዶቹ እሳት ተለኰሰባቸው ። ጎጆዎቹ ሲቃጠሉ በውስጣቸው የነበሩ ሴቶችና ሕፃናት ልጆች እየተሯሯጡ ይወጡ ጀመር ። ከነዚህ መሐከል ድንቄና ሁለቱ ሕፃናት ልጆች ነበሩበት ። ድንቄ ሸዋርካብሽን በጀርባዋ አዝላ ዓለሜን በአንድ እጅዋ እየመራች ስትሯሯጥ ባርዚኒ አያት ።

“ቁሚ በላት...ቁሚ በላት ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ አለ ባርዚኒ ።

“ቁሚ አንቺ ሴትዮ” ሲል ተጣራ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ።



ድንቄ ቆማ ትመለከታቸው ገባች ። ባርዚኒና እስጢፋኖስ ከአጠገቧ ሲደርሱ ባርዚኒ እስጢፋኖስን እያየ ፣ “ይህቺ ሴትዮ የሽፍቶቹ መሪ ሚስት አይደለችም?” ሲል ጠየቀው ።

“ነች ፣ ካፒታና ባርዚኒ” ።

“የቤት ፍተሻ ያደረግን ዕለት ባሌ ነጋዴ ነው ያለችን ይህችው አይደለችም ? ”

“እሷ ራሷ ነች ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ።”

“ሽፍታው ባልሽ የት ነው ብለህ ጠይቃት ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። ”

“ሽፍታው ባልሽ የት ነው ብለው ይጠይቁሻል” አላት ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ። ”

“እኔ የባሌ ጠባቂ አይደለሁም ! ” አለችው ድንቄ በምሬት ። ቀጠል አድርጋም ፣ “የፋሺስት መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው አበሻን ለማሠልጠን ነው አላለም ኖሯል ይህ ፈረንጅ ? ” አለች ዓይኗን ከሹምባሽ ኢስጢፋኖስ ወደ ፈረንጁ ፣ ከፈረንጁ ፣ ወደ ሹምባሽ እስጢፋኖስ አቀያይራ እየተመለከተች ። “አበሻን ማሠልጠን ማለት እንዲህ ነው ? የድሆን ጎጆ በማቃጠል.... ሰውን በጅራፍ በመግረፍ...በሠንሠለት በማሰር...? ይህ ነው አበሻን ማሠልጠን ማለት ? ”

“ዝም በይ አንቺ ሴትዮ ! ካፒታኖ ባርዚኒ ማን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ” ሲል ጠየቃት ።

ሹምባሽ እስጢፋኖስ ባሰኘው ጊዜ ባርዚኒን “አንቱ” ባላሰኘው ጊዜ “አንተ” ብሎ ይጠራው ነበር ።

“ለምን አላውቅም ? ” አለችው ድንቄ ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስን በንቀትና በጥላቻ ዓይን እያየችው ። “ጌታህ

መሆኑን እንኳን እኔ ይህ ሕፃን ልጅ ቢሆንም አይስተውም ! ”

ሹምባሽ እስጢፋኖስ የጌታው መደፈር ያስቆጣው በመምሰል ተንደርድሮ ሄዶ ሁለት ጥፊ አላሳት ። እሷ ግን በማልቀስ ፈንታ ምራቅዋን ጢቅ አለችበት ። እንደ ገና ሊመታት ሲቃጣ ጌታው ተቆጥቶ ፤ “ማን ደብድባት አለህ ” ሹምባሽ እስጢፋኖስ ? ቃሏን ለሷ እንድትተረጉምላት የቧንም ቃል ለኔ እንድትተረጉምልኝ ነበር ያዘዝኩህ !” አለው ።

“ምላሷ እንደ ተርብ ይናደፋል ፤ ካፒታኖ ባርዚኒ ። የድል አድራጊውን የዱቼን መንግሥት ነውኮ የዘለፈችው ካፒታኖ ባርዚኒ ። ”

“ገባኝ ። ነገሩን ከሁኔታዋ ተረድቼዋለሁ ። ግን ያንተ ግልፍታ የትም አያደርስም ። እኛ ፋሺስቶች የምንፈልገውን ለማግኘት ብዙ ዘዴ አለን ። እስካሁን ያወቅከው መስሎኝ ነበር...አሁንም ሽፍታው ባሏ የት እንደሚገኝ ተናገሪ በላት ! በል ጠይቃት...ሽፍታው ባሏ የት እንደሚገኝ ትንገረን ።”

“አላውቅም ትላለች ፤ ካፒታኖ ባርዚኒ ።

“ውሸቷን ነው ! ታውቃለች ! ደህና አድርጋ ታውቃለች ! ”

“አላውቅም ነው የምትለው ካፒታኖ ባርዚኒ ። ”

“ለመናገር ፈቃደኛ ካልሆነች እሷና ልጇ ከሌሎች እስረኞች ጋር በምሽጋችን ውስጥ እንዲቆዩ ። የግዷን ትናገራለች ! ” ብሎት ወደ ሌላ ጉዳዩ አመራ ።



## ፲፩

ባሻ ቅጣውና ሰዎቹ ሩቅ አልነበሩም ። በሠፈር ውስጥ ምን እንደ ደረሰና እነባርዚኒም የት እንደ መሸጉ በቃፊሮቻቸው አማካይነት ሲከታተሉና እንደ ገና አደጋ ለመጣል ጊዜው እስኪመሽ ሲጠባበቁ ነበሩ ።

መሸ ።

እነባርዚኒ በጭፍራ ጭፍራ ሆነው እራት መብላት ጀመሩ ። ከትናንት እራት የተረፈው ሥጋ በካሚዮን ተጭኖ መጥቶ ስለ ነበረ ባንዳዎቹ ወታደሮች ዛሬም ጮማ ሲቆርጡ ነበሩ ። ባርዚኒ በግራ እጁ ትልቅ ማንኪያ ፤ በቀኝ እጁም መንሽ የሚያህል ሹካ ይዞ እስፓጌቲውን ጠምጥሞ አንሥቶ ወደ አፉ ሲወሳስድ ድንገተኛ ተኩስ ተሰማ ። ከድንጋጤው የተነሣ አፉ ላይ ያደረሰውን በመጉረስ ፈንታ እስከነሹካው ሳህኑ ላይ ወረወረውና ነጥሮ ተነሣ ። የተቀሩትም ጣሊያኖች ፓስታ አልፎርኖውን ኮትሌቱንና አሮስቶ—ዲቬቴሎውን በያለበት ትተው መሣሪያ ለማንሣት ይጣደፉ ጀመር ። የጉረሱትን እየተፉ መሣሪያቸውን ለማንሣት ጉድ ጉድ ማለት ብቻ ሆኑ ። ከዚህም ከዚያም “ሽፍቶች ናቸው! ሽፍቶች! እንዳያመልጧችሁ ! እንዳያመልጧችሁ ! ” እየ ተባባሉ ይጯጯሁና ይሯሯጡ ጀመር ።

ውጊያው ወዲያውኑ ተፋፋመ ። አርበኞቹ የእጅ ቦምብ ይወረውሩ ፤ ጠበንጃቸውንም ያንደቀድቁት ገቡ ። የጠላትም ጦር እንዲሁ ። በሁለቱም ወገን ተመትቶ የሚወድቀው ሰው ቍጥር ጥቂት አልነበረም ።

በጠላት በኩል ክፉኛ ከቆሰሉት መሐከል ቢተው ነበረበት ። በአርበኞች በኩል የተተኰሰ ጥይት ከበበተ

ኋላው የሱሪውን መቀመጫ በስቶ ገብቶ ሥጋው ውስጥ ተቀረቀረበት ። መሣሪያውን ጥሉ እሪ ይል ጀመር ። ከአጉል ቦታ ስለ ተመታ መቀመጥም በጀርባው መተኛትም አልሆንልህ ብሉት በሆዱና በጐኑ እየተገለባበጠ መንፈራገጥ ብቻ ሆነ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ድንቄና ልጆችዋ ከአንዳንድ የመንደሩ ነዋሪዎች ጋር ጠላት ምሽግ ውስጥ መኖራቸውንና ለአደጋም መጋለጣቸውን እነባሻ ቅጣው ተዞስ በጀመሩበት ወቅት አያውቁም ነበር ።

ውጊያው እጅግ በተፋፋመበት ሰዓት ድንቄ ጀርባዋ ላይ ሜና ተሰማት ። ሸዋርካብሽን ከማዘልዋ በስተቀር ተጨማሪ ሸክም አልነበራትም ። ይሁን እንጂ የልጅዋ ክብደት እየተሜናት ሲሄድ ደንገጥ ብላ አንድ እጅዋን ወደ ጀርባዋ ሰድዳ ሕፃኗን አውርዳ ወደ ደረቷ አመጣቻት ። ሸዋርካብሽ እንቅልፍ እንደ ወሰዳት ሁሉ ጸጥ ብላ ነበር ። መላ አካሏም እየበረደ በመሄድ ላይ ነበር ። በራሪ ጥይት መትቷት ለካስ ሕይወቷ አልፎ ኖሯል ። "ሞታለች እንዴ ? ሸዋዬ ! ሞታለች እንዴ ?" አለችና ድንቄ እየዬዋን ለቀቀችው ። የጥይቱ ጣሽጣሽታና የቦምቡ ብምብምታ ጆሮ የሚያስይዝ ስለ ነበረ የድንቄን እሪታና ለቅሶ የሰማ ሰው አልነበረም ።

ውጊያው ለሁለት ሰዓት ያህል ቀጠለ ። በባሻ ቅጣው በኩል ብዙ አርበኞች ሞቱ ፤ ብዙዎችም ቆሰሉ ። ድሉ ግን የነሱ ሆነ ። በጠላት በኩል ከዘመተው ጦር እኩሌታው ሲሞት ከቀረው መሐል ግሚሱ ሲቆስል ግሚሱ ተማረከ ። በጣት የሚቈጠሩት ብቻ አንድ ካሚዮን ውስጥ ገብተው ለማምለጥ ቻሉ ። ከእነዚህ ውስጥ ባርዚኒ ራሱ ፣ ቁስለኛው ቢተውና ሹምባሽ እስጢፋኖስ



ነበሩበት ። የካሚዮኑ ሹፌር ፀምን አትማጫ እንደሚነዳ እንኳ ሳይገነዘብ በጭፍን እያሳበረ ፈርጥጦ ጠፋ ።

በዚህ ውጊያ እነባሻ ቅጣው ሥፍር ቍጥር የሌለው የተዞስ መሣሪያና ጥይት ማረኩ ። ጣሊያኖች ታንኮቻቸውንና ብረት ለበሶቻቸውን አንድ ጊዜ እንኳ ሳይገለገሉባቸው ባሉበት ጥለዋቸው ስለ ሸሹ እነዚህም ተማረኩ ። ሆኖም ግን እነባሻ ቅጣው በእነዚህ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ ስላልነበራቸው ጠላት ተመልሶ መጥቶ ከሚወስዳቸው ማሰናከሉ ይሻላል በማለት ከጥቅም ውጭ አደረጓቸው ። ከዚያም በኋላ የማረኳቸውን የጠላት ወታደሮች እየነዱ አዲስ ምሽግ ለመመሥረት ጉዞ ጀመሩ ።

## ፲፱

የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ እየተስፋፋ ፣ እየተጠናከረ ሄደ—ዓመት አልፎ ዓመት በተተካ ቍጥር ። የጠላትም የበቀል ርምጃ በዚሁ መጠን እየከፋ ሄደ ። ይሁን እንጂ የበቀል ርምጃው የኢትዮጵያን አርበኞች ይበልጥ እያስቆጣቸውና እንቅስቃሴአቸውን ይበልጥ እያጠናከረው ሄደ እንጂ ለአንድ አፍታ እንኳ ሊገታው አልቻለም ። አርበኞቹ በገጠር ብቻ ሳይሆን በየከተማውም እየገቡ ሽብር እየፈጠሩ ፣ የጠላትን ኃይል ምጥ እያስያዙ ሸሽተው ይወጡ ነበር ። አዲስ አበባ ራሷ ከዚህ ሽብር ነጻ አልነበረችም ። በፋሺስቱ ገዥ በግራ

ዚያኒ ሕይወት ላይ እንኳ ሙከራ ተደርጎ የቆሰለበት ወቅት ነበር ።

ጀኔራል ግራዚያኒ ጨካኝ ወታደር እንጂ የፖለቲካ ሰው አልነበረም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈጥሮው ነጻ ነት ወዳድ ፣ አትንኩኝ ባይ ፣ ኩሩና ተጋዳይ መሆኑን ሊገነዘብ አልቻለም ። አስተዳደር ማለት ሕዝብን በፍ ርሃት ብቻ እንዲገዛ ማድረግ መስሎ ይታየው ስለ ነበረ ሥራው ሁሉ አርበኞችንና ሰላማዊውን ሕዝብ መጨ ፍጨፍ ብቻ ሆነ ። ይህ ግን የባሰ ጥላቻ አተረፈለት እንጂ ሰላምና ርጋታ ሊያስገኝለት አልቻለም ። ሮማ ውስጥ የነበረው የበላይ አለቃው ፣ ቤኒቶ ሙሶሎኒ ግን የሁኔታውን አደገኛነት በመገንዘብ የፖሊሲ ለውጥ ለማ ድረግ ወሰነ ። ለውጡንም በሥራ ላይ ለማዋል ለዘብ ያለ መሪ ስላስፈለገው ግራዚያኒን ወደ ሮማ አስጠርቶ በምትኩ ሌላ ገዥ ሾሞ ላከ ። አዲሱ ገዥ መስፍን አኦ ስታ የተባለ ነበር ።

አኦስታ ገና አዲስ አበባ ከመግባቱ በግፍ ታስረው በወህኒ ቤት ሲማቅቁ የነበሩ ሰላማዊ ዜጎች እንዲለቀቁ ትዕዛዝ ሰጠ ። በዚሁ አጋጣሚ ቸሩ በላይነህ ከሦስት ዓመት በላይ ታስሮ አራተኛውን በማገባደድ ላይ በነ በረበት ጊዜ የመለቀቅ ዕድል አገኘ ።

አኦስታ ያላግባብ ታስረው የተሠቃዩትን እስረኞች ከመፍታት አልፎ በየጫካውና በየበረሃው ሲጋደሉ የነ በሩት የኢትዮጵያ አርበኞች ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመ ለሱ ጥሪ አደረገላቸው ። የአርበኞች መሪዎችንም ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመለሱ በገንዘብና በሹመት ያባብላ ቸው ጀመር ። ከአርበኞቹ መሐከል ደከምከም ያሉትና ተስፋ የቆረጡት እጃቸውን እየሰጡ ወደ ከተማ ተመለሱ።



ኢትዮጵያ ነጻ እስክትወጣ ድረስ መሣሪያችንን አናስ ቀምጥም ፣ ትጥቃችንን አንፈታም ብለው ቃል ኪዳን የገቡት ቆራጦች ግን ትግላቸውን ቀጠሉ ።

የምሕረቱ ዐዋጅ ዜና ከባሻ ቅጣው ምሽግ በደረሰ ጊዜ ባሻ ቅጣው ከትከት ብሎ ሣቀና ፣ “ግቡ ነው የሚ ለን ቀውሴ” አለ ፣ ዓይኑን ወደ በጋሻው አዞሮ ።

“ግቡ ?”

“አዎን ።”

“ወዴት ነው የምንገባው ?”

“አኦስታን ጠይቀው እንጂ እኔን ምን ትጠይቀኛ ለህ !”

“እኛ ያለነው አገራችን ውስጥ ! ባይሆን እሱ ይውጣ እንጂ እኛ የት ነው የምንገባው ?”

“በኃይል ማስገበር ሲያቅታቸው ልምምጥ ጀመሩ ልሃ !”

“አይ ሞኝነት ! አይ የዋህነት ! የአራት ዓመት ትግል እንዲህ በልምምጥ የሚያበቃ መሰላቸው !”

“ደካማነታቸውን በገዛ እጃቸው ገሀድ እያወጡት ነው !” አለና ባሻ ቅጣው ፣ “አባት ደሞ የምንታለል መስሎት የምሕረቱ ዐዋጅ የሚያስተማምን ስላልሆነ እንዳትሞኙ ” የሚል መልእክት ላከ ።”

“አይ አባት ! መቼ አግኝቼ በሳምሁት !”

“በባርዚኔ እጅ እንዳይወድቅ ብቻ እሠጋለሁ ።”

“ቸሩ እግዚአብሔር እስካሁን እንደ ጠበቀው ሁሉ ወደ ፊትም ይጠብቀዋል ። ግድ የለህም...አትሥጋ ” አለው በጋሻው ።

## ፲፫

አባተ ሺፈራው በውስጥ አርበኝነት የጠላትን እንቅስቃሴ እየተከታተለና ወሬ እየሰበሰበ ለአርበኞች ከመላኩም ሌላ ከኢትዮጵያ ውጪ ከነበሩት ስደተኞች ጋር ግንኙነት ነበረው ። በተለይ ከግደይ ገብረእግዚአ ጋር በምስጢር ይጻጻፉ ነበር ። ደብዳቤ መላላክ አባተን ሊያጋልጥ የሚችል አደገኛ ሥራ ቢሆንም ኢትዮጵያን በሚመለከት በውጭ ዓለም የነበረውን ሁኔታ ለማወቅ ሌላ አማራጭ አልነበረውም ።

አንድ ቀን በባቡር ጣቢያ ይሠራ የነበረ አንድ ወጣት የውስጥ አርበኛ ወደ አባተ ቤት መጥቶ በቆይታ ሊያነጋግረው እንደሚፈልግ ገለጸለት ። አባተ ወደ መኝታ ክፍሉ ይዞት ገባ ።

ወጣቱ አጐንብሶ የጫማውን ክር ፈትቶ ጫማውን አውልቆ በውስጡ የነበረውን እንቦልክ አውጥቶ ሰጠው ። ወጣቱ ረጅም መንገድ ሄዶ ስለ ነበረ የእግሩ ላቦትና የመንገዱ ትቢያ ተቀላቅለው መጥፎ ጠረን ይነዙ ነበር ። አባተ ግን መንፈሱን በአንቦልኩ ላይ ጥሎ ስለነበረ ጠረኑን ልብ አላለውም ።

ግደይ ለአባተ የሚልካቸው ደብዳቤዎች በተለያዩ መንገዶች ይደርሱ ነበር ። አንዳንዶቹ እንዲህ በጫማ ውስጥ ተሸጉጠው ሌሎቹ በመልእክት አምጪው ኮት ወይም ቀብ ገበር ውስጥ ተሰፍተው ይደርሱ ነበር ። አብዛኛዎቹ አጭጭር መልእክቶች ነበሩ ። የሚጻፉበት ወረቀት ከግማሽ ገጽ አያልፉም ነበር ። ወረቀቶቹም ጭምድምዳቸው የወጣ ነበር ። ይኸውም ድንገት መሬት ላይ ወድቀው ቢገኙ እንደ ቆሻሻ እንዲቈጠሩና የማንም ዓይን እንዳይስቡ የታሰቡ በመሆናቸው ነበር ።

ይኸኛው ግን ለየት ያለ ነበር ። ወጣቱ ልጅ ተሰናብቶት ከወጣ በኋላ አባተ አንቦልኩን ቀድዶ ደብዳቤውን አውጥቶ በአርምሞ አነበበው ። እውነት አልመስል ብሎት በድጋሚ አነበበው ። መልእክቱ አሁንም አልታመን ስላለው ለሦስተኛ ጊዜ በጥሞና አነበበው ። “ይህ ነገር እውነት ይሆን ?” ሲል አሰበ ገጽታው ወገግ እያለ ፤ “ይህ ነገር እውነት ከሆነ ከማናቸውም ነገር ይልቅ የችሩን የሞራል ቁስል ሊያሽርለት የሚችል ስለ ሆነ ሄጄ ላሳየው” ብሎ ከቤቱ ተነሥቶ ወጣ ።

## ፲፬

የችሩ ሞራል በእርግጥም ቆስሎ ነበር ። በእስር ቤት የደረሰበት ሥቃይ... የአፉ መመታት...የጆሮ ግንዱ መቦቀስ...የሰውነቱ በቆመጥ መነረት...እንዲሮጥ ታዝዞ የእግሮቹ መተሳሰርና አሁንም አሁንም ከመሬት ወርዶ መፈጥፈጥ...የሌሎቹን እስረኞች ሥቃይ ማየት...ጩኸታቸውን መስማት...የዚህ ሁሉና የሌላ ሌላውም ትውስት በአእምሮው ውስጥ እየተቀሰቀሰ ያንገሸግሸው ፣ ሕይወትን እንዲጠላም ያደርገው ነበር ።

በእስር ቤት የነበረው ሁኔታ በራሱ ላይ ደርሶ ያወቀውና በሌሎችም ላይ ሲደርስ ያየው ሆኖ ሳለ በፋሺስቶች ጋዜጣ ታትሞ የሚወጣውን ስብከት በማያነብበት ጊዜ የባሰውን ይማረር ነበር ። አንድ ቀን ፣ “የቄሳር መልክተኛ” የተሰኘውን ጋዜጣ ገዝቶ ገጾቹን እያ

ንባበጠ ሲመለከት ዓይኖቹ ከአንድ አርእስተ ዜና ላይ
ዐረፉ ። ቶሎ የማወቅ ጉጉት አድሮበት ዜናውን አነበ
በው ። "በፋሺስት ሥርዓት ውስጥ እስር ቤቶች የማረ
ፊያ ቦታዎች እንጂ የሥቃይ ቦታዎች አይደሉም ። ለእስረ
ኞችም አስፈላጊው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለሆነ
እስር ቤቶች እንደ ማረፊያ ቦታ እንጂ እንደ ቅጣት ቦታ
መታየት አይገባቸውም " የሚል ነበር ። ቸሩ በላይነህ
የምሬት ሣቅ ሣቀና ከጽሑፉ ሥር የነበረውን ስም አነ
በበው ። ጸሐፊው ኢትዮጵያዊ ነበር ፤ ያውም የተማረ
ያወቀ እንደነቸሩ ባሕር ማዶ ደርሶ የመጣ ! ከትዝብትና
ከብስጭት የተነሣ ቸሩ በላይነህ እንባ አውጥቶ አለቀሰ ።
ለቅሶው ለሰውዬውም ጭምር ነበር ፤ በቁመናው የሞተ
ተንቀሳቃሽ አስከሬን እንጂ ሕያው ኢትዮጵያዊ አልመ
ሰል ብሎት ነበርና ።

ቸሩ በላይነህ በዚህና በመሳሰለው በጣም ይበሳጭ
ስለነበረ ነው አባተ ሺፈራው ፤ "ይህ ነገር እውነት
ከሆነ ከማናቸውም ነገር ይልቅ የቸሩን የሞራል ቁስል
ያሽርለታል " ብሎ ወደ ቸሩ ቤት ያመራው ።

ቸሩ በላይነህ በእስቱድዮው ውስጥ ቆሞ ሥዕል
ሲስል ነበር አባተ በገባ ጊዜ ። አባተ ሥዕሉን ገና ከማ
የቱ ስቅጥጥ አለ ። "ምነው ቸሩ... ! " አለው ።

"እ...? ምነው ? ያጠፋሁት ነገር አለ እንዴ ?"

"አይ እንዲያው... ! ይህንን አሠቃቂ ነገር ከመ
ሳል ይልቅ ለዓይን ደስ የሚል ነገር ብትስል አይሻልም
ኖሯል ?"

"ያለውን ነገር ነው ሸራው ላይ ያስፈርሁት አባተ.
የሕይወትን ገጽታ..."



"ሕይወትኮ የተለያዩ ገጽታዎች አሉት ።"
"ልክ ነህ... አልተሳሳትክም... ይኸም የሕይወት አንዱ
ገጽታ ነው ። በዚህ ሥዕል ላይ ከምታየው ሰውዬ ጋር
እስር ቤት ውስጥ አብረን ነበርን ። ቀጥቅጠው ፤
ቀጥቅጠው ጥለውት ቁስሉ በሥዕሉ ላይ እንደ ምታ
የው የተጨፈለቀ ሥጋ መሰለ ። ቁስሉ ሲውል ሲያ
ድር እየበሰበሰ ሄደ እየሸተተ... እየገማ ሄደ "

"እውነት ያየኸውን ነው የሳልከው ቸሩ ? "
"እንግዲያው ፈጥሬ የሣልኩት መሰለህ ? "
"እውነት... ? እውነት... ? "
"ብትፈልግ ልማልልህ... "
"አይ ! መሐላ እንኳ አያስፈልግም ። "

"እንግዲያውስ እመነኝ በዓይኔ ያየሁትን ነው የሣ
ልኩት ። የሕይወት አንዱ ገጽታ...የአረመኔዎች ግፍ...
ደም...ቁስል...ትል...ትላትል... "

"በል ተወው" አለና አባተ "አሁን የመጣሁት
ለሌላ ጉዳይ ! ና እስቲ አንድ ጊዜ...የማሳይህ አለኝ "
ብሎት እጁን ስቦ ወደ ሳሎኑ ወሰደው ።

"ምንድነው የምታሳየኝ ? "

"እንካ ይኸንን...አንብበው " አለው አባተ ዶብ
ዳቤውን ከኪሱ አውጥቶ እየሰጠው ።

ቸሩ በላይነህ ወረቀቱን ዘርግቶ ከተመለከካተ በኋላ
በዝምታ ያነብበው ጀመር ። አባተም የቸሩን ገጽታ ያስ
ተውል ጀመር ። ከአንድ መሥመር ወደሚቀጥለው መሥ
መር እየተሸጋገረ ንባቡን ቀጠለ ። ዝቅ ብሎ በወረደም
ቍጥር ፊቱ እየበራ ሄደ ። ገፍቶ ወርዶ ንባቡን ሲጨርስ

ከፊቱ ላይ የጭጋግ ግርዶሽ እንደ ተነሣለት ሁሉ መላ ገጽታው ፈካ ።

"ሙሉ... ሙሉ... !"ሲል ከፍ ባለ ድምፅ ተጣራ፤ "ወዲህ ነይ ሙሉ...እጥበቱን ትደርሺበታለሽ... ቶሎ ብለሽ ነይ" አላት ።

ሙሉ ከቤታቸው በስተጀርባ ልብስ ስታጣጥብ ነበረች ። እጆችዋ ላይ የተከመረውን ነጭ አረፋ በውኃ ተለቃልቃ በቀሚስዋ ጉንና ጉን እያባበሰች ወደ ቤት ገባች ። "ጋሼ አባት ነህ እንዴ ?" አለችና እምቧይ የሚያካክሉ ውብ ዓይኖቿን ወደ ቸሩ አዙራ፣ "ምንድ ነው እሱ ? ጋሼ አባት ምን ይዞልህ መጣ ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ደብዳቤ ነው...አድምጪ...ላንብልሽ" አለና ድምፁን ከፍ አድርጎ ማንበብ ጀመረ ።

ኢ. አ. አ... ፩ ቀን ፲፱፻፵
ሞምባሳ ፣ ኬንያ

ይድረስ

ለውድ ወንድሜ አ. ሺ.

አዲስ አበባ ፤

እንደምን አለህልኝ ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። አሁን ያለሁበት አካባቢ ኢትዮጵያን ያስ ታውሰኛል ። እየሩ ሣር ቅጠሉ ብዙ ዓይነት ስሜት ይቀ ሰቅስብኛል ። ይህንን ደብዳቤ የምጽፍልህ ከሞምባሳ ወደብ ከባሕሩ አጠገብ ቁጭ ብዬ ነው ። ወደቡ ባንድ በኩል ምጽዋን በሌላ በኩል ሐረርን ያስታውሰኛል ።



ከናፍቆት ሰመመንም ውስጥ ይጥለኛል ። የስደት ኑሮ ምን ያህል አስከፊ ምን ያህል አስጠሊታ መሆኑንከዚህ ቀደም ገልጬልሃለሁ ። ከሁሉም በላይ ብቸኛነቱ ባይ ተዋርነቱ ተንከራታችነቱ ተመጽዋችነቱ ይህ ሁሉ እይ ጣል ያሰኛል ። በሰው አገር ተመችቶኝ ከምኖር በአ ገሬ ተቸግሬ ብኖር በሰው አገር ተቸግሬ ከምኖር ደሞ በአገሬ ታሥሬ ወህኒ ቤት ብኖር እመርጣለሁ ያሰኝ ሃል ። የሆነ ሆኖ የግል ሮሮዬን ወደ ጐን ልተውና ወደ ቁም ነገሩ ላምራ ።

በአሁኑ ጊዜ የመላው ዓለም ሁኔታ በመደፍረስ ላይ መሆኑን በተለይም አዶልፍ ሂትለር ፖላንድን በግ ጥቃት ላይ መሆኑን ባለፈው ደብዳቤ ላይ ገረፍ ገረፍ አድርጌ ጽፌልህ ነበር ። ሂትለር ወታደሮቹን ከፖላንድ ምድር ካላስወጣ እንግሊዝና ፈረንሳይ በጀርመን ላይ ጦርነት ለማወጅ እንገደዳለን የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥ ተው ነበር ። ይኸውም እንግሊዝና ፈረንሳይ የፖላንድ የቃል ኪዳን ወዳጆች በመሆናቸው ነው ። ሂትለር ግን ወታደሮቹን ከፖላንድ ምድር በማስወጣት ፈንታ ፖላ ንድን በጦር ኃይል ይዞ ፊቱን ወደ ፈረንሳይ በመመ ለስ ፈረንሳይንም ማድማት ጀምሯል ።

እስካሁን ድረስ ቤኒቶ ሙሶሎኒ በአውሮጳ ውዝግብ ጣልቃ ሳይገባ ከዳር ሆኖ ሲያስተውል ነበር ። አሁን ግን ሂትለር ፈረንሳይን በጦር ኃይል ወግቶ ለማንበር ከከ መንግሥቱንና ይኸንንም ለማድረግ በቂ ኃይል እን ዳለው በመገንዘብ የማይቀረው የሂትለር ድል የሱም ድል እንዲሆንለት በመመኘት ከሂትለር ጋር አብሯል ። እን ግሊዝ በዚህ ድርጊት በጣም ተከፍታለች ። ሂትለርና ሙሶሎኒ አንድ ላይ ሆነው ፈረንሳይን ከደቆሱ በኋላ እሷ ራሷ የፋሺስትና የናዚ ጥቃት እንደማይቀርላት በመ ገንዘብ በጣም ሠግታለች ፣ ተናድዳለች ፣ ተቆጥታለችም ።

ይህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ አንድ የተስፋ ጭላንጭል ለማሳየት በቅቷል ። ኢትዮጵያና እንግሊዝ በምሥራቅ አፍሪቃ የጋራ ጦርነት ለመክፈት ከስምምነት ደርሰዋል ይባላል ። የስምምነቱ ዝርዝር ሁኔታ ባይገለጽም ሁለቱ አገሮች በመተባበር ጣሊያንን ለመውጋት ከስምምነት መድረሳቸው ተረጋግጧል ። በአውሮጳና በመሐከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ የኢትዮጵያ ስደተኞች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ ሱዳን እንደሚያመሩ ይነገራል ። እስካሁን ድረስ ጂቡቲ ውስጥ የነበርነው የኢትዮጵያ ስደተኞች ጂቡቲን ለቅቀን ወደ ኬንያ ሄደናል ። ይህንን ደብዳቤ ከሞምባሳ ሆኜ የምጽፍልህ ለዚህ ነው ።

የእንግሊዝና የኢትዮጵያ የጋራ ጦርነት በሁለት ግምባር እንደሚከፈት ሰምተናል ፤ አንደኛው በምዕራብ በኩል በሱዳን ጠረፍ ፤ ሁለተኛው በስተደቡብ በኩል በኬኒያ ጠረፍ ይከፈታል ። እዚህ ያለነው ሁላችንም በደቡብ ግምባር ለመዋጋት ተመዝግበናል ። እንግሊዞች ከአፍሪቃ ቅኝ ግዛታቸው ፤ ማለትም ከናይጄሪያ ከጎልድ...ኮስት...ከሱዳን ...ከታንጋኒካ...ከኡጋንዳ... ከኬንያ...ከደቡብ አፍሪቃ እንኳ ሳይቀር ወዶ ዘማቾችን በመመልመል ላይ ናቸው ።

እዚህ ኬኒያ ውስጥ ያለው ሁኔታ በጣም የሚያስደንቅ ነው ። በወዶ ዘማችነት ለመመዝገብ የሚመጡት ኬንያውያን ቍጥር ትንሽ አይምሰልህ !

ኢትዮጵያ የጥቁር ሕዝብ የነጻነት አርማ ሆና መኖርዋን በይበልጥ ለመገንዘብ የቻልሁት አሁን ነው፤ ማለቴ ስደት ከመጣሁበት ቀን ጀምሬ...ኢትዮጵያ ከአራት ዓመታት ወዲህ በፋሺስት አገዛዝ ሥር በመውደቋ ያልተቆጣ አፍሪቃዊ ወይም ጥቁር ሕዝብ ከቶ የለም ። በአሁን ጊዜ የኢትዮጵያን ትግል የሚደግፉ የጥቁር



ሕዝቦች ንቅናቄዎች በየአገሩ እየተቋቋሙ ናቸው ... በእንግሊዝ አገር...በአሜሪካ አገር... በአፍሪቃ..ወዘተርፈ። ሌላው ቀርቶ የኒው ዮርክ ከተማ ጥቁሮች ኢትዮጵያን ለመደገፍ ያህል የጣሊያን አይስክሬም እንዳይገዙ አድማ አድርገዋል ይባላል ። ከዚህም በተረፈ በሎንዶን ከተማ የሚገኙ የአፍሪቃ ተማሪዎች የፋሺስትን ድርጊት በማወገዝና ኢትዮጵያን በመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል። በዚህ በተማሪዎች ንቅናቄ የመሪነት ቦታ ከያዙት መሐከል አንደኛው የኬንያ ተወላጅ ነው ፣ ጆሞ ኬንያታ ይባላል ። አንደኛው ደሞ የጎልድ ኮስት ተወላጅ ነው፣ ክዋሜ ንክሩማ ይባላል ። ምናልባት ውጭ አገር በነበርክበት ዘመን ታውቃቸው እንደሆነ ብዬ ነው ስማቸውን የጠቀስኩልህ ።

ዋናው ቁም ነገር ግን እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ጐን መቆምዋ ነው ። እንግሊዞች ከጣሊያን ያላነሰ በምብ ጣይ አውሮፕላኖች ፣ ተዋጊ አውሮፕላኖች ፣ የጦር መርከቦች እና ለዘመናዊ ጦርነት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም ዓይነት መሣሪያ ስላላቸው ኢትዮጵያ በዚህም ሰበብ ኤርትራ እና የጣሊያን ሱማሌ ነጻ የሚወጡበት ቀን ሩቅ የሆነ አይመስለኝም ። የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎም ከንቱ ሆኖ አይቀርም ።

ወደ ጦር ግምባር የምንጓዝበት ጊዜ እየተቃረበ በመሄዱ ቶሎ ብለህ ጻፍልኝ ። አለዚያ ደብዳቤህ ሳይደርሰኝ ይችላል ።

ኧረ ለመሆኑ ች. በ. ተፈትቷል ወይንስ አሁንም ወህኒ ቤት ውስጥ ነው ? እኦስታ ብዙ እስረኞች ፈትቷል የሚል ወሬ ሰማሁ እንጂ ስለ ች. በ. ምንም አል

ሰማሁም ። ባሻስ እንዴት ነው ? ለጓደኞቻችን ሁሉ የሞቀ ሰላምታ አቅርብልኝ ።

አፍቃሪ ወንድምህ ግ. ገ

ተጨማሪ ፤
ግ.ገ. ይጠጣል እንጂ አይሰክርም ! ብትፈልግ አሁንም እንወራረድ ቻው... በሰላም ይግጠመን...በሕይወት !

ቸሩ በላይነህ ከላይ ያለውን ደብዳቤ አንብቦ ሲጨርስ እሱና አባተ ፤ አባተና ሙሉ ፤ ሙሉና ቸሩ በየተራ እየተቃቀፉ ይሳሳሙ ጀመር ። እግሩ ደህና ቢሆን ኖሮ ቸሩ በላይነህ እንደ ሕፃን ልጅ ጮቤ ሳይረግጥ ባልቀረ!

"ሙሉ...መጠጥ አምጪልን" አላት ፤ "ቶሎ በይ.. መጠጥ አምጪልንና ለደስደሱ እንጠጣ !"

ሙሉ በጥድፊያ ወደ ወጥ ቤት ገብታ ከብርጭቆና ሳህን መደርደርያ ውስጥ አንድ ያልተከፈተ ጠርሙስ አረቄና ሦስት መለኪያዎች ይዛ ተመለሰች ።

"ሆርና ላቫል የአውሮጳን ሰላም ለመጠበቅ ሲሉ ኢትዮጵያን ለሮማው ተኩላ አሳልፈው ሰጡት !" አለ አባተ እየሣሣቀ ፤ "የአውሮጳን ሰላም ለመጠበቅ ግን አልቻሉም ! የአውሮጳ ምድር እንደ ኢትዮጵያ ምድር እየጋየች ነች ! ፈረንሳይ በሂትለርና በሙሶሎኒ ተጠቃች ! እንግሊዝ ባለተራ መሆኗን ዐውቃ በገነች ! የዓለም ጦርነት ተፋፍሟል ! እኛም በሰበቡ አጋር አገኘን ! እንዴት ደስ የሚል ዜና ነው እባካችሁ !" ብሎ መለኪያውን አንሥቶ አረቄውን ጨለጠው ።

ቸሩም በበኩሉ የተቀዳለትን መጠጥ ኸው አደረገና ፤ "አዎን... አጋር አግኝተናል ! ተዋጊ አውሮጵላን ቦምብ ጣይ አውሮጵላን ውስጥ ለውስጥ ተጓዥ መርከብና ቢያስፈልግም የመርዝ ጢስ ያላት አገር" አለ ።

"ኢትዮጵያ ተሸንፋ እንደማትቀር በሕልሜ ይታየኝ ነበር" አለች ሙሉ እንደነሱ አረቄውን ኸው በማድረግ ፊንታ በኒያ በለመለሙ ከንፈሮችዋ ቀመስ ቀመስ እያደረገች ።

"ዛሬ ካልጠጣሽ መቼ ልትጠጪ ነው ሙሉዬ ? ፉት በዪው" አላት ቸሩ ።

"ደሞ ስከሪ ልታፊዙብኝ... ! እስቲ ይልቁንስ ለጋሼ አባተ ቅዳለት ።"

"በል እምጣ መለኪያህን አባተ...ወዲህ በል" ብሎ ቸሩ ጠርሙሱን ወደ አባተ መለኪያ አዘንብሎ ቀዳለት ። ለራሱም ቀድቶ እንዲሁ ሲደስቱ ሲስቁ ሲፍለቀለቁ ቆዩና ፤ "አሁን መሄድ አለብኝ" አለ አባተ ።

"ወዴት ? ይህንን ጠርሙስ እስከናጋባ ድረስ ከዚህ ንቅንቅ ማለት የለም ! ቀልድህን ተወውና ጠጣ ።"

"ዜናውን ለራሳችን ብቻ ብናስቀረው ንፉግ ያስኘናል ፤ ቸሩ ። ዜናውን በየአቅጣጫው ማሰራጨት አለብን ፤ ለውስጥና ለውጭ አርበኞች..."

"እሱማ የት ይቀራል ! ብቻ በቅድሚያ እንደሰት.. እንጠጣ ። ኢትዮጵያ ነጻ የምትወጣበት ቀን ተቃርቧል!"

"ወይ የኔ ነገር !" አለች ሙሉ በዚህ ጊዜ "የሚቀመስ ነገር ምልቶ እያለ ደረቅ አረቄ እስያዝኳሁችም አይደል !"

"ቻዲያ ለምን አላመጣሽልንም"ን አላት ቸሩ ።

"ደስታው ነዋ ያስዘነጋኝ! ደስታው!" ብላ ወደ ወጥ ቤት ደርሳ ቋንጣ በአንድ ሳህን፥ ዳቦ ቆሎ በሌላ ሳህን ይዛ መጣች።

እንዲሁ ሲጫወቱና ሲጠጡ ሳሉ ለቸሩ ያልገለጸችለት አባተ ግን በከፊል የሚያውቀው፥ በእሷ ላይ የደረሰው ፈተና ትዝ አላት...

## ፲፩

ሹምባሽ እስጢፋኖስ ከቤቷ መጥቶ ሲያባብላት ከቆየ በኋላ፥ አባተ በድንገት በመድረሱ ተደናግጦ፥ "ነገ ተመልሼ እመጣለሁ" ብሏት፥ ከጥድፊያውም የተነሣ በራፉ ላይ አባተን ገፍቶት ወጥቶ እንደ ሄደ አልቀረም። እንዳለውም በበነጋታው በምሽት ሰዓት ተመልሶ መጥቶ ነበር። ሙሉ ገና ስታየው ብርክ ያዛት። የአእምሮም ጭንቀት ተሰማት። "አይ የኔ ፍዳ! ይኸ ሰው አልተወኝም" ስትል አሰበች።

"ካፒታኖ ባርዚኒ አሁን ይዘሃት ና ብሎኛል" አላት።

"ባለትዳር ነኝ...ጥቁር ነኝ...ተገዢ ነኝ...ስለዚህ ተውኝ ብዬአችሁኮ ነበር፥ ሹምባሽ እስጢፋኖስ።"

"እንዴት ያለሽ ሞኝ ነሽ ለመሆኑ? አንቺ የካፒታኖ ባርዚኒ ወዳጅ የመሆን ዕድል አግኝተሽ እንዲህ መግደርደሩሽ..." ሲል አቋርጣው፥ "አልተግደረደር



ኩም፥ ሹምባሽ እስጢፋኖስ፥ ፈቃደኛ አይደለሁም ነው ያልኩህ" አለችው።

"ካፒታኖ ባርዚኒ አንቺን የፈለገሽ ሌላ የቤት ወዳጅ አጥቶ አይምሰልሽ። አሥርና ሃያ ሴት ልወዳጅ ቢል የሚያቅተው ሰው አይደለም። አሥርና ሃያ ሴቶ ችም ይህን ዕድል ቢያገኙ ባልጠሉ! እና ምን ዓይነቷ ሞኝ ነሽ! ፈረንጅ...አበሻ...የፈለገውን መርጦ ለመወ ዳጀት የሚችል ሰው ነው። ደሞ ሴት ጠፍቶ... !"

"ታዲያ ለምን አያረገውም?"

"ጣለበታ... ! ምን ያድርግ? አንቺን ፈለገ..."

"አልሄድም! አልሄድም!" አለች፥ በቃል ሳይ ሆን በሐሳቧ፤ ቸሩ ታስሮ እኔ አሳሪውን ለማስደሰት... የአሳሪውን ፍላጎት ለማርካት አልሄድም! ብቻ...ብቻ ባርዚኒ በእኔ ምክንያት ቸሩን ያስገድለው ይሆናል፤ ባያስገድለውም ከማይችለው ሥቃይ ውስጥ ያስገባው ይሆናል። ኧረ አዛኙቱ ምን በደልኩሽ? ምን ይሻለኛል? ከምን ዓይነቱ ፈተና ውስጥ ነው የገባሁት? ከከተማው ጠፍቼ ልውጣ? ነገር ግን ማን ያስወጣኛል? ይህንን ቤትስ ምን አደርገዋለሁ? ዘግቼው ልኮብልል? ወይንስ ምን ባደርግ ይሻለኛል? ኧረ አዛኙቱ መንገዱን አመልክቺኝ! መንገዱ ጠፍቶብኛል። ወዴት ልሂድ? ምን ይዋጠኝ? ምን ባደርግ ይበጀኛል?" ብላ ስታስብና ስታሰላስል ሳለች፥

"ምነው እንዲህ ተከፋሽ?" አላት፥ ሹምባሽ እስ ጢፋኖስ የፊቷን መጥለም አይቶ፥ "ካፒታኖ ባርዚኒኮ ጭራቅ አይደለም።"

"ጭራቅ ነው ማን አለህ?"

"አይ እንዲያው...እንዲህ ተከፍተሽ ሳይሽ..." አለና፣ "አንድ ነገር ልምከርሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

"ምን ?"

"ለባብሺና ይዤሽ ልሄድ ። እምቢ ብለሽ ብትቀሪ ካፒታና ባርዚኒ ክብሩን ያዋረድሽበት መስሎት ባንቺም ላይ ሆነ በባልሽ ላይ...በተለይም በባልሽ ላይ አስከፊ የሆነ ቅጣት ሊወስን ይችላል ። ብትሄጂለት ይሻላል ።"

ሙሉ ከበፊቱ የባሰ ጭንቀት ውስጥ ገባች ። ፋሺስቶች ከአበሻ ሴቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ 'ዘር እንዳያበላሹ' በጥብቅ የተከለከሉ መሆኑን አባተ ቢነግራትም፣ ደንብ ማውጣትና ደንቡን አክብሮ በሥራ ላይ ማዋል ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን አላጣችውም ። ጣሊያኖች ገና አዲስ አበባ ከመግባታቸው በማን አለብኝነት በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ ከኢትዮጵያ ባህል ውጭ የሆኑ አስነዋሪ ድርጊቶች እንደ ፈጸሙ ሰምታለች ። ከደንቡ ውጭ ሠርታችኋል በመባል አለመወንጀላቸውንም ታውቅ ነበር ። እሷም ባርዚኒ ያለውዴታዋ ቀረበኝ ብላ አለቃው ላይ ብትከሰው ሰሚ የምታገኝ መስሎ አልታያት ። በዚህ ላይ በተለይም በቸሩ ላይ ሊደርስ የሚችለውን መከራና ሥቃይ በዓይነ ልቡናዋ ታያትና፣ "ባርዚኒ ሥጋዬን ያረከሰው እንደሆን እንጂ ነፍሴን አያረክሰው ! ቸሩን ሊደርስበት ከሚችል ሁሉ ማዳን አለብኝ " ብላ ቆረጠችና፣ "በል እሺ እንሂድ " አለችው ።

ሹምባሽ እስጢፋኖስ ደስ ብሎት ፈገግ አለና "ጸዳ ያለ ልብስ ልበሺ !" አላት ።



"ከኔ ነው እንጂ ከልብሴ ምን አለው ! ተነሥ እንሂድ" አለችው ።

ተከታትለው ወጥተው ከአንድ የወታደር መኪና ውስጥ ገቡ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከባርዚኒ መኖሪያ ቤት ደርሰው እሱ ወደ ነበረበት ክፍል አመሩ ። ክፍሉ በጣም የጸዳ ነበር ። ባርዚኒ ፒጃማውን አጥልቆ ጋዜጣ ይመለከት ነበር ። የሙሉ አለባበስ ግን ከአካባቢው ጋር ሊመጣጠን የሚችል አልነበረም ። ባርዚኒ ፊቱን አቅንቶ ራቅ ራቅ ብለው የበቀሉ ትንንሽ ጥርሶቹን ብልጭ በማድረግ ለሙሉ ፈገግታውን አሳያት ። ሙሉ ግን ገና ስታየው ሰውነትዋ ሲሸማቀቅ፣ ፊትዋ ሲጠቁር፣ ዓይኖችዋ ዕንባ ሲያቀሩ ተሰማት ።

ሁኔታዋ ባርዚኒን ቅር አሰኘው፤ ስሜቱም በረደበት ። በአእምሮውም ውስጥ ብዙ ሐሳቦች ይነሡና ይወድቁ ጀመር ። — ይህች ውብ ሴት አልፈቀደችኝም ። ትዕዛዜን አክብራ መጣች እንጂ ለኔ ፈጽሞ ፍላጎት የላትም ። ፍላጎት ቢኖራት ኖሮ አጊጣ ለብሳ በመጣች ነበር ። እኔንም ለማስደሰት ያህል ትናንት የላኩላትን ሐብል አንገቷ ላይ አድርጋ በመጣች ነበር ። አንገቷ ግን ሌጣ ነው ። የለበሰችውም ልብስ የሥራ ልብሷ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ኩሩ ነች ይህች ውብ ሴት...በጣም ኩሩ ! ምናልባትም ይበልጥ የፈለግኋት በዚሁ በኩሩነትዋ ላይ ሆን ይቀራል ! ለማንኛውም እንድትፈቅደኝ ለማድረግ መሞከር አለብኝ—ብሎ አሰበና ሹምባሽ እስጢፋኖስን አሰናበተው ።

ሹምባሽ እስጢፋኖስ እንደ ወጣ ባርዚኒ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ ሙሉ ሄደና እጅዋን ይዞ በዓይኑ ይለማምናት ጀመር ። ፊቷን ፈካ ሰውነቷን ፈታ...ለቀቅ እንድታደርግለት ። እሷ ግን ሰውነቷን ይበልጥ ሰበሰበች

በት ። እገጪን በእጁ ይዞ ፊቷን ቀና አደረገው ። እሷ ግን
ዓይኗን ከዓይኑ አሸሸችበት ። አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ
ስሜቷን ለማሞቅ በመሞከር ጉንጯን አሻሻትና ሳመው።
እሷ ግን ሰውነቷን አበረደችበት ። ባርዚኒ ጨንቀውና
የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ያህል አንዴ አንገቷን
አንዴ ጆሮ ግንዷን አንዴም ውብ ጡቶቿን ሲደባብስ
ቆየና ዝቅ ብሎ ከንፈሯን በከንፈሩ ነካው ። በረዶ በከን
ፈሩ ያነካ ያህል ስቅጥጥ አለው ። ሙሉም እጁን ከጡቷ
አሸሻ ይባስ ብላም የሳመው ከንፈሯን በጅዋ ጠረገችው ።
የባርዚኒ ሐሞት ፍስስ አለ ። የገዛ ራሱን በመታዘብና
የገዛ ራሱን በመጥላት ጭንቅላቱን ነቀነቀና በፊት ከነ
በረበት ቦታ ሄዶ ቁጭ አለ ። አስገድጄ... ? ሲል
አሰበ ። የለም ! አላደርገውም ! በወንድና በሴት መኻ
ከል እኩል መፈቃቀድ ሳይኖር የሚፈጸም ግብረ ሥጋ
ርኪቃታ የለውም...ይህች ሴትዮ አልፈቀደችኝም ። አባ
ብዬ እንኳ አልጋ ላይ ባስወጣት ዋጋ የለውም ። በድን
አካሏን ታቅፌ ልተኛ ? የለም ! የለም ! አላደርገውም ።
ሰውነትዋ አልፈቀደኝም ። እዚህ ከፊቴ ቆሞ የማየው
በድንዋን እንጂ ስሜት ያለው አካሏን አይደለም ብሎ
አሰበና ወንበር ላይ እንድትቀመጥ በእጅ ምልክት አሳ
ያት ። ሙሉ ደረቅ ወንበር ላይ ሀረፍ አለች መሬት
መሬቱን እያየች ።

ለአንድ ሰዓት ያህል ባርዚኒና ሙሉ በዚሁ ሁኔታ
ቆዩ ። በአካል በአንድ ክፍል ውስጥ ቢሆኑም በመን
ፈስ በጣም ተራርቀው ነበር ። እሱ ጣሊያን አገር እሷ
አገሯ ውስጥ ቢሆኑ እንኳ ከዚህ የበለጠ በመንፈስ
ባልተራራቁ ! ለሙሉ ከባርዚኒ ጋር የቆየችባት ያቺ
ሰዓት እንደ አንድ ዓመት ረዘመችባት ። ባርዚኒም ከአ
ሁን አሁን ዓይኗን አቅንታ አንድ ምልክት ታሳየኛለች



በሚል ተስፋ ቢያስተውላትም ለሥጋዊ ፍላጐቱ ፍን
ከች ባለማለትዋ ተስፋ ቆርጦ ዓይኑን ወደ ጋዜጣው
መለሰ ።

ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ባርዚኒ በክፍሉ ውስጥ
የነበረውን መጥሪያ ጫን አለው ። ሙሉ የመጥሪያውን
ድምፅ ስትሰማ በርግጋ ከቀን ሕልሟ ነቃች ። ወዲያውኑ
አሽከር ገብቶ ፤ "ምን ልታዘዝ ጌታዬ ?" አለው ።

ባርዚኒ ስሜቱን አርክቶ የተደሰተ በማስመሰል
"እስከግቢው መውጫ በር ድረስ ሸኛት " አለው ። በልቡ
ግን ከፊቴ አስወግድልኝ...ሁለተኛ ዓይኗን ለማየት አል
ፈልግም...አስወጥተህ አባርልኝ ማለቱ ነበር ።

ባርዚኒ ወደ ቤቱ ያስመጣት በመኪና ቢሆንም
በጭለማ ወደ ቤቷ የተመለሰችው በእግሯ ነበር ።

አሁንም ነገሩ ትውስ ብሏት በሐሳብ ኮብልላ ሳለች፣
"የት ነው ያለሽው ሙሉዬ ? ምን ነካሽ ?" አላት ቾሩ።

"ምንም ! አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው" አለችው።

"ምንድነው እሱ ?"

"ዛሬ አይደለም የምነግርህ ።"

"ምስጢር ነው እንዴ ?"

"ምስጢርስ አይደለም ። እንዲያውም ጋሽ አባተ
ከሥር ከመሠረቱ የሚያውቀው ነገር ነው " አለችና ፤
"ይልቁንስ እንደሰት ! እንዲህ ያለ ደስ የሚል ዜና ሰም
ተን... ! "

"ጨርሰነዋልኮ ጠርሙሱን ። ሌላ ካላመጣሽልን
በስተቀር ..."

እውነትም እንዳችም ጠብታ ሳያስቀሩ ጨልጠውት ነበር ። ሙሉ ሌላ ጠርሙስ ለማምጣት ስትነሣ አባተ ብድግ አለና፣ “አሁንስ አበዛችሁት ! እኔ መሄድ አለ ብኝ...ዜናውን ለራሳችን ብቻ ሰምተን ዝም ማለቱ የሚ ያስተዛዝብ ነገር ነው ” አለና ተሰናብቷቸው ወጣ ።

፲፮

አባተ ወደ ቤቱ እንደተመለሰ ያልታሰበ እንግዳ ሲጠብቀው አገኘ ። ያ ሁሉ ደስታ...ያ ሁሉ ፈንጠዝያ.. ያ ሁሉ ፍልቅልቅታ እንዳልነበረ ሊሆን ኖሯል ። –

“ምነው መጡ እማማ ወርቂቱ ?”

“ልጄ ይዘውት ሄዱ ።”

“ማንን ? አብዬ አላናን ?”

“አዎን ፣ ይዘውት ሄዱ ።”

“ምን ጊዜ ? እነማን ናቸው ለመሆኑ ይዘዋቸው የሄዱት ?”

“አንድ ጥልያንና አንድ ባንዳ አሁን በቅርብ ከቤ ታችን መጥተው ይዘውት ሄዱ ። ከጓሮ ሆኖ እረም ሲነ ቅል ነበር ። እጁን ለመታጠብና የጠዳ ልብስ ለመል በስ እንኳ ጊዜ አልሰጡትም ። እያጣደፉ ወሰዱት ።”

“ለምን እንደ ፈለጓቸው ነገሯችሁ ?”

“ለጥያቄ ነው ያሉት ። ስለ አንድ ነገር ለጥያቄ ትፈለጋለህ አሉት ።”



“አይዞት እማማ ወርቂቱ ። ይህ ግዳጅ ለጥያቄ መሬቱን የተከመዱ ሆኗል ። የፈለጉትን ጥያቄ ጠይቋ ቸው ምንም ሲያጡ ይለቋቸዋል ” አላቸው ።

አባተ ይህንን ያለው ወርቂቱን ለማረጋጋት ያህል እንጂ እስከዚህ ቀላል ይሆናል ብሎ በግልፅ አልነበ ረም ። እንዲያውም እሱ ራሱ ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ መረበሽ አድርበት ነበር ። ነገር ግን የራሱን ፍርሃት ደብቆ ወርቂቱን ማረጋጋቱን ቀጠለ ። “በየትም የሚሆን ነገር ነው ፣ እማማ ወርቂቱ ። የተጠረጠሩትን ሁሉ ወስደው ይመረምሯቸውና ምንም ነገር ባያገኙ ቢቀሩ ፈትተው ይለቋቸዋል ። ስለዚህ አይዞዎት ” አላቸው ።

“ምን ባደርግ ይሻላል ፣ ልጄ ?”

“ምንም የሚያደርጉት ነገር የለም ፣ እማማ ወርቂቱ ። ዛሬውኑ ወደ ማታ ጊዜ ይለቋቸው ይሆናል ። አለዚያም ነገ...አለዚያም ከሳምንት በኋላ ። በትእግሥት መጠበቅ ብቻ ነው ያለብዎት ። እስከዚያም ድረስ ጥያቄን እኔ እከታተለሁ ። ለመሆኑ የሥራ ልብሳቸውን እንደ ለበሱ ነው ይዘዋቸው ሄዱ ያሉኝ ?” አላቸው በአእም ሮው ውስጥ ፈጣን ዕቅድ እያወጣ ። ከአሁን ወዲያ እን ዳችም በከንቱ የሚያጠፋው ጊዜ አልነበረውም ።

“አዎን ፣ የሥራ ልብሱን እንደ ለበሰ ነው ይዘ ውት የሄዱት ።”

“የክት ልብሶቻቸውን ያዘጋጁልኝ...ያስፈልጉ ኛል ።”

“ይዘህላት ልትሄድ ? የት እንደ ወሰዱት ባውቅ እኔ ራሴ ይዤለት እሄድ ነበር”

“ሌላ ግድ የለትም ። ልብሶቻቸውን ብቻ ያዘጋጁልኝ ። ዝግጋቸውና ገጣባዋ አህያቸውም ያስፈልጉኛል”

አባተ ምን ለማድረግ እንዳሰበ ወርቂቱ ለመጠርጠር አልቻሉም ። ሆኖም የጠየቃቸውን ሁሉ ለማዘጋጀት ቃል ገብተውለት ወደቤታቸው ለመመለስ ተነሥተው ወጡ ።

አባተ ወዲያውኑ ሰው ልኮ ማሞን አስጠራው ። ማሞም ከሚሠራበት ሆቴል ፈቃድ ጠይቆ ወደ አባተ ቤት አመራ ። እዚያ እንደ ደረሰ ፣ “ምን አዲስ ነገር ተገኘ ፣ ጋሽ አባቴ ? ዘመድ ታሞብኝ ለመጠየቅ መሄድ ስላለብኝ ፈቃድ ይስጠኝ ብዬ ዋሽቼ ነው የመጣሁት” አለው ።

“ፋሺስቶች የተጠራጠሩት አንዳች ነገር አለ ማሞ ። ከሰዎቻችን አንዱ ተይዘው ለምርመራ ተወስደዋል ። ሰውዬውን አንተ አታውቃቸውም ። እነባርኪኒ በእነባሻ ቅጣው ላይ ከመዝመታቸው በፊት ለባሻ ቅጣው መልእክት ያደረሱለት ሰው ናቸው ።”

“ያንን ዘመቻ የሚመለከት ጉዳይ ከሆነማ ሁላችንም አለቀናል ማለት ነው ፣ ጋሽ አባተ !”

“በአንተ ላይ አንዳችም ነገር ሊደርስ አይችልም ። እኔ ግን ከዚህ መጥፋት አለብኝ...የምርመራው ውጤት እስኪታወቅ ድረስ...”

“ያንን ዘመቻ የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ እኔም መሸሽ አለብኝ ፣ ጋሽ አባተ ፤ እለዚያ ያሠጋኛል ።”

“አንተን የሚያሠጋህ አንዳችም ነገር የለም ስልህ! ሰውዬው ከእኔ በስተቀር የሚያውቁት የላቸውም ። መቼም



በቀላሉ የሚበገሩ ሰው አይደሉም ። ሆኖም ሥቃይ በዝቶባቸው ቢናዘዙ የእኔን ስም ከመስጠት በስተቀር ሌላ የሚያውቁት የላቸውም ።”

“ሹምባሽ እስጢፋኖስ...”

“ከብት አትሁን ፣ ማሞ ። አቃጣሪው ራሱን ሳያስወንጅል ስለዚህ ጉዳይ አንድ ቃል እንኳ ሊተነፍስ አይችልም ። ለምርመራ የተወሰዱት ሰውዬም መልእክቱን እንዲያደርሱ እኔ እንደላክኋቸው ይናዘዙ እንደሆን እንጂ ሌላ የሚያውቁት አንዳችም ነገር የለም ። ስለዚህ ነው እኔ መሠወር ያለብኝ ። አንተንና በድርጅታችን ውስጥ ያሉትን ሌሎችንም ጭምር ለመሸፈን...”

“እንግዲያው ለምን አስጠራኸኝ ፣ ጋሽ አባተ ?”

“እኔ መሠወር እንዳለብኝ ልነግርህ ነዋ ! ሰውዬውን አሠቃይተው ለማናዘዝ ከቻሉ እኔን ፍለጋ እዚህ መምጣታቸው አይቀርም ። ስለዚህ አንዳችም ደቂቃ ሳላጠፋ መሸሽ አለብኝ ። እኔ በሌለሁበት ሥራህን ቀጥል ። መልእክት ከላክሁልህ የኔ መታወቂያ “ ቁጥር አምስት ” የሚል ይሆናል ። አንተም መልእክት ከላክህልኝ ያንተ መታወቂያ “ቁጥር አምሳ አምስት ” ይሆናል ። ተግባባን ?”

“ተግባብተናል ፣ ጋሽ አባተ ። ነገር ግን ፍርሃት ፍርሃት ብሎኛል ።”

“አንተ ላይ አንዳችም ነገር ሊደርስ አይችልም ብዬሃለሁ ። እኔ ጠፍቼ ስሄድ የከተትኩላቸው ሰንሰለት የሚበጠስ ስለሆነ አንተ ላይ ምንም ሊደርስብህ አይችልም ። አንተንም ሆነ አቃጣሪውን የሚያስጠረጥራችሁ አንዳችም ነገር አይኖርም አለና በሊሬ የታጨቀ ቦርሳ

ከኪሱ አውጥቶ ፥ "እንካ...እኔ በሌለሁበት ገንዘብ ሳያስ ፈልግህ አይቀርም...በነገራችን ላይ...ይገርምህ የቆየሁት ከቶ ወሬ ብቻ አይደለም ፥ ግጥ ። ደስ የሚል ወሬም ሰምቻለሁ ። እንግሊዞች ከጐናችን ቆመዋል አሉ ። አገ ራችን ነጻ የምትወጣበት ቀን ሩቅ አይደለም ። እና ፥ በር ትተህ ሥራ ፥ ግጥ ። ማን ያውቃል ! ምናልባት መልሰን የምንገናኘው ኢትዮጵያ ነጻ ከመውጣቷ በፊት ላይሆን ይችላል" አለው ።

"ወዴት ነው የምትሄደው ፥ ጋሽ አባተ ? አድራሻ ህን አልነገርከኝም ። "

"አድራሻዬን እዚያ ስደርስ እልክልሃለሁ ። በል ቆሁን ደህና ሰንብት ። በጣም እቸኩላለሁ ።"

አባተና ግጥ እጅ ለእጅ ተጨባበጡ ። ከዚያም በኋላ አባተ ወዴት ለመሄድ እንዳሰበ ለቸሩ እንኳ ሳይ ነገረው ተነሥቶ ጭልጥ አለ ።

## ፲፯

በእንባሻ ቅጣው እጅ ውርደት ከደረሰበት ቀን ወዲህ የባርዜኔ አእምሮ እርጋታ አልነበረውም— የአርበኞች እንቅስቃሴ ከተጀመረ ጊዜ ወዲህ እንዲያ ያለ ውድቀት አጋጥሞት አያውቅም ነበርና ። በዚህ ምክንያት ምሥጢ ሩን ያወጣበትን ሰው ለመያዝ ሌት ከቀን ይጥር ነበር ። ምንም እንኳ ፍንጭ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ቢወስድ በትም ከእውነቱ ከሚያደርሰው ጉዳና ላይ ገብቶ ነበር።



ቢተው በዘመቻው ከአጥቂ ቦታ ቆስሎ ከእኔ ባር ዜኔ ጋር አምልጦ አዲስ አበባ መጥቶ ሐኪም ቤት ገብቶ ሥጋውን በስቶ የገባው ጥይት በቀዶ ጥገና ወጥ ቶለት ፥ በግዳጅ ላይ በመቁሰሉም ለማገገሚያ ወፍራም ጉርሻ ተሰጥቶት ፥ ወደ ግዛቱ ከመመለሱ በፊት ባርዜኔ እንደ መመርያ ሰጥቶት ነበር ። ይኸውም ከዘመቻው ቀን አስቀድሞ በባሻ ቅጣው ዘመዶች ሠፈር እንግዳ የሆነ ሰው ታይቶ እንደ ነበረ አጣራ የሚል ነበር ።

ሠራተኞቹን በጅራፍ ካስገረፈና አንዳንዶቹንም በጠላት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ካስደረገ በኋላ ፥ እን ዲሁም የሠራተኞችን መኖሪያ ጉጆዎች በእሳት ካቃጠለ በኋላ የሚተባበርለትን ሰው ማግኘት ቀላል አልሆነለትም ። ሆኖም ግን የኋላ ኋላ አንድ ፍንጭ ለማግኘት ቻለ ። ምን ጥቅም ባገኝ ያለ አንድ ድሀ ሰው ወደ ቢተው ቀርቦ ፥ "በግምት አምሳ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ፊታቸው የተሸበሸበ ፥ ቁምጣ ሱሪ የለበሱ አንድ አዛው ንት ከውጊያው ዕለት ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ በባሻ ቅጣው ዘመዶች ሠፈር ታይተዋል ። አዛውንቱ በዚያ አካባቢ ሲታዩ የመጀመሪያ ጊዜአቸው አይደለም ። ዘመድ አዝማድ ለመጠየቅ አልፎ አልፎ ይመጡ ነበር። አዛውንቱ በአዲስ አበባ አካባቢ የሚኖሩ ናቸው" ሲል ገልጾለት ነበር ። የሂህ አዛውንት ዘመዶች እነማን እን ደሆኑ ቢተው በይበልጥ ካጣራ በኋላ ፥ እኒህ ዘመድ አዝ ማድ የተባሉት የባሻ ቅጣው ዘመዶች መሆናቸውን አዛውንቱም የድንቄ አጎት መሆናቸውን ሊደርስበት ቻለ ። ይህንን መረጃ ለባርዜኔ ካካለት በኋላ ነበር አባና ለጥያቄ ተፈልገው የተወሰዱት ።

## ፲፰

አባተ ሺፈራው የአባናን ተነፋነፍ ሱሪ ታጥቆ ጋቢአቸውን ደርበ፣ በራሱ ላይ መናኛ ቆብ ደፍቶ፣ በእግሩ ከአሮጌ ጎማ የተበጀ መጫሚያ ተጫምቶ፣ ባለጅንፎ ዘንግ ይዞ ጀርባው የቆሰለውን አህያ እየነዳ በሚያልፍበት ጊዜ በመንገድ ያዩት ጣሊያኖችም ሆኑ ባንዳዎቻቸው የሚፈለግ ሰው ይሆናል ብለው አንድ ጊዜም አልተጠራጠሩም። ስለዚህ ያለ ምንም እክል አራት ቀናት ሙሉ ተጉዞ ከአሰበው ቦታ፣ ከእነባሻ ቅጣው ምሽግ፣ ደረሰ። እዚያ ሲደርስ አካባቢውን ሲጠብቁ ለነበሩ ቃፊሮች ታሪኩን ቢነግራቸውም ሊያምኑት አልቻሉም።

"እውነቱን ብታወጣ አይሻልም?" አለው ከቃፊሮቹ አንደኛው፣ "እዚህ ምን ልትፈጥር መጣህ? ደሞስ ማን ነህ?"

"ባሻ ቅጣውን ፍለጋ ነው የመጣሁት ብያችሁኮ ነበር።"

"ለምን? ምን ጉዳይ አለህ ከባሻ ቅጣው?"

"ምን ብዬ ብነግራችሁ ታምኑኛላችሁ?"

"እውነቱን ተናገር አንተ ቀጣፊ! የጣሊያን ሰላይ ነህ!" አለው ቃፊሩ፤ ጠመንጃውን አመቻችቶ ይዞ።

"ባሻ ቅጣው ዘንድ፣ አለዚያም በጋሻው ዘንድ ብታቀርቡኝኮ ይህ ሁሉ ጥርጣሬ ባልኖረ!"

"ማንም ሰላይ ከእነሱ ዘንድ አቅርቡኝ ሲል የምናቀርብ መሰለህ! በል እውነቱን አውጣው ነው የምንልህ።"

አባተ ሺፈራው ግራ ተጋብቶ ዝም ብሎ ይመለከተው ገባ። ቀጠል አድርጎ፣ "አላደርስም ካላችሁኝ በዚህ ምክንያት በአርበኞች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂዎቹ እናንተ ናችሁ" አላቸው።

"ደሞ ደርሰህ እኛን ልታስፈራራ!"

"ማስፈራራቴ አይደለም። እቅጩን ነው የነገርኳችሁ።"

"ለምን አታደርሰውም?" አለ ሁለተኛው ቃፊር ለአንደኛው።

"ማንንም ሰላይ ባሻ ዘንድ እንዳቀርብ አልተነገረኝም" አለና፣ "ለመሆኑ መሣሪያ ይዘሃል?" ሲል አባተን ጠየቀው።

"ምንም ዓይነት መሣሪያ አልያዝኩም።"

"በል እጅህን ወደ ላይ አንሣ" ብሎት ይፈታትሸው ጀመር። ምንም ሲያጣ፣ "ለማንኛውም ባሻ ቅጣው በቅርብ የሉም" ሲል ዋሸው፤ "ከሌላ አርበኛ ጋር እንዳገናኝህ ከፈለግህ ግን ልወስድህ እችላለሁ።"

"ከማንኛውም አርበኛ ጋር አገናኘኝ...ባሻ ዘንድሊያቀርበኝ የሚችል ከሆነ..."

"በል እሺ ተከተለኝ" ብሎት መንገዱን ይመራው ጀመር።

ቃፊሩ አዳዲስ አርበኞች ከሚመለመሉበት ሥፍራ አደረሰው። አዲስ መጦች አርበኛ ለመሆን እንፈልጋለን ባሉ ብቻ ተቀባይነት አያገኙም ነበር። ማንነታቸውን አረጋግጦ ለማወቅ መስቀልኛ ጥያቄ ይጠየቁ፣ ጥንካሬአቸውንና ቁርጠኛነታቸውን ለማረጋገጥም ብዙ

ዓይነት ፈተና ይሰጣቸው ነበር ። ሁኔታው አጠራጣሪ ሊሆን ይደበድቡ ፣ ይገርፉም ነበር ። ይኸም በተለይ የጠላት ሰላይ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር ።

መልማዩ ጉግሬ አለንጋ ይዞ አዲስ መጡን ሲሠ ልጠው ባየ ጊዜ አባተ ስቅጥጥ አለ ። መርማሪው አር በኛ ለአባተ ሺፈራው እንግዳ ሰው ባይሆንም ማንነቱ ለጊዜው ስለ ተሠወረበት ዝም ብሎ ይመለከተው ገባ ። የበሙቀው ገጽታ በጣም ተለውጦ ነበር ። ራቁ ጸጉር ብቻ ነበር ። የራስ ጸጉሩም እንደ ዱሮው በመላጨት ፈንታ ጉፍር ይታይ ነበር ። አለባበሱም በፍጹም ተቀ ይር ነበር ። አርበኛው ግርፈያውን አብቅቶ ፊቱን ሲያ ዞር ከአባተ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ ።

"ጋሽ አባተ ! አረሳኸኝ እንዴ ?" አለው አርበኛው ።

"እንዴ... ! እንዴ... ! አንተ ተመስገን አይደለህም እንዴ ! "

"ተመስገን አይደለሁም ፣ ጋሽ አባተ ! የአሥር አለቃ ተመስገን ነው የምባል !" አለና ፊቱ ተመስገን፣ ከአቶ ዱርጮ እስከ አቶ ዱርጮ ! "በየት አሳበርህ መጣህ ለመሆኑ ፣ ጋሽ አባተ !"

"እሱቴ ባሻ ዘንድ አደርሰኝ ፣ ተመስገን ። ይህ የምትሰጠው ፈተና እጅግም አላስደሰተኝም !"

"ፈተናውን ካታልፍ ወደ ባሻ ቅጣው ልወስድህ አልችልም ፣ ጋሽ አባተ ። ደምብ ነው ፣ ጥንካሬህን ለማየት መገረፍ አለብህ ። "

"እሱቴ ቀልዱን ተወውና ወደ ባሻ ዘንድ ውሰደኝ። ታረሮቻችሁ ያጉላሉኝ እንጂ አንተ ደግ ከንሱ አትቀ ስበኝ ። "



"በል እሺ ተከተለኝ ፣ ጋሽ አባተ ፤ ቀልድ አይደለም ነው መገረፍ አለብህ ያልኩህ " ብሎት እየሣቀ መንገድ ይመራው ጀመር ። ታሪፉም ወደ ግንባር ቦታ ሰመመ ሰለ ፊቱን አዞረ ።

በባሻ ቅጣው የሚመሩት አርበኞች ቁጥር ከአንድ ሺህ ዘለል ነበር በዚህ ጊዜ ። ሁላቸውም አፈር የመ ሰለ ልብስ ለብሰው ፣ ጸጉራቸውን አጐፍረውና አንጨብ ርረው ሁለትና ሦስት ዙር ዝናር ታጥቀው ጠበንጃ አን ግበው ፣ ፊታቸውን ተናካሽ አውሬ አስመስለው ፣ ዓያቸው ሰው ያስፈሩ ፣ ያርበደብዱም ነበር ።

ባሻ ቅጣው ከሌሎች አርበኞች የሚለይበት አንዳ ችም ምልክት አልነበረውም ። በአለባበሱም በቁመናው በጠቅላላ አኳኋኑም እነሱን ይመስል ነበር ። የማዕርግ ስሙን እንዲቀይር ደጃዝማች ወይም ከዚያ በላይ ባይ ሆን ፊታውራሪ እንዲሰኝ ተከታዮቹ ቢወተውቱትም "ራሴን አልሾምም ፤ ባሻነቱ ይበቃኛል" ስላለ ፣ እንደ ዱሮው በባሻነት ይጠሩት ነበር ። አንዳንዶቹ ግን ባሻ ቅጣው በማለት ፈንታ ፣ "ባሻ አሞራው " እያሉ ያቆላ ምጡት ነበር ።

አባተ በተመስገን መሪነት ከባሻ ቅጣው ድንኳን ደርሶ ከባሻ ጋር ተሳሳመ ፤ ለረጅም ጊዜ ስለ ጤና ቸው ደኅንነት ቃላት ከተለዋወጡ በኋላ ፣ "ለመሆኑ ከበግዴ ወረዳህ ወይንስ ምድር ተፋችህ !" አለው ባሻ ቅጣው ፣ ጉንጩ ላይ የበቀለውን አጭር ጢም እየዳበሰ።

"ጠፍቼ ነው የመጣሁት ባሻ ። "

"እንዴት በል ! "

"ፋሺስቶች አብዮ አሳኘ አሰረዋቸዋል ። ከናዘዘ ቸው እኔንም ሊገቡኙኝ ሳይመጡ አይቀሩም ብዬ ጠፍቼ መጣሁ ። "

"እብዬ አላናን ያዟቸው ?"
"ይዘው አስረዋቸዋል ።"

"ዋጋቸውን ያገኙታል !" አለ ባሻ ፣ በዛቻ ድምፅ። "አንድ ዘዴ ፈጥረን ማስለቀቅ አለብን ፣ ባሻ ። እስከዚያ ሊገድሏቸውም ይችላሉ ።"

"የት እንዳሰሯቸው ካወቅሁ እስር ቤቱን አስወርረዋለሁ !" አለ ባሻ ቅጣው ፣ በአፉ የመጣለትን በመናገር ፤ "እስር ቤቱን አስወርሬ እሳቸውንና ሌሎችንም እስረኞች አስፈታቸዋለሁ" ካለ በኋላ ፣ ለአጭር ጊዜ ዝም አለና ሐሳቡን በመለወጥ ፣ "ወይ ደሞ..." አለ ፣ "ወይ ደሞ ሌላ ዘዴ አይጠፋም ። በዚያ ዘመቻ የማረክናቸው ሁለት ጣሊያኖች ከኛው ጋር አሉ ። ባርዚኒ እብዬ አላናን ለመልቀቅ ከተስማማ እነዚህን ሁለት ምርኮኞች... አልቤርቶንና ብሩኖን...ልንለቅለት እንችላለን ። ምን ይመስልሃል አባተ ?"

"ጥሩ ሐሳብ ይመስለኛል ።"

"ወይ ደሞ ...እብዬ አላናን ከገደልሃቸው አልቤርቶንና ብሩኖን እረሽናቸዋለሁ" የሚል መልእክት ብልክለት ይሻላል ። "እነዚህን ሁለት ጣሊያኖች ልለቃቸው አልፈልግም ። ከጠላት የምንማርካቸው ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ለእኛ አዲስ ስለሆኑ እነዚህ ጣሊያኖች ካላሳዩን በስተቀር ልንጠቀምባቸው የሚቸግረን ጊዜ አለ። በዚህ ረገድ አልቤርቶና ብሩኖ በጣም እየረዱን ናቸው። ስለዚህ ልለቃቸው አልፈልግም ። በሌላም በቴክኒክ ሥራ ብዙ ይረዱናል" አለና ባሻ ቅጣው ፣ "እስቲ ለማንኛውም ከተማችንን ላስጎብኝህ !" አለው ።

ተነሥተው ወጡ ። በቀልድ እንደበት "ከተማችንን ላስጎብኝህ" ያለው ጫካውን ነበር ። ገለጥ ገለጥ ያለ



ውን ሥፍራ ይዘው መዘዋወር ጀመሩ ። አርበኞቹ በአንድ ሥፍራ ለረጅም ጊዜ አይቆዩም ነበር ። ጠላት ሠፈራቸውን አውቆ አደጋ እንዳይጥልባቸው እንደ ዘላን ከአንድ ጫካ ወደ ሌላ ጫካ እየተዘዋወሩ ነበር የሚኖሩት ። ምሽግ በሚቀይሩበትም ወቅት ለውስጥ አርበኞች ስለ አዲሱ አድራሻቸው መልእክት ይልኩ ነበር ። አሁን ያሉበት ሥፍራ ጥቅጥቅ ያለ ደን ነበር ። አብዛኛውን ለኑሮ የሚያሻቸውን ነገር ከዚሁ ጫካ ያገኙ ነበር ፣ የማገዶ እንጨት... ለመጠጥና ለአጠባ የሚሆን ውኃ... የአደን አውሬ...

"ዋናውን ነገር ሳልነግርህ !" አለው አባተ ።

"ቀድመንህ የሰማነው ዜና እንዳይሆን !"

"ምን ሰማችሁ ?"

"ግልጽ ጦርነት የሚጀመርበት ሰዓት ስለ መድረሱ እንደሆነ ብዬ..."

"ሰምታችኋላ !"

"ባላምባራስ አበበ መልእክት ልከውልናል ። እሳቸውኮ ከውጪ ቀጥታ ግንኙነት አላቸው...ከሎንዶን... ማንኛውንም መመሪያ የምናገኘው በሳቸው በኩል ነው።"

"ከሆነማ ደግ !"

"አዲስ አበባ ውስጥ ሌላ ምን አዲስ ነገር አለ?" አለው ፣ ባሻ ቅጣው ።

"አዲስ አበባ ዱሮ የምታውቃት "የገጠር ከተማ አይደለችም ፣ ባሻ ። ትልቅ ከተማ ወጥቷታል ። ጣሊያኖች ፍጹም ሌላ ከተማ አድርገዋታል ። የጥንት ሮማውያን በመንገድ አቀያየስ ፣ በሕንፃ አሠራር ፣ እና ፣ በመ

ባለሱት ሥራዎች ዝነኞች እንደ ነበሩ ሳትሰማ አትቀርም።
የዛሬዎቹም ጣሊያኖች ያው ናቸው ። ይሠራሉ ፤ ያሠራ
ሉም። ወደ አዲስ አበባ ስትመለስ በጣሊያን ከተማ ያለህ
እንጂ እውነትስ ዱር በምታውቀው ፤ ምኒልክ በቆረቆ
ሩት ከተማ ያለህ አይመስልህም ፣ ባሻ ። አንዳንድ ቦታ
ዎች ለጣሊያኖች ብቻ ተከልለዋል ። ከእሽክርምቻቸው
በስተቀር ሌላ አበሻ በእነሱ ሠፈር ሊኖር አይችልም ።
ለአበሻም የተለየ ቦታ ተመድቧል ። የከተማውም ልዩ
ልዩ ክፍሎች አዳዲስ ስም ተሰጥቷቸዋል ። ለምሳሌ ፣
ካዛንቺስ...ካዛ ፖፖላሬ..ፒያሳ...ቪያ ሙሶሊኒ...ኮርሶ ፣
ቪቶርዮ አማኑኤሌ ትሬ ሬዴ ኢ ኢምፔራቶሬ...”

“ምን ? ምን ? የመጨረሻውን አልያዝኩትም ።”

“ኮርሶ ቪቶርዮ ኢማኑኤሌ ትሬ ሬዴ ኢ ኢምፔራ
ቶሬ !”

“ምን ዓይነቱ የተንዛዛ ስም ነው ፣ በል ! ለመሆኑ
የትኛው ቦታ ነው በዚህ ስም የሚጠራው ?”

“የመንገድ ስም ነው ፣ባሻ ! ከአራዳ ወደ ራስ መኮ
ንን ድልድይ የሚወስደው ዋና መንገድ ።”

“አንተ የምትኖርበት ሆቴልስ ? ስሙን ለወጡት?”

“እኔስ ከምኖርበት ሆቴል ከወጣሁ ዓመታት አል
ፈዋል ፣ ባሻ ። ጣሊያኖች አዲስ አበባ እንደ ገቡ ወዲ
ያውኑ አስለቅቀውን የለም እንዴ ! ስሙን ግን ቀይረ
ውታል ።”

“ምን አሉት ?”
“አልበርጎ ኢምፔሪያሌ ።”
“በጄ ! አራዳንስ ምን አሉት ?”



“አራዳ ያው አራዳ ነው ። በዚያ የነበረውን የዳ
ግማዊ ምኒልክን ሐውልት ግን ነቅለው ወስደው በቦ
ታው ቁልቋል ተክለውበታል ።”

“አፈረሱት ?”

“አላፈረሱትም ። ነቅለው ወስደው ከሥውር ቦታ
ጉድጓድ ቆፍረው ቀብረውታል ይባላል ። ለኔ እንደሚ
መስለኝ የምኒልክ ስም ቢነሣ ወይም እሳቸውን የሚያ
ስታውሳቸው ነገር ሲያዩ ያበግናቸዋል ። ችግሩም ታቦር
የተሠቃየው በእጁ ሽጉጥ ስለ ተገኘበት ብቻ አይደለም ።
የምኒልክ ሥዕል በቤቱ በመገኘቱም ጭምር ነው ።”

“ሌላስ ምን አደረጉ ?”

“ሌሎችንም ሐውልቶች ከነበሩበት እያነሡ በም
ርኮ መልክ ወደ ጣሊያን አገር እያጓጓዙቸው ነው ። ከእ
ነሱም የድንጋይ አምዶች አንዱን ነቅለው በመርከብ
ጭነው ወደ አገራቸው እንደ ወሰዱት ሰምተናል ። በአ
ዲስ አበባም ከባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት የነበረውን
ሐውልት ወደ ሮማ ልከውታል ።”

“ከተማውን አራቆቱት ?”

“ከተማው የነበረውን ባህላዊና ታሪካዊ መልክ
እየገፈፉ በራሳቸው መልክ እየገነቡት ናቸው ፤ ባሻ ።
አዲስ አበባ የኢጣሊያ ከተማ ነው የሚያሰኝ ነገር ሳታይ
ግማሽ ኪሎ ሜትር እንኳ ልትራመድ አትችልም ። የን
ጉሣቸው ፣ የልዑላቸውና የልዕልቶቻቸው ፎቶግራፎች፣
እና በተለይም የቤኒቶ ሙሶሊኒ ፎቶግራፎች እዚህም
እዚያም ተሰቅለው ወይም ተንጠልጥለው ይታያሉ ።
የአምባገነኑ ተሸበት ፎቶግራፍ ቁመትና በፋት ከራስ
በላይ እጅ በልጦ ፣ የመኪናን ቆብ ደፍቶ ፣ የዝሆን ጆሮ

የሚያህል የዓይን መነጽር አድርጎ ሲታይ ፣ መላውን ዓለም ለማንቀጥቀጥ ከሰማይ የወረደ ልዩ ፍጡር እንጂ ያንድ ጠይብ ልጅ የነበረ ተራ ሥጋ ለባሽ አይመስልም ። ፈጽሞ የማይበገር…የማይደፈር…መላው ዓለም የሚሰግድለት…ከሰው በላይ የሆነ የጀግና ጀግና አስመስለው ነው ለሕዝብ የሚያሳዩት…”

“ከንቱ ! የከንቱ ከንቱ !” አለ ባሻ ቅጣው ፤ “ሙሶሎኒና ሶልዳቶዎቹ የመውደቂያቸው ቀን መቃረቡን አልተገነዘቡም ! ከተማውም ከዚህ ዓይነቱ ዝባዝንኬ የሚጸዳበት ቀን ሩቅ አለ መሆኑን አላወቁም !”

## ፲፱

ኢትዮጵያ ነጻ የምትወጣበት ቀን በርግጥም ሩቅ አልነበረም ። እስከዚያ ቀን ድረስ ግን በፋሺስቶች እጅ ይሠቃዩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ጥቂት አልነበሩም ። አሳናም ከእነዚህ መሐከል አንዱ ሆነ ።

እናዛገርቸው ቀደም ባለው ጊዜ ችሩን ያሠቃየው ብረት ለበስ የመሰለው ጨካኝ ፋሺስት ነበር ። አሳና ሥቃይ ሲበዛባቸው ሳይወዱ በግድ ተናዘዙ ።

“ልጅ አባተ ነው የላከኝ” አሉት ።

“አባተ ደሞ ማነው ?” ሲል ጠየቃቸው ።

“አባተ ሺፈራው ።”



“ሺፈራው ደሞ ማን ነው ?”

“ቀኛዝማች ሺፈራው…እናንተ የረሸናችኋቸው ።”

“የ ደደብ ! ለቤተ ሰቡ ቸር ሆነንለት ነበር !” አለና ፋሺስቱ የአሳናን ኑዛዜ በጽሑፍ አድርጎ ለባርዚኒ አቀረበለት ። ባርዚኒም ሹምባሽ እስጢፋኖስንና ብረት ለበሱን አባተን ይዘው እንዲያመጡ አዘዛቸው ። ፍል ውኃ ደርሰው አባተ የት እንዳለ ቢጠይቁ አሽከሮቹ አና ውቅም አሉ ። የአባተም እናት ከተኙበት ቦታ ሆነው ምንም የሚያውቁት እንደ ሌለ ገለጹላቸው ። ሹምባሽ እስጢፋኖስና ብረት ለበሱ ተመልሰው ሄደው ለባርዚኒ ይህንኑ ነገሩት ። ባርዚኒ ጤሰ ።

“አመለጠ ?” አለ ።

“እምልቢል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ” አለው ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ።

ባርዚኒ ቡጤውን ወደ ሰማይ ሰቅሎ እያወዛወዘ ተራገመና ፣ “ወዴት ነው ያመለጠው ?” አለ ።

“ማን ያውቃል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ !”

“ሁልጊዜ ማን ያውቃል ! ማን ያውቃል ! ነው መልስህ” አለው ባርዚኒ በቁጣ ፤ “አበሻ ሆነህ ለምን አታውቅም ?”

“እንዴት አድርጌ ለማወቅ እችላለሁ ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ? እርሶ ያዘዙኝን ከመሥራት በስተቀር እንዲህ ያለውን ለማወቅ እንዴት ይቻለኛል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ?”

“በኛ ልልነት ነው ያመለጠው ! ከአሁን ወዲያ ግን ቀልድ የለም ። የአባቱም ንብረት በሙሉ ይወረሳል” አለ ባርዚኒ ፣ ምርር ፣ ብስጭት ብሎ ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ባሻ ቅጣው የላከው መልእክት ለባርዚሊ ሲደርሰው የባሰውን ጨሰ..., ነደደ... ከረረ... ዘለለ ። "ኢጣሊያ አለኝ ብትኮፈሱም ከአበርቶችና ብሩና የጥይት እሩት እንደማይረባቸው ዕወቅ ። ይህንን መልእክት የሚያመጣልህ ሰው አዛዥ አለኝ በግድ እዩት ! እስ መንገዳቸውን ከረገጡ ወደ እኔ እንዲ መለስ ይሁን" የሚል ነበር የባሻ ቅጣው ትዕዛዝ መሰል መልእክት ።

ባርዚሊ መልእክቱ ተነቦ ከተተረጎመለት በኋላ በበኩሉ ዛተ ፤ "ይህንን አመጸኛ ሽፍታ አፈር ድሜ ካላስጋጥሁት እናቴ አልወለደችኝም !" አለ ።

፪

አዲሱ ጦርነት በአዲስ ጉልበት ተጀመረ ። በምሥራቅ አፍሪቃ የነበሩት የኢትዮጵያ ስደተኞች ከእንግሊዞችና ከመለመሏቸው አፍሪቃውያን ጦረኞች ጋር ሆነው በሞያሌ በኩል ሰብረው ገብተው ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ ማምራት ጀመሩ ። በሰሜን ፤ በመካከለኛው ምሥራቅና በሱዳን የነበሩት የኢትዮጵያ ስደተኞች እንዲሁ ከእንግሊዞችና እነሱ ከመለመሏቸው አፍሪቃውያን ጦረኞች ጋር ሆነው በሱዳን ጠረፍ በኩል ወደ ጎጃም አቅጣጫ ማምራት ጀመሩ ። ጦርነቱ በሁለቱም ግንባሮች ተፋፋመ ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን አሰበን ፤ ግን ይደፍረናል ብለው ሊደፍሩና ሊመክቱ የነበሩት



ፋሺስቶች የእንግሊዝን አውሮፕላኖች ግፍት ሲደርሱ ፍርሃት ፍርሃት ይላቸው ጀመር ።

የኢትዮጵያ አርበኞች የውጭ እርዳታ መምጣቱን ካረጋገጡ በኋላ ሞራላቸው ጎበር በአዲስ ጉልበት ፤ በአዲስ ቀበቶ በአዲስ መንፈስ ተጋድሏቸውን ቀጠሉ ።

ባሻ ቅጣውና በእርሱ የሚመሩ አርበኞች ለብዙ ወራት ጠላት ባለበት ሥፍራ እየተዘዋወሩ አደጋ ሲጥሉ ፤ የጠላትን ንብረት ሲያቃጥሉ ፤ ጠላት የሠራውን ሲያፈርሱ ቆዩና ፤ "የደቡብ ግምባር ጦር አዲስ አበባን ለመያዝ ተቃርቧል" የሚል ወሬ ሲሰሙ እነሱም በመንገዳቸው ላይ ያለውን አገር እያለፉ ወደዚያው ማምራት ጀመሩ ። ወደፊት እየገፉ ይሄዱ በነበረበት ጊዜ "ባርዚሊ እናንተን ለማጥፋት ስምንት መቶ ያህል ወታደር አስከትሎ መጥቶ ከቅርብ መሽጓል" የሚል ዜና ለባሻ ቅጣው ተነገረው ።

"ሠርጋችን ነው !" አለ ባሻ ቅጣው ፤ ለአርበኞቹ የእንጋጤ ፈልጥ ! "እንግዲህ እንጠብቀዋለን ፤ ሠርጋችን ነው" አለ መልሶ ።

"የሠርጋችን አንዱ በመሆኔ እንዴት ደስ ያሰኛል" አለው አባተ ።

"ግዴለህ ውጊያውን ለኛ ተውልን ! የሠርጉ ወጋ ጋን ለማየት በተጋፈጥንበት ሰዓት እንድትደርሱልን እለ ራለሁ ።"

"እዋጋለሁ !" አለው አባተ የምሩን ። እስከዚያ ቀን ድረስ ግን ውጊያ ውስጥ ገብቶ አያውቅም ነበር ።

"ውጊያውን ለኛ ተውልን ብያለሁ ፤ አባቴ ። ይልቁንስ የፎቶግራፍ ማንሻ ያዘህ ብትመጣ ኖር እን

ዴት መልካም በሆነ ! ብዙ ማስታወሻ ይዘህ ለመመለስ በቻልህ !

“ባርዚኒን ሸሽቼ ከመጣሁ ወዲህ የይፋ የውጭ አርበኛ እንጂ የውስጥ አርበኛ አይደለሁም ፣ ባሻ ። ስለዚህ ከናንተ ጐን ቆሜ እዋጋለሁ ። ይልቁንስ ደህና ጠበንጃ ፈልግልኝ ። ”

ያን ቀን ባሻ ቅጣው በባርዚኒ ጦር ያልታሰበ አደጋ ለመጣል ወደፊት ገፍቶ አልሄደም ። ባለበት እንዲጠብቀው ወሰነ ። ይኸውም በስትራተጂ በኩል ሲታይ እነባሻ ቅጣው የነበሩበት ሥፍራ ለውጊያ አመቺ ስለ ነበረ ነው ።

ቦታው ሸለቆአማ ሆና በግራርና በጥድ ፣ በወይራና በሌላ ሌላም ዓይነት ዛፎች የተሸፈነ ፣ ለአየር ጥቃት የማያጋልጥ ነበር ። ሸለቆውን አቋርጦ የሚሄድ አንድ ጥርጊያ መንገድ ፣ በሸለቆውም ሥር ጣሊያኖች የሠሩት አንድ ድልድይ ነበረበት ።

የባርዚኒ ጦር በሸለቆው ውስጥ የነበረውን ድልድይ ተሻግሮ እንዳይሄድ በአለት ድንጋይ እንዲዘጋ ባሻ ቅጣው ትዕዛዝ ሰጠ ። አርበኞችም ትላልቅ አለቶች ከሸለቆው ግራና ቀኝ ከነበሩ ከፍታ ቦታዎች እያንከባለሉ አውርደው መሸጋገርያውን ድልድይ ዘጉት ። ጣሊያኖች የድልድዩን መዘጋት ሲያዩ ከካሚዮናቸው ወርደው አለቶቹን ለማንሣት ሙከራ በሚያደርጉበት ጊዜ ተኩስ እንዲከፈትባቸው ነበር የባሻ ዕቅድ...

ቀጥሎም ባሻ ቅጣው ጦሩን ከፍሎ በጥርጊያው መንገድ ግራና ቀኝ መከለያ አብጅቶ እንዲጠባበቅ ፣ የተቀረውም ጦር ጣሊያኖች ሸለቆውን ወርደው ሲጨ



ርሱ ወደ ኋላ ዞሮ በሩን እንዲዘጋባቸው አዘዘ ። የማርሻል ባዶልዮ ጦር አምባራዶምን ከብቦ የራስ ሙሉጌታን ጦር ከቦት እንደ ነበረ ሁሉ ፣ በባሻ ቅጣው የሚመሩት አርበኞችም የባርዚኒን ጦር በምድር ከብበው እንዲያስጨንቁት ነበር የባሻ ቅጣው ዕቅድ...

አርበኞቹ ድምፃቸውን አጥፍተው በየከለላቸው ሆነው አድብተው ይጠባበቁ ጀመር ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ የሞተር ድምፅ ሰሙ ። ሞተሮቹ ግን የካሚዮን ሞተሮች አልነበሩም ። ሰማይ ላይ ከደኑ በላይ የሚበርሩ የጦር አውሮጵላኖች ነበሩ ። በየሥርጓጉዱ የነበሩት አርበኞች አንገታቸውን አቅንተው ወደ ሰማይ አንጋጥጠው ይመለከቱ፡ ገቡ ። እነሱ አላወቁም እንጂ ሰማይ ላይ የተጧጧፈ ውጊያ በመካሄድ ላይ ነበር ። የእንግሊዝ አውሮጵላኖች በአንድ አቅጣጫ ሲበርሩ ሳሉ የጣሊያን አውሮጵላኖች በሌላ አቅጣጫ ሲበርሩ ነበሩ ። እንግሊዞችና ጣሊያኖች እንዲሁ እየበረሩ ሲጣበሱ በነበሩበት ሰዓት አንድ የእንግሊዝ አውሮጵላንና አንድ የጣሊያን አውሮጵላን በድንገት አፍንጫ ለአፍንጫ ተጋጩ ።

ወዲያውኑ በጠራ ሰማይ ላይ የእሳት ላንቃ ቱግ ሲል ታየ ። ጢሱም የነሐሴን ደመና መሰለ ። የሚነድ የብረት ስብርባሪም ራቅ ራቅ ብሎ እየወረደ መሬቱን ያጋየው ጀመር ።

የአየሩ ውጊያ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ እነባሻ ቅጣው የባርዚኒን ካሚዮኖች ጉምጉምታ ሰሙ ። ካሚዮኖቹ ቁልቁለቱን በመውረድ ላይ ነበሩ ። እያንዳንዳቸው አምሳ ያህል ነጭና ጥቁር ወታደር የያዙ ሃያ አምስት የሚሆኑ ካሚዮኖች ነበሩ ። ካሚዮኖቹ ዝግ ብለው ሲሽከረከሩ ሳሉ በላያቸው የነበሩ ወታደሮች በተጠንቀቅ ሆነው ግራና ቀኝ ሲታዩ ነበሩ ። ቀዳሚው ካሚዮን

ቁልቁለቱን ጨርሶ ወርዶ ከድልድዩ ሲደርስ ባሻ ቅጣው ራሱ ተኩሶ ከፈተ ። አርበኞችም አከታትለው ተኰሱ ።

ጣሊያኖቹ በድንጋጤ ተውጠው መርበትበት ጀመሩ ። አርበኞቹ በየጕድጓዱና በየዛፉ ጀርባ ተከልለው ስለነበረ የጣሊያን ወታደሮች ዒላማ አይተው ለመተኮስ አልቻሉም ። ስለዚህ በአጋጣሚ ብንመታ በማለት ጭፍን ተኩስ ይተኩሱ ገቡ ።

አካባቢው መልሶ ርጭ አለ ። ባርዚኒና ሰዎቹ ዙርያ ገቡን ቃኝተው ሰው ሲያጡ ፣ "ምናልባት ዝርፊያ የቋመጡ ተራ ወንበዴዎች ይሆኑ ተኩሰ ከፍተውብን የሸሹት ?" ሲሉ አሰቡ ። ዓይናቸውን ወደ ድልድዩ መልሰው አለቆቹን ሲመለከቱ የድልድዩ መዘጋት በዕቅድ የተፈጸመ እንጂ የተራ ወንበዴዎች ሥራ አልመሰላቸው ። እዚስ እንቅስቃሴ መኖር አለ ፤ መኖሩን ለማረጋገጥ ለትንሽ ጊዜ ዝም ብለው ቆዩ ። ነገር ግን እንዳችም እንቅስቃሴ ለማየት አልቻሉም ። በዚህ ጊዜ ድልድዩን ለመሻገር ቆርጠው አለቆቹን ለማንሣት ከካሚዮናቸው ሲወርዱ እንደ ገና ተኩስ ተከፈተባቸው ። በር ከት ያሉ ነጮችና ባንዳዎች ተመትተው ወደቁ ። እንዳንዶቹም ካሚዮኖች ጎማቸው በጥይት ተበሳስቶ ወደ መሬት ዝቅ እያሉ መውረድ ጀመሩ ።

የባሻ ተከታዮች ግማሾቹ በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ወጥተው ዝቅዝቅ ይተኩሱ ነበር ። ግማሾቹ ከዛፍ ግንድ ዘለተ ጀርባ ሆነው አነጣጥረው ተኩሰው ይሸሹ ነበር ። የተቀሩትም ከቆፈሩት ጕድጓድ አፍ እንደ ሌሊ ራሳቸውን ብቅ እያደረጉ የጥይት ናዳ አውርደው ፣ ራሳቸውን እንደ ገና ወደ ጕድጓዱ ውስጥ ይመልሱ ነበር ። ባርዚኒ አርበኞቹን ለማየት ባለ መቻሉ ተበሳጭቶ ቆሞና የሉ ሰዎች እንዲበታተኑና አርበኞቹን ፈልገው ዒላማ



አይተው እንዲተኩሱ እንጂ ጥይት በከንቱ እንዳያባክኑ አዘዛቸው ።

ይህ ውጊያ አስቂኝ ውጊያ ነበር ። የጠላት ወገን ጥርጣሬና ፍርሃት የሰፈነበት ነበር ። የባሻ ሰዎች ጠላታቸውን በጉልህ እያዩ እነጣጥረው ሲተኩሱ ፣ የጣሊያን ወታደሮች ግን ዒላማቸውን ለማግኘትና ለመተኰስ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸው ነበር ። በዚህ ምክንያት ውጊያው ተራዘመ ። ከሰዓት በኋላ እንሥቶ እስከ ማታ ድረስ ተኩስ ሲንጣጣ ዋለ ። ጊዜው ላይን ሲደርስ ባሻ ቅጣው ጥሩምባ አስነፍቶ ለጠላት ጦር ማስጠንቀቂያ ሰጠ ። "እጃችሁን ስጡ ! አለዚያ ከማለቅ በስተቀር ሌላ አማራጭ የላችሁም" የሚል ነበር ማስጠንቀቂያው ።

የጠላት ጦር መውጫ ቀዳዳ ስላልነበረው ምርጫው በርግጥም ይኸው ነበር ። ዳሩ ግን ጣሊያኖች እንዲህ በቀላሉ እጃቸውን ለመስጠት ሳይፈቅዱ ቀሩ ።

ሌሊት አልፎ ንጋት ተተካ ። ውጊያው እንደ ገና ተጀመረ ። የጥይቱ ጣጣጣታ እየበረከተ ሄዶ በረቀቀ ትንሽ ጋብ ሲል ተመስገን የሥቃይ ጩኸት ሰማ ። ድምፁ የማን እንደሆነ በውቀ ቁስለኛውን ለመርዳት ሩጫውን ሲል አንድ ጣሊያን አይቶት ሊተኩስበት በርከክ አለ ። ተመስገን ነቅቶበት ቀድሞ ጣለው ። ከዚያም በኋላ በአጠገቡ ደርሶ ፣ ከዝናሩ ሥር የነበረውን ስስ ነጠላ መዞ አውጥቶ ፣ በስለቱ አናቱን ቀድዶ የአባቱን ቁስል ያስር ጀመር ። አባቱ ብዙ ደም ፈሶው ነበር ። "ወደ ሌላ ጕድጓድ ተንፏቀቅህ ሂድ ጋሽ አባቱ" አለው ተመስገን ፣ የጠላትን እንቅስቃሴ በዓይኑ እየቃኘ ! "ወይንም ቆይ...ቆይ ጋሽ አባቱ ፣ እኔ ልርዳህ" ብሎ ደግፎ ወደ ጕድጓዱ ወሰደው ። "እዚህ ሆኜ እከላከልልሃለሁ ፣ እሱ

ፀሀ ጋሻ አባተ ፣ አትንቃንቅ" ብሎት በደረቱ ተኛ ፣ ጠበንጃውን በፊቱ ደግኖ ።

ወጊያው ቀኑን ሙሉ ቀጠለ ። ባሻ ቅጣው ለጣሊያኖች ድጋሚ ማስጠንቀቂያ ሰጠ ። እነሱ ግን አሁንም እጃቸውን ለመስጠት አልፈቀዱም ። ወጊያው እንደገና ተፋፍሞ ሳለ ፣ ባርዜኔና ባሻ ቅጣው በሩቅ ተያይተው ተጣቀሱ ። ሳይመታቱ ወደ አንድ ከለላ ዞር አሉ ሁለቱም ። ከዚያ በኋላ ድብብቆሽ ይጫወቱ ይመስል ባሻ ቅጣው ራሱን ብቅ ሲያደርግ ባርዜኔ ይተኩስ ፣ ባርዜኔ ራሱን ብቅ ሲያደርግ ባሻ ቅጣው በተራው ይተኩስ ጀመር ። እንዲሁ ሳይገናኙ ለረጅም ጊዜ መተኳኮሳቸውን ቀጠሉ ።

ጊዜው ወደ አሥር ሰዓት ሲሆን የባሻ ቅጣው ጦር ማየሉን ከተረዱት የጠላት ባንዶች መሐከል አንዳንዶቹ መሣሪያቸውን ጥለው እጃቸውን ለመስጠት ወደ እነባሻ በኩል መሮጥ ጀመሩ ። የገዛ ወገናቸው ተኩስ ከፍቶ አንዳንዶቹን በመሐል መንገድ አስቀራቸው ። የተቀሩት ግን አምልጠው ሄደው እጃቸውን ሰጡ ።

የጠላቷ ጦር ሞራል እየላሸቀ ሄደ ። ወጊያው ግን ቀጠለ ። በሁለቱም ወገን በርከት ያሉ ጦረኞች ይወድቁ ፣ በርከት ያሉም ቆስለው ይሠቃዩ ነበር ። ይበልጥ ጉዳት የደረሰበት ግን የጠላት ጦር ነበር ።

የሰማይ አሞሮች ዓይናቸውን በሬሳ ላይ ተክለው ሲያንዣብቡ ፣ ሲያማትሩ ፣ ሲሰልሉ ቆዩና የሥጋና ደም እምርት አላስችል ብሏቸው ቀስ በቀስ ወደ ምድር መውረድ ጀመሩ ። የተኩስ ድምፅ ሲሰሙ ሽሽት እያሉ ተሆሱ ጋብ ሲል ተመልሰው መጥተው የሙታንን ዓይን እየጐረጐሩ እያወጡ ፣ የተዝረከረከ ሥጋ ሲያጋጥማቸውም



መንቆራቸው ይዘው ይጐትቱ ጀመር ። አንዳንድ ጊዜም ክፉኛ ቆስለው መንቀሳቀስ ያቃታቸውን ጦረኞች ሲያዩ የሞቱ እየመሰላቸው ይዳፈሯቸው ነበር ።

ቀኑ እንደ ገና መሽቶ እንደ ገና ነጋ ። በሦስተኛው ቀን ወጊያው ከምን ጊዜም ይልቅ በተፋፋመበት ሰዓት ባርዜኔ ግንባሩን ተመትቶ ወደቀ ። "ማማ ሚያ!" ብሎ ጸጥ አለ ።

የባርዜኔ ጦር ከዚያ በኋላ ወጊያውን ለመቀጠል በቂ ኃይልም ሆነ የመንፈስ ጽናት አልቀረውም ነበር ። ስለዚህ ጣሊያኖቹም ፣ ባንዳዎቻቸውም መሸነፋቸውን አምነው መሣሪያቸውን እየወረወሩ እጃቸውን ለመስጠት ይራኮቱ ጀመር ።

እነባሻ ቅጣው የወደቁባቸውን የጦር ባልደረቦቻቸውን አስከሬን በቃሬዛ ተሸክመው ከቅርብ ወደ ነበረ ቤተ ክርስቲያን ወስደው ፣ ጸሎት አስደርሰው ካስቀበሩ በኋላ ቁስለኞቻቸውን በየሠፈሩ አስተኝተው እንዲያገግሙ አደረጉ ። የአባተ ቁስል እስከዚህም ከባድ አልነበረም ። ይሁን እንጂ ቁስሉ በወደቀ ጊዜ ብዙ ደም ስለ ፈሰሰው እሞታለሁ የሚል ሥጋት አድሮበት ነበር ። ለጥቂት ቀናት ዕረፍት ተደርጎ የእሱም ቁስል ጠገግ እያለ ሲሄድ ግን በሕይወቱ ተሰምቶት የማያውቅ ደስታ ተሰማው ።

"ወጊያውን ለኛ ተውልን ብለህ አምቢ አልከኝ ፣ እሺ ብትለኝ ኖሮ ግን ባልቆሰልክ" አለው ባሻ ቅጣው ፣ የዕረፍት ጊዜ አልቆ የአዲስ አበባ አቅጣጫ ጉዞአቸውን እንደ ገና ሲጀምሩ ። ከቆሰሉት መሐከል አንዳንዶቹ አባተ ጭምር ኮርቻ ላይ ነበሩ ። ፈረሶቹና በቅሎዎቹ ከየጠሩ በግዥም ሆነ በስጦታ የተገኙ ነበሩ ። ያልቆሰሉ አርበኞች ግን ምርኮኞቻቸውን እንደ ከብት እየነዱ በእግር ሲጓዙ ነበሩ ።

"ገንዘብን ያልሞተክ ብቻ!" አለው ባሻ ፣ ቅጣው ቀጠል አድርጎ ።

"በምንተም ባልተቀጣዋኝ ! በባርነት ከመኖር ነጻ ሆኖ መሞት ይበልጣል ...ኧረ ጊዜ... !" አለው አባተ ።

"ካልተዋጋሁ ያልኸውን አውርደ አላለሳለበኝም ! የወገኔ እልቂ..የወገኔ ወሬ...የወገኔ እምቢ ባይነት.... የወገኔ አልበገሬነት በእኔም ደም ሥር ውስጥ አለ ለማለት ፈልገህ ባይሆን እደቀርም !" ብሎ ግቶ ባሻ ቅጣው ።

"በዚህ ጉዳይ ላይ ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ተከራክረንበታል ፣ ባሻ ። አውርደ አላለሳለበኝም አላልኩም ። ነገር ግን ሰውን የሚያሰለሳለውና የሚያጠነክረው የጊዜው ሁኔታ እንጂ ሌላ አይደለም ። ከፋሺስት ወረራ በፊት በውስጥ አርበኝነትም ሆነ በአርበኝነት የምሳተፍበት ቀን ይኖራል ብዬ ያሰምኩበት ጊዜ አልነበረም ። ነገር ግን ይኸው ጊዜው አስገድዶኝ ባለሁበት ሁኔታ እገኛለሁ ። በመቀበሉም ከፍ ያለ ኩራት ይሰማኛል ።" ሲለው ላለ ምርኮኞቹ በነበሩበት አቅጣጫ ከፍ ያለ ጫጫታ ተሰማ ። ባሻና አባተ ጨዋታቸውን አቋርጠው ወደዚያው አመሩ ። ከምርኮኞቹ አንዱ መራመድ አቅቶት መሬት ላይ ተነጥፎ ነበር ። በወገኑ ጊዜ ደራ ቀን ከሰዎች ተመትቶ ኖሮ ጉሁ በሚያደርግበት ወቅት መሬት መሬት ተበጥቶ ነበር ።

"እንጨርሰው ፣ ባሻ !" ሲል ጠየቀ አንድ ወጣት አርበኛ ፣ ጠበንጃውን በቁስለኛው ራስ ላይ ደግኖ ። ሌሎቹ ምርኮኞች ባይንጫጩበት ኖሮ ገና ዱር ሳይጨርሰው ባልቀረ ።

"ገለልበል !" አለው ባሻ ቅጣው ቱግ ብሎ ፣ "ምርኮኛ እንደማይገደል እስከ ዛሬ ድረስ አታውቅም ! ይል



ቁስሉ በቅጠል ፈልጎና ከርቤ ላይ አውጣው" አለውና ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

"ሰውዬውን ዐውቀዋለሁ" አለው አባተ ።

"የቱን ?" ሲል ጠየቀው ባሻ ።

"የወደቀውን ምርኮኛ"

"ምን አገናኛችሁ?"

"ከዚህ ቀደም ሙሉን አግብቶ ለባርያ ሊያቀርባት ያላደረገው ነገር የለም ።"

"ምን ! የኛን ሙሉ?"

"እምንሰጠታውን ሰብስበን ያቀጥቀጥባት ነበር ።"

"አይደረግም !"

"ሲያደርግ ነው የከረመው ባሻ ። ነገር ግን እንዳሰበው አልሆነላቸውም ። ሙሉ መች ተበገረላቸው ። ሹምባሽ አስጠቁማስ ባርያ ቤት ድረስ ይዟት ሄዶ በቀይታ እንዲገናኙ ካደረገ በኋላ ለፋሺስቱ ባለቤቱ የሲቪልና ንቀት ልምዱን አፍሰሰ ለመመለስ በትታለች ።"

"እንዲያ ነው እንጂ ቆራጥነት ! እረ ለመሆኑ ምን ዓይነቱ አታጣሪ ኖረል በል ?"

"እረ አሱስ ብዙ ነገር ነው ! ባንድ ሬት አታጣሪ፣ በሌላ ሬት ባንዳ ፣ በምስኪኑ መልኩ ደግሞ ለኛ ወሬ አቀባይ..."

"እንዴት በል ?"

"አንድ ቀንበት አብሮ አባና ያመጣው መልእክት በዚህ ባንዳ ያገኘነው ነበር ። ወሬውን በአምስት መቶ ሊሬ ሸጠልን ።"

“እንዲህ ያለም ሰው አለ ?”

“ሞልቶ !”

“ማን ይባላል ለመሆኑ !”

“ሹምባሽ እስጢፋኖስ ።”

“ጉድ ነው !” አለና ባሻ ቅጣው በተዘከሮ ዓለም ውስጥ ገባ ። ሕፃን ልጁ ፣ ሽዋርካብሽ ትዝ አለችው ።

“በሰሞኑ ውጊያ አንድ ባንዳ በሞቱም ሆነ በቁሙ አገኘዋለሁ ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር ። ነገር ግን ደብዛው ጠፋብኝ” አለ ።

“ማነው እሱ ?”

“አንተ የምታውቀው አይመስለኝም ። ዱሮ ሽፍታ የነበረ ፣ ጣሊያኖች ከገቡ ወዲህ ግራዝማች የሚል ማዕረግ ሰጥተው በሕዝብ ጫንቃ ላይ ያስቀመጡት ፣ እነ ባርዚኒን እየመራ ያመጣብን ፣ ለልጄ ለሽዋርካብሽ ሞት ምክንያት የሆነ ፣ ቢተው የሚባል ነበር” አለው ባሻ ቅጣው ።

“ታዲያ ስለሱ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ይነግርሀ የለም እንዴ ! በዚያ ዘመቻ ተካፋይ የሆነ ሰውኮ ነው ፣ ባሻ ።”

“እሱቴ ከተሻለው እጠይቀዋለሁ ” አለና ፣ “ቢተው በሕይወቱ ካለ ምን ጊዜም አልምረውም ። ብምረው እግዚአብሔር አይምረኝ” ሲል ማለ ።

“አንድ ነገር አስታወስከኝሳ ፣ ባሻ !”

“ምንድነው እሱ ?”

“ሽዋርካብሽ ክርስትና የተነሣችበትን ቀን ታስታውሰዋለህ ? ያን ቀን ከአንተ ቤት ቁጭ ብለን ድፎ ዳቦ



እየበላን ፣ ጠጅ እየጠጣን ስንጫወት በነበርንበት ሰዓትኮ ነው የነጋሪቱን ድግዝድጊታ የሰማነው ። ትዝ ይልሃል ?”

“እንዴታ አባተ ! እንዴታ !”

ነገርን ነገር ያነሣዋልና ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ በአየአምሮአቸው ያወጡ ፣ ያወርዱ ጀመር ።

ዐዋጁ ከተነበበ በኋላ በግቢ አካባቢ የተሰማው ሽለላ...የዘመቻው ዝግጅት...በግቢ የተደረገው ሰልፍ... ጉዞ ወደ ሰሜን ግምባር...የቀበሮው አጋጣሚ...የምሽት ግብር...የአምባራዶም ከበባ...የባሻ ቅጣውና የፈረንጁ ትግል...የከበባው መሰበር...ሽሽት...የአረሩ ሞት...በምንጩ አካባቢ ያደረጉት ዕረፍትና የወንድ አዳኞች በድንገት መምጣት...የማይጨው ጦርነት...አሁንም ሽሽት.. በአሸንጌ ሐይቅ አካባቢ የታየው የሬሳ ክምር...የሴሊት ጉዞ...የእዴላ ሞት...በአላና ቤት ያደረጉት ዕረፍት... የአርበኝነት ዘመን መጀመር...አሁን ያሉበት ሁኔታ...!

“አምስት ዓመት !” አለ ባሻ ቅጣው ።

“አዎን ፣ አምስት ዓመት !” ሲል መለሰ አባተ “የአምስት ዓመት ተጋድሎ !”

መንገዱ ቢያደክማቸውም ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ከአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ሲደርሱ በደቡብ በኩል የዘመተው የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ጥምር ጦር ገፍቶ መጥቶ በትናንትናው ቀን ዋናውን ከተማ ነጻ ማውጣቱን ፣ በምዕራብ በኩል የዘመተው የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ጥምር ጦር ከሱዳን ጠረፍ ተነሥቶ ጠላትን እየወጋ ገፍቶ መጥቶ ጐጃም መድረሱን ሰሙ ።

ቀጥሎ በነበሩት ሳምንታት ጦርነቱ በጅማ በጐን ደር በአምባላጌና በሌሎችም ቦታዎች ተጧጥፎ ስነበተ። የጠላት ኃይል በየቦታው ፍርክስክሱ እየወጣ ስለ ሄደ መሰሎኒ በኢትዮጵያ ምድር የመጨረሻ ውድቀት ደረሰበት። በሰሜን አፍሪቃና በአውሮጳም ተመሳሳይ ውድቀት ይጠብቀው ነበር። የገዛ ሕዝቡም "ዱቼ! ዱቼ!" እያለ እንዳላከራረው ሁሉ ገደሉ የዘቅዝቅ ሊሰቅለው የነበረበት ቀን ሩቅ አልነበረም።

## ፴፩

የኢትዮጵያ ሕዝብ አምስት ዓመት ሙሉ በትእግሥት ሲጠብቀው የነበረ ቀን እውን ሆነ። ከሰሜን አዲስ አበባ እስከ ደቡብ አዲስ አበባ፥ ከምዕራብ አዲስ አበባ እስከ ምሥራቅ አዲስ አበባ ያሉ ደብሮች የምሥራች ደወላቸውን ይደውሉ ጀመር። የአዲስ አበባ ሕዝብ ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ግቢ ድረስ ባለው መንገድ ግራና ቀኝ ተሰልፎ፥ ሴቶች እልልታቸውን ያቀልጡት፥ ካህናትና ደብተራዎችም ከበሮ ይደልቁ፥ ያሸበሽቡ፥ ስፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀርቡ ጀመር።

የድል ቀን ሰልፍ ረጅም ነበር። በቅድሚያ ባለ ሞተርሳይክሎች ሞተርሳይክሎቻቸውን እያንዶቀዶቁ አለፉ። የታንክ ሠልፍ ተከተለ፤ ቀጥሎም የፈረሰኛ ሠልፍ። የኢትዮጵያ አርበኞችና የእንግሊዝ ወታደሮች ደጀን ይዘው ለጡ። ሠልፉ ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ግቢ ድረስ በሚያልፍበት ጊዜ ሁሉ ሕዝቡ በያለበት ሆኖ! ይል፥ ይዘፍን፥ ይጨፍር ነበር።



አትለውም ወይ...
አትለውም ወይ...
የጦር ገበሬ...
አይደለህም ወይ...
አላልኩህም ወይ...
አላልኩህም ወይ...
የማታ ማታ...
ድሉ የኛ ነው...
አላልኩህም ወይ...

እያለ ሲዘፍን፥ ሲጨፍር፥ ሲሸልል ቆየና በመጨረሻም ወድቆ የተነሣው የኢትዮጵያ ባንዲራ እንደ ገና በኢትዮጵያ አየር ላይ መውለብለብ ጀመረ።

የበዓሉ ፍጻሜም ሲደርስ ሕዝቡ በየቤቱ ተመልሶ ከዘመድ አዝማድ ጋር ሆኖ ይበላና ይፈነጥዝ፥ ይበላና ይደሰት ጀመር።

ያን ቀን ማታ የባሻ ዘመዶችና ወዳጆቹ እሱ ዘንድ ለማምሸት ወስነው ስለ ነበረ እያንዳንዳቸው የያዙትን መሰናዶ ይዘው ወደዚያ ማምራት ጀመሩ። አባናና ወርቂቱ ከእንጦጦ፥ ቾፋና ሙሉ ከራስ መኩንን ድልድይ አካባቢ፥ ቢጋሻውና ባለቤቱ ከባቡር ጣቢያ፥ ግደይና ግማ ከኢቱጌ ሆቴል፥ አባተ በቻውን ከፍል ውኃ፥ እና ሌሎችም ከያሉበት ተነሥተው ወደ አራዳ አቅጣጫ ሲያመሩ ነበሩ።

ባሻ ቅጣው አዲስ አበባ ከገባበት ቀን ጀምሮ አራዳ ውስጥ በሚገኙና ባሊያናች ባሠሩት በአንድ ድንጋይ ቤት ውስጥ አርፎ ነበር። ድንጋዩና ግለሚም ከባላገር ተመልሰው ነበር። የኢሥር አለቃ ተመስገንም ቋሚ ሥራና ቋሚ መኖሪያ ቤት እስኪያገኝ ድረስ ለጊዜው አንድ ክፍል ተሰጥቶት እዚያው አርፎ ነበር።

ባሻና ድንቂ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ተቀምጠው ወዳጆቻቸውን ሲጠባበቁ በነበሩበት ሰዓት ፥ "አንድ ነገር ሳልነግርህ ባሻ" አለችው ድንቂ ።

"ምን ኖሯል ?"

"ለአራዳው ጊዮርጊስ አንድ ድልብ በሬ ማስገባት እንዳለብን !"

"ድልብ በሬ ? ምን አሳሰበሽ ደሞ ?"

"ስለት አለብን ፥ ባሻ ። የቆየ ስለት...ከአምስት ዓመታት በፊት ወደ ጦር ግምባር በዘመትክበት ወቅት አንተ በደህና ከተመለስክ ጧፍ ገዝቼ ለማስገባት ፥ ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸናፊ ከሆነች አንተና እኔ አንድ ድልብ በሬ እንድናስገባ ተስዬ ነበር ።"

"እስከዛሬ ድረስ ነግረሽኝም አታውቂ ፥ ድንቂ ። እንዲህ ያለ ስለት ካለብሽ ግን ስለቱን እናደርስለታለና! እንዲያውም አንድ ድልብ በሬ ብቻ ሳይሆን አንድ ሸህር ጭምር እናስገባለታለን" አላት ፥

እንዲሁ ሲጨዋወቱ ሳሉ በመንገድ የነበሩት ተከታትለው መግባት ጀመሩ ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ሲሆን የእንግዳ መቀበያው ክፍል ተጣበበ ። መጠጥ ተቀድቶ ግብግቡና ፈንጠዚያው ተሟሟቀ ።

ዓለሜ ከወዲህ ወዲያ ፥ ከወዲያ ወዲህ ሲሯሯጥ ፍልቅልቅታ ሲያሳይ ቆየና በመጨረሻም ወደ ባሻ ሄዶ፥

"አባዬ" አለው ።

"እ... ?"

"ጠበንጃህን ልተኩሰው ፥ አባዬ...ፍቀድልኝ" አለው ።



«አትችለውም ፥ ዓለሜ»

«እችለዋለሁ ፥ አባዬ...አስተኩሰኝ» አለው ።

«በል እሺ ከቻልከው...ምን ችግረኝ !» አለው ባሻ ።

ጠበንጃው በጣም ከባድ ስለነበረ ዓለሜ መሣሪያውን በቅጡ ለመያዝ ይታገል ጀመር ። የሰውም ሁሉ ዓይን በሱ ላይ ዐረፈ ። ባሻ ቅጣው መሣሪያው ወድቆ እንዳይባርቅ በመፍራቱ ዓለሜን ያግዘው ገባ ። የጠመንጃውን አፈ ሙዝ ወደ ተከፈተው መስኮት አዙሮ ፥ «በል አሁን ቃታውን ሳበው» አለው ። ቃታው ደረቅ በመሆኑ ዓለሜ ሊስበው አልቻለም ። ባሻ ቅጣውም ፥ «ቆይ ትንሽ ላግዝህ» ብሎ ጣቱን በዓለሜ ጣት ላይ ጫነው ። ቀጥሎም ፥ «በል አሁን ሳበው» አለውና የዓለሜን ጣት በጣቱ ጫን አለው ። ተኩሱ ብም ሲል ሴቶቹ ተደናገጡ ። ጠበንጃው የጐረሰ መሆኑን ያልተገነዘቡትም ወንዶች ግር ተሰኙ ። ባሻ ቅጣው ግን ደስ ብሎት እየሣቀ ፥ «ጐበዝ !» አለው ዓለሜን ፥ «ወደፊት ሌላ ጠላት ቢነሣብን የአርበኝነቱ ተራ ያንተ ይሆናል !»

አላና ይህንን ሲሰሙ ስቅጥጥ አሉ ። «እንዲህ ያለ ነገር ምን አሳሰበህ ፥ ባሻ ? ለመደሰት ተሰብስበን ሳለን እንዲህ ያለ ነገር መናገር ባልተገባህ... በተለይም ለሕፃን ልጅ !» አሉት ።

አላና በጠላት እጅ ክፉኛ ተሠቃይተው ነበር። የድብደባው ምልክት በፊታቸው ላይ ነበር ። አንድ ዓይናቸውም አያይላቸውም ነበር ። በዓይናቸው አካባቢ የነበረ ጅማት ከመጐዳቱ የተነሣ ቅንድባቸው ከቆጥጥራቸው ጠጭ ሆኖ ያለ ዕረፍት ሰውን የሚጠቅስ ይመስል ነበር ።

«ኢትዮጵያ ላይ ተንሥተው ሌላ ጠላት ሊነካ አይችልም ማለትም ነው ፤ አብዬ አላና ? አይምስ ልዎት ?» አላቸው ባሻ ።

«እንደገና በኛ ሕይወት ላይ ደንበራችንን የሚደፍር ሌላ ጠላት እንዳይነሣብን ፈጣሪያችን እንማጸናለሁ ። እንነጋገርኛል... እንነጋገርኛል... !» አሉ ።

«ሁሉም የሁላችንም ምኞት ነው፤ አብዬ አላና፤ ነገር ግን ደንበራችንን የሚገፉ ፤ ቤት ንብረታችንን የሚያጠፉ ጠላቶች በኢትዮጵያ ላይ አይነሡ ሎ ትም ለማለት አይቻልም ።»

ባሻና አላና እንዲሁ በሚጫወቱበት ጊዜ ልጆቹ በየፊናቸው ሌላ ጨዋታ ይዘው ነበር ። ግደይ በስተደቡብ አቅጣጫ ስለተደረገው ጦርነት ፤ አባተ ስለ ጥቡሉ ፤ ቸሩ በእስር ቤት በነ በረበት ጊዜ ስላጋጠሙት ነገሮች ሲጨዋወቱ ቆዩና በመጨረሻም ቸሩ ዓይኑን ወደ ባሻ ትጣው አዞር ፤ «በዘመድና በወዳጅ ፊት አንድ የምጠ ይቅህ ነገር አለኝ ፤ ባሻ» አለው ።

«ለአርበኝነት ለመመልመል ፈልገህ ከሆነ በምሆን ለአሥር አለቃ ተመስገን መስጠት አለ ብህ... እሱም ትንሽ ፊትና ይሰጥሃል!» ብሎ ሲሥቅ ሌሎቹም ተመስገን ጭምር ከትከት ብለው ሳቁ ።

«ቀልዱንኮ አይደለም ባሻ ፤ አንድ የምጠ ይቅህ ነገር አለኝ ።»

«በልኮ ተናገር !»

«ዓፈረሁን ከማላጥርህ በፊት ልስልህ እፈ ልጋለሁ ባሻ ።»

«ታዲያ እሱ ምን ችግር አለው ?»



“ችግርስ የለበትም ። ብቻ ሥዕሉ አንተን ላይመ ስል ስለሚችል በቅድሚያ ልንገርህ ብዬ ነው ።”

“እኔን ከሣልህ ሥዕሉ እኔን ላይመስል እንዴት ይቻላል ? ወይንስ ፊቴን ትተህ ጐፈሬዬን ብቻ ለመ ሣል ነው የምትፈልግ ?”

“አንተ ‘ሞዴል’ እንድትሆንልኝ እንጂ አንተን በአንተነትህ ልሥልህ አይደለም ፍላጎቴ ።”

“እንዴት በል ?”

“እየህ ባሻ...” አለው ቸሩ ፤ ካስፈለገ አንድን ሰው ራሱን በቀጥታ መሣል ይቻላል ። ወይንም ለሚፈለገው ነገር ትምሳሌት እንዲሆን ተደርጎ ሊሣል ይቻላል ።”

“አልገባኝም ” አለው ባሻ ቅጣው ።

“አንተን ራስህን ብሥልህ ቁ—ርጥ አንተን ይመ ስላል ። አንተን በትምሳሌነት ወስጄ የአርበኛን ሥዕል ብሥል ግን አንተን ላይመስል ይችላል ።”

“የእኔ አምሳያ አድርገህ የምትሥለውን ሥዕል የማን ሥዕል ነው ልትል ነው ? ምንስ ብለህ ትጠራዋ ለህ ?”

“ግሩም ጥያቄ ! ” አለው ቸሩ ፤ እየሣሣቀ ።

“እኮ ፤ ምን ብለህ ልትጠራው... ?”

“የአርበኛው ገጽታ ።”

“የአርበኛው ገጽታ ? የየትኛው አርበኛ ?”

“የኢትዮጵያ አርበኛ ነዋ !”

"እንዲያው እገሌ ሳይባል ?"

"አዎን ፣ እገሌ ሳይባል ።"

"ታዲያ ምን ቸገረኝ ! በፈለግህ ጊዜ ልትሥለኝ ትችላለህ ፣ ቸሩ ።"

ጨዋታው ፣ መጠጡ ፣ ጠቅላላ ፈንጠዚያው ቀጠለና መንፈቀ ሌሊት ላይ ሁላቸውም ብርጭቆአቸውን ለመጨረሻ ጊዜ አስሞልተው ብርጭቆ ለብርጭቆ አጋጭተው ፣ "እቶ ሙሶሎኒ ምን አቅበጠበጠው ፣ አልነገረውም ወይካዱ ያመለጠው !" የተሰኘውን ሽለላ ከመካከላቸው አንዱ ጦረኛ ቆፍጣና ወኔው እያንዘፈዘፈው በመረዋ ድምፁ ሲያንቀረቀረው ከሰሙ በኋላ ወደ የቤታቸው አመሩ ።